# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ሐሙስ

83ኛ ዓመት ቁጥር 122 ጥር 2 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!







# ‹‹የኢትዮጵያ ዲፕሎማሲ ከራሷ አልፎ ለጥቁር ሕዝቦች ጉልህ አስተዋጽኦ አበርክቷል››

*- አቶ ደመቀ መኮንን*
*ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር*

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ ለዘመናት ያደረገችው ዲፕሎማሲያዊ እንቅስቃሴ ከራሷ አልፎ ለአፍሪካውያን ብሎም ለጥቁር ሕዝቦች ጉልህ አስተዋጽኦ ማበርከቱን ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን ገለጹ።

አቶ ደመቀ መኮንን ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር በነበራቸው ቆይታ እንዳሉት፤ በቅኝ ግዛት ዘመን ኢትዮጵያ ብቸኛዋ የጥቁር ሕዝብ ወኪል ሆና በሊግ ኦፍ ኔሽን ተሳትፋለች። ይህም የኢትዮጵያ ዲፕሎማሲ ከራሷ አልፎ ለአፍሪካውያንና ለሌሎችም ጥቁር ሕዝቦች ትልቅ አስተዋጽኦ እንዳበረከተች የሚያመላክት ነው።

በቀደምት ዘመናት ኢትዮጵያ በልዩ ልዩ መንገድ የውጭ ግንኙነት ታካሂድ እንደነበር አስታውሰው፤ ከ116 ዓመት በፊት የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ተቋቁሞ ሥራው ተቋማዊ መደረጉን አውስተዋል።

በዛሬው ዕለት የሚከፈተው ‹‹የዲፕሎማሲ ሳምንት›› ያለፉት ዓመታት የዲፕሎማሲ ጉዟችን ያሉንን ወረቶች ማየት፣ አሁን ላይ በዲፕሎማሲው ዘርፍ ያሉ ዕድሎችና ፈተናዎችን መለየትን የሚሉ ዓላማዎችን አንግቦ እንደሚካሄድ ጠቁመው፤ ያለፉትን ዓመታት ልምዶችና አሁናዊ ሁኔታዎችን በመገንዘብ በቀጣይነት ብሔራዊ ጥቅማችንን አስጠብቀን ለማሻገር ምን መደረግ አለበት የሚለውን ለማየት እንዲሁም የመጪው

‹‹የኢትዮጵያ ዲፕሎማሲ.. ወደ ገጽ 6 ዞሯል



ፎቶ፡ ሳሙኤል ተስፋዬ






## የማዕድን ሀብትን በአግባቡ ጥቅም ላይ ለማዋል ምን ይደረግ?

ገጽ 6



## ባንኮች ለኢንተርፕራይዞች ብድር እያቀረቡ አይደለም

**ውብሸት ሰንደቁ**

አዲስ አበባ፡- ባንኮች ብሔራዊ ባንክ በሚያዘው መሠረት ለኢንተርፕራይዞች ብድር እያቀረቡ አለመሆኑን የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር አስታወቀ።

የሥራና ክህሎት ሚኒስትር ዴኤታ ንጉሡ ጥላሁን እንደገለጹት፤ ባንኮች በዓመታዊ የብድር ዕቅዳቸው ውስጥ ኢንተርፕራይዞችን እንዲያካትቱ የብሔራዊ ባንክ መመሪያ የሚያዝ ቢሆንም በመመሪያው መሠረት

ባንኮች ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል

# ለድርቅ አደጋ በተጋለጡ አካባቢዎች የከፋ ችግር እንዳያጋጥም ተከታታይ ድጋፍ ይደረጋል

- ለስድስት ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ዜጎች የሠብዓዊ ድጋፍ ይቀርባል

**ጌትነት ተስፋማርያም**

አዲስ አበባ፡- ለድርቅ አደጋ በተጋለጡ አካባቢዎች ችግሩ ወደ ረሃብ እንዳይቀየር ተከታታይ የሠብዓዊ ድጋፍ እንደሚደረግ የአደጋ ሥጋት አመራር ኮሚሽን ኮሚሽነር አምባሳደር ሽፈራው ተክለማርያም (ዶ/ር) አስታወቁ።

በአሁኑ ጊዜ የአስቸኳይ ርዳታ ድጋፍ የሚሹ አራት ሚሊዮን ዜጎች መኖራቸውን፤ በቀጣይ ሦስት ወራት ደግሞ ስድስት ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ዜጎች ድጋፍ እንደሚያስፈልጋቸውና የሠብዓዊ ርዳታ እንደሚቀርብ ተገልጿል።

አምባሳደር ሽፈራው ተክለማርያም (ዶ/ር) ትናንት በሰጡት መግለጫ እንዳመለከቱት፤ ለድርቅ አደጋ የተጋለጡ አራት ሚሊዮን ሰዎች በመኖራቸው ችግሩ ወደ ረሃብ አደጋ እንዳይቀየር አስፈላጊው ድጋፍ ይደረጋል።

የአስቸኳይ የምግብ ርዳታ የሚያስፈልጋቸው

ለድርቅ አደጋ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል



ፎቶ፡ ዳኜ አበራ







# “በመዲናዋ የሚገኙ ሕንጻዎች ለአካል ጉዳተኞች ምቹ ባለመሆናቸው አገልግሎት ለማግኘት እየተቸገርን ነው”

## -የአዲስ አበባ ከተማ አካል ጉዳተኞች ማህበር

# “ግንባታዎች ከዲዛይናቸው ጀምሮ ለአካል ጉዳተኞችና ለአቅመ ደካሞች ተደራሽ ሆነው እንዲገነቡ ክትትል እየተደረገ ነው”

## -የአዲስ አበባ የግንባታ ፍቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን

**ቃልኪዳን አሳዬ**



አዲስ አበባ፡- በመዲናዋ የሚገኙ የተለያዩ ሕንጻዎች ለአካል ጉዳተኞች ምቹ ባለመሆናቸው አገልግሎት ለማግኘት ችግር እየፈጠረ ነው ሲል የአዲስ አበባ ከተማ አካል ጉዳተኞች ማህበር ገለጸ፤ የአዲስ አበባ የግንባታ ፍቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን በበኩሉ ግንባታዎች ከዲዛይናቸው ጀምሮ ለአካል ጉዳተኞችና ለአቅመ ደካሞች ተደራሽ ሆነው እንዲገነቡ ክትትል እያደረገ እንደሆነ አስታውቋል።

የአዲስ አበባ ከተማ አካል ጉዳተኞች ማህበር ፕሬዚዳንት አቶ ገለታው ሙሉ ለኢፕድ እንደገለጹት፤ በመዲናዋ የሚገኙ የተለያዩ ግንባታዎች ለአካል ጉዳተኞች ምቹ አይደሉም። አብዛኞቹ የሕዝብ አገልግሎት መስጫ ተቋማት በትላልቅ ሕንጻዎች ላይ የሚገኙ በመሆኑ አካል ጉዳተኞች የሚፈልጉትን አገልግሎት ለማግኘት እየተቸገሩ ነው።

እንደ አቶ ገለታው ገለጻ፤ ለዊልቸር ተጠቃሚዎች ሕንጻዎች ላይ ለመውጣት ቀርቶ ወደ ጊቢው እንኳን ለመግባት ትልቅ ተግዳሮት እየገጠማቸው ነው፤ ይህንን አልፈው ቢገቡም እንኳን አሳንሰር የሌላቸው ሕጻንዎች በመኖራቸው የሚፈልጉትን አገልግሎት አያገኙም።

በየተቋማት ተቀጥረው የሚሠሩ አካል ጉዳተኞች በየሕንጻዎች የሚገኙ መጸዳጃ ቤቶች ለእነሱ አመቺ ባለመሆናቸው ምክንያት ውሃ ለመጠጣትና ምግብ ለመመገብ አዳጋች እየሆነባቸው መሆኑን አንስተው፤ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት እነኚህን ችግሮች እየተረዱት አይደለም ብለዋል።

በየትምህርት ቤቶች የሚገኙ ሕንጻዎች ተደራሽ አለመሆን አካል ጉዳኞች ትምህርት እንዳይማሩ እንቅፋት እየፈጠረ በመሆኑ ማህበራዊና ሥነ ልቦናዊ ቀውሶች እየደረሰባቸው መሆኑን ገልጸው፤ አካል ጉዳቶች ለህክምና ወደ ሆስፒታሎች ሲሄዱም ተመሳሳይ ችግር እንደሚያጋጥማቸው አመልክተዋል።

ችግሩን እንዲያስተካክሉት ለመንግሥትም ሆነ ለግል ተቋማት ቢነገራቸውም የተለያዩ ሰበቦችን እንደሚያቀርቡ ያነሱት ፕሬዚዳንቱ፤ ለአብነትም ባንኮች ሕንጻዎቻቸው ለአካል ጉዳተኞች ምቹ እንዳልሆነ ቢነገራቸውም ሕንጻው የነሱ እንዳልሆነና ተከራይተው እንደሚሠሩበት ምክንያት እንደሚያቀርቡ ጠቁመዋል።

አካል ጉዳኞች በእነኚህ ምክንያቶች በማንኛውም ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ መብትና ጥቅማቸውን በአግባቡ እየተጠቀሙ ባለመሆኑ ከተለያዩ እንቅስቃሴዎች እየተገለሉ ነው ብለዋል።

የማህበሩ ዓላማ ግንዛቤን በመፍጠር የአካል ጉዳተኞችን መብትና ጥቅም ማስከበር መሆኑን አንስተው፤ አሁን ላይ የተወሰነ የግንዛቤ ለውጥ ቢኖርም በሚመለከታቸው አካላት ላይ ግንዛቤውን ወደ ተግባር ከመቀየር አኳያ የቁርጠኝነት ማነስ በመኖሩ ማህበሩ የሚያከናውናቸው ተግባራት በውጤት ሲገለጹ አይታይም ነው ያሉት።

የአዲስ አበባ የግንባታ ፍቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የግንባታ ክትትልና ቁጥጥር ዳይሬክተር ኢንጂነር ከማል ጀማል በበኩላቸው፤ ግንባታዎች ከዲዛይናቸው ጀምሮ ለአካል ጉዳተኞችና ለአቅመ ደካሞች ተደራሽ ሆነው እንዲገነቡ ክትትል እየተደረገ ነው ብለዋል።

የከተማ ፕላንና የሕንጻ አዋጅን መሠረት በማድረግ በተለይም የሕዝብ ግልጋሎት መስጫ ግንባታዎች ለሁሉም ዜጎች ተደራሽ መሆናቸው ሲረጋገጥ የግንባታና የመጠቀሚያ ፍቃድ እንደሚሰጥ ገልጸው፤ ሕጎችን፣ ደንቦችንና መመሪያዎችን በመከተል ክትትል እንደሚደረግ ጠቁመዋል።

የሕንጻ የመጠቀሚያ ፍቃድ ሲሰጥ ትልቁ መስፈርት ዲዛይኑ ላይ በተቀመጠው መሠረት ለአረጋውያንና ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽ ሆኖ ሲገነባ ነው። የሕዝብ መገልገያ ሕንጻዎች ሲሠሩ ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽ እንዲሆኑ ማድረግ ግዴታ መሆኑን ዳይሬክተሩ አስገንዝበዋል።

ይህንን መስፈርት አሟልተው ለማይገኙ የሕንጻ ባለንብረቶች ጊዜያዊ የመጠቀሚያ ፍቃድ ለአንድ ዓመት ያክል ተሰጥቷቸው እንዲያሟሉ ይደረጋል ነው ያሉት።

አሁን ተግዳሮት እየሆነ ያለው የሕንጻ አዋጁ ሳይሻሻል ከዚህ ቀደም አካል ጉዳተኞችን ከግምት ውስጥ ሳያስገቡ የተገነቡ አንድ አንድ ሕንጻዎች መኖራቸውን የጠቀሱት ዳይሬክተሩ፤ እነሱንም ማሻሻያ አድርገው ለሁሉም ዜጎች ተደራሽ እንዲያደርጉ እየተደረገ መሆኑን ጠቁመዋል።

እንደ ኢንጂነር ከማል ገለጻ፤ የሚሰጠው የግንባታ ፍቃድ ለአምስት ዓመት የሚቆይ ሲሆን ግንባታው ተጠናቆ የመጠቀሚያ ፍቃድ ሲሰጥ አሳንሰር፣ የአካል ጉዳተኞች መቀመጫ፣ የአደጋ ጊዜ መውጫና ሌሎችም መሠረታዊ የሚባሉ መስፈርቶችን ካልተሟሉ ቋሚ ፍቃድ አይሰጥም።

የዓለም ባንክና የዓለም ጤና ድርጅት ባጠኑት ጥናት ኢትዮጵያ ካሏት ዜጎች ውስጥ 17 በመቶ አካል ጉዳተኛ እንደሆነ መገለጹ የሚታወስ ነው።

# የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ሲቢኢ ኑር ተቀማጭ ገንዘብ ከ100 ቢሊዮን ብር በላይ ደረሰ

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዲስ አበባ፡-የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ከወለድ ነጻ የባንክ አገልግሎት የሲቢኢ ኑር የተቀማጭ ገንዘብ 100 ቢሊዮን ብር መሻገሩን አስታወቀ። ባንኩ ከወለድ ነፃ የባንክ አገልግሎት መስጠት የጀመረበትን 10ኛ ዓመት በማክበር ላይ ነው።

ባንኩ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ትናንት በላከው ጋዜጣዊ መግለጫ እንዳስታወቀው፤ በሲቢኢ ኑር በኩል የሰበሰበው የተቀማጭ ገንዘብ 100 ቢሊዮን ብር ተሻግሯል።

ከወለድ ነፃ የባንክ አገልግሎት በመስጠት ፈር ቀዳጅ መሆኑን የጠቀሰው ባንኩ፤ በባንክ ኢንዱስትሪ ታሪክ በአጭር ጊዜ 100 ቢሊዮን ተቀማጭ መሰብሰብ የቻለ ባንክ ስለመሆኑም ነው የገለጸው።

የሀገር የኢኮኖሚ እድገትና የዜጎች ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የባንክ አገልግሎት ወሳኝ ነው  ያለው ባንኩ በመግለጫው፤ ከዚህ አንጻር ከወለድ ነጻ የባንክ አገልግሎት የሚጫወተው ሚና ከፍተኛ እንደሆነ አስታውቋል።

ባንኩ ከወለድ ነፃ የባንክ አገልግሎት በሰጠባቸው ባለፉት 10 ዓመታት፤ ከ40 በላይ በሚሆኑ የወዲዓህ መርህ መሠረት ያደረጉ የአደራና የተንቀሳቃሽ እንዲሁም ትርፍ አጋሪ በሆነው በሙዳራባህ መርህን መሠረት ያደረጉ የተቀማጭ ሒሳቦችን መሠረት በማድረግ ስድስት ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ደንበኞችን በማፍራት ከ100 ቢሊዮን ተቀማጭ ገንዘብ በላይ ማሰባሰብ መቻሉን ጠቁሟል።

በአሁኑ ጊዜ የሲቢኢ ኑር የባንክ አገልግሎት በአንድ ሺህ 934 ቅርንጫፎች እየተሰጠ  እንደሚገኝ የጠቆመው መግለጫው፤ በዚህም 153 ሙሉ በሙሉ አገልግሎቱን ብቻ የሚሰጡ ቅርንጫፎች ስለመሆናቸውም ከባንኩ ተገኘው መረጃ ያመለክታል።

በተለይ ባለፉት አምስት ዓመታት ባንኩ እየሰጠ ላለው ከወለድ ነፃ የባንክ አገልግሎቱ የተለየ ትኩረት በመስጠት ያከናወናቸው ተግባራት አሁን ላይ ለሚታዩት ለውጦች ከፍተኛ አስተዋጽኦ ማበርከቱ  ተገልጿል።

አገልግሎቱ በኢትዮጵያ  ከተጀመረ ጀምሮ ከወለድ ነጻ አገልግሎት ባለመኖሩ ምክንያት ከባንክ የራቀውን ህብረተሰብ ወደ ባንክ በማምጣት ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል ያለው ባንኩ በመግለጫው፤ የተሟላ ከወለድ ነጻ የባንክ አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል።

መንግሥት በፋይናንስ ዘርፉ ላይ ለወሰዳቸው ጠንካራ የማሻሻያ ርምጃዎችን ተከትሎ ባንኩ ያደረጋቸው የመዋቅር ፣ የአሠራርና የአገልግሎት አሰጣጥ ለውጦች ሰፊ የህብረተሰብ ክፍሎች የአገልግሎቱ ተጠቃሚ እንዲሆኑ አስችሏል።

ከወለድ ነጻ የባንክ አገልግሎት ለሚፈልጉ የህብረተሰብ ክፍሎች የተሟላ አገልግሎት ለመስጠትና አሠራሩን ለማሻሻል ቀላልና ቀልጣፋ የአሠራር ሥርዓት ማበጀቱን ባንኩ በመግለጫው አመልክቷል።

# በኤጀንሲው የሚሰጡ አገልግሎቶች ከሌብነት የራቁ እንዲሆኑ ጠንካራ ቁጥጥር እየተደረገ ነው

**ማህሌት ብዙነህ**

አዲስ አበባ፡- በከተማዋ  የሚሰጡ  አገልግሎቶች ከሌብነት የራቁ እንዲሆኑ ጠንካራ ቁጥጥር እየተደረገ መሆኑ የሲቪል ምዝገባ እና የነዋሪነት አገልግሎት ኤጀንሲ አስታወቀ።

የሲቪል ምዝገባ እና የነዋሪነት አገልግሎት ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተር አቶ ዮናስ ዓለማየሁ በስድስት ወራት ውስጥ  በሕገ-ወጥነት እና ተጠያቂነት ላይ በተሠሩ ሥራዎች ዙሪያ ትናንት በሰጡት መግለጫ  እንዳሉት፤ ኤጀንሲው በተቋም ግንባታ ሥራ ትልቅ ትኩረት የሚሰጠው የተጠያቂነት ጉዳይ ነው። ከዚህ አኳያም በኤጀንሲው የሚሰጡ አገልግሎቶች ከሌብነት የራቁ እንዲሆኑ ጠንካራ ቁጥጥር እየተደረገ ነው።

ኤጀንሲው ስር በሚገኘው  የሥነ ምግባር እና ጸረ ሙስና ዳይሬክቶሬት በተሠራው የቁጥጥር ሥራም ባለፉት ስድስት ወራት 83 ባለሙያዎችን እና ተገልጋዮችን ከቀላል ዲሲፕሊን እስከ ወንጀል ተጠያቂ መደረጋቸውን አስታውቀዋል።

ከመደበኛ የአሠራር ጥሰት ጀምሮ በገንዘብ አገልግሎትን መሸጥ ወይም ጉቦ እስከመቀበል ባለው አጠቃላይ ሁኔታ 47 ባለሙያዎች ተጠያቂ ማድረግ መቻሉን ገልጸው፤ 34 ባለሙያዎች ከባድ እና ቀላል ዲሲፕሊን ርምጃ የተወሰደባቸው ሲሆን 9 ባለሙያዎች በወንጀል ተከሰዋል ብለዋል።

በተጨማሪም 36 ሃሰተኛ ሰነድ ይዘው የተገኙ ተገልጋዮች በሕግ ቁጥጥር ስር እንዲውሉ የተደረገ መሆኑን አስታውቀው፤ ከእነዚህም  4ቱ በወረዳ ፣ 34ቱ በኤጀንሲው ዋና መሥሪያ ቤት መሆናቸውን ገልፀዋል። ከዚህም ውስጥ ሁለቱ ፍርድ ተሰጥቷቸዋል ብለዋል።

በዚህ ቁጥጥር ሥራም በአገልግሎት ሌብነት ሊተላለፍ የነበረ ከ150 ሺህ እስከ 200 ሺህ የሚሆን ገንዘብ ማዳን መቻሉን አቶ ዮናስ ገልጸዋል።



በተጨማሪም በ2015 በተቋሙ የተሠራጩ ካርዶችና ዲጂታል መታወቂያ ጨምሮ  ኦዲት ለማድረግ የህትመት ዝግጅት ስርጭትና ቁጥጥር ክፍል መደራጀቱን ጠቁመው፤ በዋና መሥሪያ ቤቱን ጨምሮ 11 ክፍለ ከተማ እና 22 የወረዳ ጽህፈት ቤቶች  ላይ የኦዲት ሥራ መሠራቱን ተናግረዋል።

አቶ ዮናስ እንደገለጹት፤ ከኦዲት ግኝቱ አንጻር ከባለሙያ እስከ አመራር ከቀላል እስከ ከባድ ዲሲፕሊን ድረስ ተጠያቂ የማድረግ ሥራ ተሠርቷል። በዚህም 41 ባለሙያዎችን  የዲሲፕሊን ርምጃ የተወሰዳባቸው ሲሆን 12 ባለሙያዎችን ደግሞ በወንጀል ተጠያቂ እንዲሆኑ ተደርጓል።

ህብረተሰቡ እጅግ አስጊ እየሆነ ከመጣው ሃሰተኛ ሰነድ ከሚያዘጋጁ ሕገ-ወጦች እና አገልግሎትን በገንዘብ ለማግኘት ከመሞከር እራሱን እንዲጠብቅ አቶ ዮናስ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።

ዜና



ፎቶ ሃዲስ አብርሃ

ወይዘሮ አስካል ለማ

## የወደብ ስምምነቱ የሴቶችን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ተጠቃሚነት ለማሳደግ የሚያግዝ ነው

**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያና ሶማሊ ላንድ መካከል የተፈረመው የባህር በር ስምምነት የሴቶችን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ተጠቃሚነት ለማሳደግ የሚያግዝ መሆኑን የኢትዮጵያ ሴቶች ፌዴሬሽን አስታወቀ።

በኢትዮጵያና ሶማሊ ላንድ መካከል የተፈረመውን የመግባቢያ ሰነድ አስመልክቶ ትናንትና መግለጫ የሰጡት የፌዴሬሽኑ ተወካይ ፕሬዚዳንት ወይዘሮ አስካለ ለማ እንደገለጹት፤ ስምምነቱ ሴቶች የአካባቢያቸውን የተፈጥሮ ሀብት ተጠቅመው ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ አቅማቸውን እንዲያጎለብቱ የሚያግዝ ነው።

ኢትዮጵያ ከሶማሊላንድ ወደብ ማግኘትዋ ለኢትዮጵያ ኢኮኖሚ እድገትና ብልጽግና ከፍተኛ አስተዋጽኦ ይኖረዋል ያሉት ወይዘሮ አስካለ፤ የሎጂስቲክስ አቅምን ለማሳደግ፣ አዳዲስ የንግድ እድሎችንና የገበያ መዳረሻዎችን በመፍጠር ሴቶችን ተጠቃሚ ያደርጋል ብለዋል።

የወደብ መሠረተ ልማት መገንባት የሥራ እድሎች ለመፍጠር የሚረዳ ሲሆን፤ ሴቶች በሥራ እድሉ ተጠቃሚ ሆነው አዳዲስ ክህሎቶችንና ሙያዊ እውቀቶችን እንዲያገኙ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረክታል ሲሉ ተናግረዋል፡፡

ስምምነቱ ኢትዮጵያ ለወደብ ኪራይ እያወጣች ያለውን ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪን በመቀነስ ለማህበራዊ ልማት እንድታውል፣ የትምህርት እና የጤና አገልግሎት ተደራሽነትን ለማሻሻል ያግዛል ያሉት ወይዘሮ አስካለ፤ በዚህም በከተማም ሆነ በገጠር ላሉ ሴቶች የጤና፣ የትምህርና የልማት አገልግሎቶች ተጠቃሚነት ለማሳደግ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረክታል ብለዋል፡፡

የወደብ መሠረተ ልማት ማግኘት የወጪና ገቢ ንግድ ሂደቶችን ከማሳለጡም በተጨማሪ ወጪን በመቀነስ በዓለም አቀፍ ደረጃ የኢትዮጵያን ምርቶች ተወዳዳሪነት ለማሳደግ እንደሚረዳ ተናግረዋል፡፡

ስምምነቱ ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነትን ከማሳደጉም ባለፈ የሕዝብ ለሕዝብ ዲፕሎማሲና የባህል ልውውጥን በማሳደግ መግባባትና ስምምነትን ለማጎልበት የሚጠቅም መሆኑን አመልክተዋል።

ኢትዮጵያ ከሶማሊ ላንድ ጋር ወደብን አስመልክቶ ያደረገችው ስምምነት የጋራ ተጠቃሚነትን ብቻ ታሳቢ ያደረገ እንጂ የማንንም ብሔራዊ ጥቅምና ሉዓላዊነት የሚጻረር አለመሆኑንም ጠቁመዋል።

በስምምነቱ ላይ የሚነሱ ጥርጣሬዎችን ለመቅረፍና ትክክለኛ ግንዛቤ እንዲፈጠር ለማድረግ ፌዴሬሽኑ የድርሻውን እንደሚወጣ ገልጸዋል፡፡

የወደብ ስምምነቱን ስኬታማ ለማድረግ ሁሉም ዜጋ ከመንግሥት ጋር በትብብር ኃላፊነቱን ሊወጣ እንደሚገባ መልዕክት አስተላልፈዋል።

# “የዲፕሎማሲ ሳምንቱ የአዲስ አበባን የዲፕሎማሲ ማዕከልነት ለማጽናት ትልቅ አቅም ይሆናል”

*- አምባሳደር መለስ አለም (ዶ/ር)*
*የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቃል አቀባይ*

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- ከዛሬ ጀምሮ የሚካሄደው የዲፕሎማሲ ሳምንት የአዲስ አበባን የዲፕሎማሲ ማዕከልነት ለማጽናት ትልቅ አቅም እንደሚሆን የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አስታወቀ።

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቃል አቀባይ አምባሳደር መለስ አለም (ዶ/ር) የዲፕሎማሲ ሳምንትን አስመልክቶ ለጋዜጠኞች መግለጫ ሰጥተዋል።

የሚኒስቴሩ ቃል አቀባይ አምባሳደር መለስ አለም (ዶ/ር) እንደገለጹት፤ የሀገራችን የብሔራዊ ጥቅም እንዲከበር በዲፕሎማሲው መስክ ሁሉም የህብረተሰብ ክፍል ተሳትፎ ማረጋገጥ ይገባል።

ይህን ለማድረግ እንዲቻልም የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር «ዲፕሎማሲያችን ለብሔራዊ ጥቅማችን፤ ከአፍሪካ መዲና እስከ ዓለም መድረክ» በሚል ርዕስ ያዘጋጀው የዲፕሎማሲ ሳምንት ዛሬ በይፋ ይከፈታል።

አምባሳደር መለስ እንዳብራሩት፤ ከዛሬ ጀምሮ የሚካሄደው የዲፕሎማሲ ሳምንት የአዲስ አበባን የዲፕሎማሲ ማዕከልነት ለማጽናት ትልቅ አቅም ይሆናል።

እንደ አምባሳደር መለስ ገለጻ፤ የኢትዮጵያ ዲፕሎማሲ የቆየና በመንግሥት ተሳትፎ ብቻ ሳይሆን በእያንዳንዱ ዜጋ ጥረትና ጽናት የጸና ነው። ዜጎችና ተቋማት የሀገራቸው አምባሳደሮች ናቸው። ለአብነትም አትሌቶችን፣ የኢትዮጵያ አየር መንገድና ሌሎችን ተቋማትን መግለጽ ይቻላል። ሁሉን አቀፍ የዲፕሎማሲ እንቅስቃሴ እንዲጀመር የተጀመረው የዲፕሎማሲ ሳምንት ትልቅ ትርጉም አለው። ብሔራዊ ጥቅምን ለማረጋገጥ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር እየተለወጠ ባለ ዓለም ውስጥ የተለወጠ አሠራር እንዲኖረው እየሠራ ነው።

በተለይ የአዲስ አበባን የዲፕሎማሲ ማዕከልነት ከማጽናት አንጻር ዛሬ የሚከፈተው የዲፕሎማሲ ሳምንት ትልቅ ትርጉም አለው ያሉት አምባሳደር መለስ፤ አዲስ አበባ በዓለማችን ውስጥ ካሉ ሦስት ዋና ዋና የዲፕሎማሲ ማዕከሎች ውስጥ አንደኛዋ መሆኗን አምባሳደር መለስ ገልጸዋል።

አዲስ አበባ የዲፕሎማሲ ማዕከልነት በብዙ የዲፕሎማሲ ውጣ ውረድ የተጠበቀ ነው ያሉት ቃል አቀባዩ፤ አንዳንድ አካላት ይህ የዲፕሎማሲ ማዕከልነት እንዳይኖር ብዙ ሠርተዋል። የአዲስ አበባ የዲፕሎማሲ ማዕከልት በምኞት ማጽናት አይቻልም። የዓለም አቀፍ ተቋሞችን መቀመጫነት የማጽናት ጉዳይ ፍላጎት ብቻ ሳይሆን ጠንካራ ሥራ ይጠይቃል። ለዚህም የሁሉም የህብረተሰብ ክፍል ተሳትፎ ወሳኝ መሆኑን ገልጸዋል።

የዲፕሎማሲ ሙያ አንድ ሀገር ከሌላ ሀገር ጋር የሚያደርገው ግንኙነት ነው ያሉት አምባሳደሩ፤ የዲፕሎማሲ ሳምንቱ ኢትዮጵያም ከሀገራትና ከተቋማት ጋር የምታደርገውን ግንኙነት መቀመጫቸውን በአዲስ አበባ ላደረጉ ዲፕሎማቶች ለማሳየት እድልን ይፈጥራል፤ ግንኙነቶችንም እንደ አዲስ ለማጠናከር እድል የሚሰጥ ይሆናል ብለዋል።

በሀገሮች መካከል የሚደረግ የዲፕሎማሲ ግንኙነት የባለብዙ ወገን ወይም የሁለትዮሽ መሆኑን በመጥቀስም የሀገራችን ብሔራዊ ጥቅም በሚገባ እንዲከበር ለማድረግ የሁሉንም ህብረተሰብ አቅምና ችሎታ ሁለንተናዊ በሆነ መልኩ መጠቀም ያስፈልጋል ሲሉ ተናግረዋል።

በተለይ የዲፕሎማሲ ሳምንቱ ኢትዮጵያውያን ብቻ ሳይሆኑ መቀመጫቸውን አዲስ አበባ ያደረጉ



ኤምባሲዎች፣ የዓለም አቀፍ ድርጅት ተወካዮችና የመንግሥታዊ ድርጅት ተወካዮች ይህን አጋጣሚ ተጠቅመው የዲፕሎማሲ ሳምንቱ አንደኛና ዋነኛው አካል የሆነውን አውደ ርዕይ ላይ ይሳተፋሉ ተብሎ ይጠበቃል ብለዋል።

በተያያዘ ዜና በያዝነው ሳምንት ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንንና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዴኤታ አምባሳደር ምስጋኑ አርጋ ሰፊ የዲፕሎማሲ እንቅስቃሴዎችን ማከናወናቸውን የገለጹት አምባሳደር ምስጋኑ፤ ኢትዮጵያ ከተለያዩ ሀገሮች ጋር ያላት ግንኙነት የበለጠ እንዲጠናከር አበክራ እየሠራች እንደምትገኝም ገልጸዋል።

# የማረሚያ ቤት የተሀድሶ ልማት ሥራዎች ውጤት እያስገኙ ነው

**ዮርዳኖስ ፍቅሩ**

አዲስ አበባ፡- በማረሚያ ቤት እየተከናወኑ የሚገኙ የተሃድሶ ልማት ዘርፍ ሥራዎች ውጤት እያስገኙ መሆናቸውን የፌዴራል ማረሚያ ቤት ኮሚሽን አስታወቀ፡፡

የኮሚሽኑ የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ አቶ ገረመው አያሌው ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳስታወቁት፣ ኮሚሽኑ በስሩ በሚገኙ ማረሚያ ቤቶች በተሃድሶ ልማት ዘርፍ እያከናወናቸው በሚገኙ የትምህርትና ሥልጠና ሥራዎች የታራሚዎችን አመለካከት መቀየርና የሙያ ባለቤት ማድረግ ችለዋል፡፡

ታራሚዎች የቀለም ትምህርትን መሠረት ባደረገ መልኩ እያገኙ ባለው የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና የእንጨት፣ የብረታ ብረት፣ የሽመና፣ የኤሌክትሪክ፣ የቧንቧ፣ የጨርቃ ጨርቅና የሌዘር ሙያን እየተካኑ እንደሚገኙ ኃላፊው ተናግረዋል፡፡

ሥልጠናው ታራሚዎች ሰርቼ መለወጥ እችላለው የሚለውን አመለካከት እንዲላበሱ ከማስቻሉም ባለፈ ከማረሚያ ቤት በሚወጡበት ጊዜ በሠለጠኑበት ሙያ ተሠማርተው ራሳቸውን በኢኮኖሚ እንዲችሉና፣ ቤተሰባቸውንና ሀገራቸውን እንዲጠቅሙ ያስችላቸዋል ያሉት አቶ ገረመው፤ ለውጡ በተግባርም እየታየ ይገኛል ብለዋል፡፡



ሁሉም ታራሚዎች የቴክኒክና ሙያ ፍላጎት ላይኖራቸው እንደሚችል ያነሱት የቴክኒክና ሙያ ፍላጎቱ ለሌላቸውና ከአርሶና አርብቶ አደር አካባቢ ለመጡ ታራሚዎችም በእንስሳት እርባታ በከተማ ግብርና፣ በአነስተኛ መሬት ጓሮ አትክልትን እንዴት ማልማት እንደሚቻልና በሰብል ልማት ላይ በተግባር የታገዘ ሥልጠና እየተሰጣቸው እንደሚገኝም ጠቁመዋል፡፡

በቴክኒክ ሙያና በግብርና ሙያ ዘርፍ የታራሚዎች የሥራ ውጤቶች በማረሚያ ቤቶች አካባቢ ያለው ማኅበረሰብ እንዲጠቀም በመሸጫ ሱቆች አማካኝነት ለሽያጭ እንደሚቀርብና ታራሚዎቹም ተጠቃሚ እንደሆኑ የጠቆሙት አቶ ገረመው፤ ታራሚዎች በማኅበራት ተደራጅተው ከሚያገኙት ገቢ 80 መቶ እንዲቆጥቡ እንደሚደረግም አመልክተዋል፡፡

ቀሪውን 20 መቶ ደግሞ የማረሚያ ቤቱን አሠራር ተከትለው ለራሳቸው እንዲጠቀሙና ቤተሰባቸውንም በማረሚያ ቤት ሆነው ማገዝ የሚችሉበት ሁኔታ እንደተመቻቸላቸውም ኃላፊው ተናግረዋል፡፡

ታራሚዎች የንባብ ባህላቸውን እንዲያሳድጉና በመጻሕፍትም እንዲታረሙ ለማስቻል ቤተ መጻሕፍትን በአግባቡ የማደራጀት ሥራዎች እተሠሩ እንዳሉ የጠቆሙት አቶ ገረመው፤ ከፍተኛ የትምርት ተቋማትና ሌሎችም ባለድርሻ አካላት ሥራውን በመደገፍ ረገድ ከኮሚሽኑ ጋር በትብብር እየሠሩ እንደሚገኙም ጠቁመዋል፡፡

ባለፈው ዓመት ኮሚሽኑ ከሁሉም ማረሚያ ቤቶች 47 ተማሪዎችን ለዩኒቨርሲቲ መግቢያ ፈተና ማስቀመጡን ያስታወሱት አቶ ገረመው፣ ከአንዳንድ ትምህርት ቤቶች በተሻለ ሁኔታ ብዙም የተመቻቸ ሁኔታ በሌለበት ኮሚሽኑ ካስፈተናቸው ተማሪዎች መካከል 4ቱን ወደ ዩኒቨርሲቲ ማሳለፍ መቻሉንና ብዙዎቹ ማካካሻ ትምህርትና ድጋሚ ፈተና እንዲወስዱ ማስቻሉን ተናግረዋል፡፡

ይህም አንዱ የተሃድሶ ልማት ዘርፍ የትምህርትና ሥልጠናው ውጤታማነት ማሳያ ነውም ብለዋል፡፡ አያይዘውም፣ ኮሚሽኑ በዘርፉ ከተለያዩ አካላት በጎ ግብረ ምላሽ እየተሰጠው እንደሚገኝም ኃላፊው አንስተዋል፡፡

ኮሚሽኑ በስሩ በሚገኙ የድሬዳዋ ማረሚያና ማረፊያ ማዕከል፣ ሸዋሮቢት ማረሚያ ማዕከል፣ ዝዋይ ማረሚያ ማዕከል፣ ቃሊቲ ማረሚያ ማዕከልና ቃሊቲ የሴቶች ማረሚያና ማረፊያ ማዕከላት ታራሚዎች የእርም ጊዜያቸውን አጠናቀው ወደ ህብረተሰቡ ሲቀላቀሉ ለራሳቸው፣ ለቤተሰባቸውና፣ ለሀገራቸው ጠቃሚ ዜጋ መሆን የሚያስችላቸውን የተሃድሶ ልማት ሥራዎችን አጠናክሮ እንደደሚቀጥል ኃላፊው አመልክተዋል፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## ሁላችንም የኢትዮጵያ አምባሳደር፣ ስለ ኢትዮጵያም ዲፕሎማት እንሁን!

ሀገር በሕዝቦቿ ተግባር ልክ ትገለጻለች፡፡ መልካም ዜጎች መልካም ሀገርን ይገነባሉ፤ ካልሆነው የሀገር መገለጫው ከዚህ በተቃራኒ ነው፡፡ እኛ ኢትዮጵያውያንም በየዘመኑ ትውልዶች እሳቤና ተግባር ልክ ኢትዮጵያን ሠርተናል፡፡ በዓለም የሚታየው ገጽና ስሟንም ፈጥረናል፡፡

ኢትዮጵያ የሥልጣኔ ቀደምትነቷም፤ የነጻነት አርነቷም፤ የጥበብና ባህል ማዕከልነቷም፤ የድህነትና ጦርነት ታሪኳም፤ የረሃብና ስደት ገጿም መነሻና መሥሪያ ማዕከሏ እኛው ዜጎቿ ነን፡፡ ኢትዮጵያን ማዕከል አድርገን በሠራን ልክ፤ ስለ ኢትዮጵያ ተጨንቀን በተንቀሳቀስን መጠን የኢትዮጵያን ገጽ እናስውባለን፡፡ ካልሆነ ግን የኢትዮጵያን ልክ እናጠይማለን፡፡ የልዕልናዋንና የጉስቁልናዋም ገጽ የመሳሉ እውነትም በዚሁ አግባብ የተገለጠ ነው፡፡

ይሄን የኢትዮጵያን ገጽ የመግለጥ፤ ልዕልናዋን የማረጋገጥ መንገድ ደግሞ የተለያየ ፈርጅ አለው፡፡ ሰላሟን በማጽናት፤ ልማቷን በማሳለጥ፤ የዴሞክራሲ ግንባታ መንገዷን ቀና በማድረግ፤ የተረጋጋ የፖለቲካ ምህዳር በመፍጠር፤ ብቁ (በእውቀትም በጤናም) የሰው ኃይልን በመፍጠር ሂደት ውስጥ የሚገለጽ የእያንዳንዱ ዜጋ ተግባር ድምር ውጤትን ይፈልጋል፡፡

ከዚህ የውስጥ የቤት ሥራዎች በተጓዳኝ ግን ኢትዮጵያን በሠራናት ልክ ለውጪው ዓለምና ማኅበረሰብ የማሳወቅ፤ ከውጪው ዓለም ጋር የሚኖራትን ግንኙነትና ትብብር ቀና የማድረግ፤ ከውጪው ዓለም ጋር በሚኖራት ግንኙነት ተጠቃሚነቷን የማረጋገጥ፤ ከፍ ያለ የአምባሳደርነት ተግባር ከዜጎች ይጠበቃል፡፡ ይሄ ደግሞ ከኢትዮጵያ ሉዓላዊ ግዛትና ድንበር ባሻገር የመሥራት የዲፕሎማትነት ልዕልና መጎናጸፍን ይጠይቃል፡፡

አምባሳደርነት፣ የሀገርን ስምና ገጽ ይዞ መንቀሳቀስ፤ በዛ ልክ ራስን ቀርጾ መትጋትን መጎናጸፊያ ማዕረግ ነው፡፡ ይሄን ማዕረግ በልኩ መጠቀም፤ ኢትዮጵያን በሚገልጸው ስዕል ልክ መጠቀም ይገባል፡፡ ይሄን ለማድረግ ግን የግድ የአምባሳደርነት ማዕረግን ከመንግሥት አካል ማግኘት የግድ አይልም፡፡ ምክንያቱም አምባሳደርነት ሀገርን የመውደድና ሀገርን የማክበር የውስጥ ስሜት የሚፈጥረው ማንነት ነው፡፡

ይሄ ማንነት ደግሞ ለሀገር ጥቅም የመቆምን፣ ስለ ሀገር ገጽታ ማንንም ሳይጠብቁ የራስን ተግባር መወጣትን በጥቅሉ ስለ ኢትዮጵያ በውጪው ዓለም መልካም ገጽ መሳልን እውነት ለመግለጥ የሚያስችል የዲፕሎማሲ ሥራ የመፈጸም የኢትዮጵያ አምባሳደር መሆንን ያጎናጽፋል፡፡

ዲፕሎማትነት ደግሞ በአንድ ሁኔታና ሁነት ውስጥ ተቀንብቦ የሚገለጽ አይደለም፡፡ ዲፕሎማትነት ሀገርን መስሎም፣ ሆኖም መገለጥን የሚሻ ነው፡፡ ሀገርን መምሰል የቻለ ዜጋ፣ ሀገሩን የመግለጥ አቅም አለው፡፡ አንድ ዜጋ ደግሞ ሀገሩን በእርሱነቱ ውስጥና ገጽ መግለጥ ከቻለ የሀገሩ ጥቅም አስከባሪ ዲፕሎማት ሆነ ማለት ነው፡፡

ዛሬ ኢትዮጵያ በብዙ መልኩ የሚገልጧት ዲፕሎማቶች ትሻለች፡፡ በብዙ ፈተና፣ በብዙ ችግር፣ በብዙ ውጣ ውረድ ውስጥ እያለፈች ባለችበት በዚህ የለውጥ ሂደት ውስጥ ከእነዚህ ችግሮች ባሻገር የሚመለከታትንና ለብልጽግናዋ የሚያግዛትን ዓለም ለመፍጠር የሚያስችል ሥራን የሚከውን ትውልድ ትፈልጋለች፡፡

ኢትዮጵያ በጤናው፣ በቱሪዝሙ፤ በኢኮኖሚው እና በጂኦ ፖለቲካው እንዲሁም በቴክኖሎጂው ዘርፍ፤ ብሎም በሳይንስና ሌሎችም መስኮች ከፍ ያለ ገጿን የሚገልጡላት አያሌ ዲፕሎማቶችን ትናፍቃለች፡፡ እነዚህ ዲፕሎማቶች ደግሞ የትናንቶቻቸውን (ቀደምቶቻቸውን) የሚመስሉ መሆን አለባቸው፡፡

ቀደምት ኢትዮጵያ ዲፕሎማቶች ኢትዮጵያን ከፍ አድርገው የሳሉ፤ የኢትዮጵያን ገጽ በግርማ ሞገስ የገለጡ፤ በዲፕሎማሲው ጎራ የኢትዮጵያን ተጽዕኖ ፈጣሪነትና ቅቡልነት ያረጋገጡ ናቸው፡፡ አዲስ አበባን ሦስተኛዋ የዓለም ዲፕሎማሲ መዲና ማድረግ የቻለን ሥራ የከወኑም ናቸው፡፡

የዛሬው ትውልድም ይሄንን እውነት ተገንዝቦ በቀደምቶቹ መንገድ መጓዝን፤ ከዚህም በላቀ መልኩ ዘመኑን የዋጀ አቅም ፈጥሮ መራመድን መላበስ አለበት፡፡ ኢትዮጵያን የሚወክል የአምባሳደርነት ክብርን በላዩ ሊደርብ፤ ኢትዮጵያን የሚገልጽና በዓለምአቀፍ መድረኮች ጥቅሟን የሚያስጠብቅ የዲፕሎማትነት ፍላጎትንና ግብርን ሊጎናጸፍ ያስፈልጋል፡፡

ምክንያቱም ኢትዮጵያ በጥቂት መንግሥት በሰየማቸው አምባሳደሮችና ዲፕሎማቶች ተግባር ብቻ በከፍታዋ ልክ ልትገለጽ አትችልም፡፡ እነዚህ አምባሳደሮችና ዲፕሎማቶች መሠረታዊ የሚባሉ ጉዳዮችን ማስፈጸምና መፈጸም ቢችሉ እንኳን፤ ኢትዮጵያን በልኳ እና በቱባ ማንነቷ ልክ አመላክተው ጥቅሟን ያስጠብቃሉ ብሎ ማሰብ የዋህነት ይሆናል፡፡

የታሪክ ሂደት፣ የዲፕሎማሲው እውነት የሚነግረን ይሄንኑ ነው፡፡ ኢትዮጵያ ከንግሥተ ሳባ የዲፕሎማሲያዊ ጉዞ ጥንስስ ጀምሮ እስካሁኑ የዲጂታል ዲፕሎማሲ ሁነት የነበራት ሂደትም፤ አምባሳደሮቿም፣ ዲፕሎማቶቿም በዜጎቿ ከፍ ያለ ተግባር ታግዘው የተጓዙና ውጤት ያመጡ ናቸው

የሩቁም እውነት፤ የቅርቡም ሁነት ይሄንኑ የዜጎችን የአምባሳደርነት እና የዲፕሎማትነት መንገድ ከገለጠ፤ የዛሬው እና የነገው የዲፕሎማሲ ጉዞም በዚሁ አግባብ ሊመራ እንደሚገባው መገንዘብ ይቻላል፡፡ የኢትዮጵያን ፖለቲካዊም፣ ኢኮኖሚያዊም ሆነ ሌሎች ከሁለትዮሽና ከባለብዙ ወገን ትብብር መስኮች የምታገኛቸውን ጥቅሞች ማስጠበቅ የሚቻለውም ይሄንኑ ማድረግ ሲቻል ነው፡፡

እነሆ ዛሬ በሳይንስ ሙዚየም “ዲፕሎማሲያችን ለብሔራዊ ጥቅማችን!” በሚል መሪ ሃሳብ የተከፈተው የኢትዮጵያ የዲፕሎማሲ ሳምንት አውደ ርዕይም ይሄንኑ በዓለም መድረክ የኢትዮጵያን ጥቅም ማስጠበቅ የሚችል ትውልድን የመፍጠር መንገድ ነው፡፡ አውደ ርዕዩም ዜጎች ከትናንቱ መንገድ የሚማሩበት፤ ከዛሬው ሁነት ልምድ የሚቀስሙበት፤ የነገውን መንገድ የሚመለከቱበት ሲሆን፤ እኛም ይሄንኑ በመገንዘብ የኢትዮጵያ አምባሳደሮች፣ ስለ ኢትዮጵያም ዲፕሎማቶች የምንሆንበትን የዜግነት ከፍታ ልንጨብጥ የተገባ ነው!


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፦ epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፦ 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፦ ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ነገዎቻችንን ብሩህ ለማድረግ እንመካከር !

**ሙሉጌታ ብርሃኑ**

ዛሬ ላይ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ምን ትሻለህ ተብሎ ቢጠየቅ፤የሀገሬን ሰላም ከማለት ውጪ ሌላ ምላሽ ያለው አይመስለኝም፡፡ ”ከሌለህ የለህም” የሚለው አባባልም፤ከምንም በላይ ሰላምን ይገልጸዋል፡፡ እዚህች ምድር ላይ ምንም ነገር ባይኖረን ሰላምና ጤና ካለን የቱንም የምንፈልገውን ነገር ለማድረግም ሆነ ለማግኘት እንችላለን፡፡እኚህ ከሌሉ ግን የሌለንን ነገር ለማግኘት ይቅርና ያለንንም ነገር መጨበጥ ሊያቅትን ይችላል፡፡

ዝንጀሮ እንኳን “በመጀመሪያ የመቀመጫዬን” ማለቷ ነገሩ ቢገባት ነው፡፡ ከሁሉም ጉዳዮቻችን በላይ ለነገ ብለን ማሳደር የሌለብን የመቀመጫችንን እና የሰላማችንን ጉዳይ ነው፡፡ የሰላማችንን ጉዳይ ለነገ ብለን በይደር ካቆየነው መሽቶ በነጋ ቁጥር ነገን የማየት ህልማችን አስተማማኝ አይሆንም፡፡

እንደ ሀገር ዱካው የጠፋብንን ሰላም ለማግኘት፤የመንግሥትና የሕዝብ ጥምረት የሆነ ሀገራዊ የምክክር ኮሚሽን ተቋቁሞ ችግሮቻችንን በውይይትና ተቀራርቦ በመነጋገር ፈትተን ወደ ቀደመው ሰላማችን እንድንመለስ የሚያደርጉ ሥራዎችን እየሠራ ነው፡፡ ነገር ግን በተግባር ስንቶቻችን ተቀብለን እየሠራንበት ይሆን? ሰላማችን እንዲመለስ ግላዊም ሆነ ቡድናዊ አስተዋጿችንን እንዴት ለማበርከት ተዘጋጅተን ይሆን? ጉዳዩን ጀመርነው እንጂ ገና አላጠናቀቅነውምና ሁላችንም ወደ ሰላም ያደርሳሉ በተባሉ መንገዶች ላይ ለመራመድ እንዘጋጅ፡፡

ከጠመንጃ አፈሙዝ የምናገኘው የጥይት ባሩድና ሞት ብቻ ነው፡፡ እስከዛሬም ዓለም ባላት ታሪክ፤በጠመንጃ አፈሙዝ የጸና ሰላም አይተንም ሆነ ሰምተን አናውቅም፡፡ ሳይንስ በደረሰበት ጥበብም እሳት በእሳት ጠፍቶ አያውቅም፡፡ ታዲያ በኛ የሚጀምር ከመሰለን ተሳስተናል፡፡

ጠመንጃ አንግበን ሰላምን ፍለጋ ብንኳትን ከቶም አናገኘውም ፤ እንዲህ አይነቱ የአዳኝና የታዳኝ ጨዋታ ምናልባት ውጤት ያመጣል ቢባል እንኳን ዘለቄታ አይኖረውም፡፡ ዓለም ላይ የብዙ ሰዎችን እልቂት ያስከተሉና የንብረት ውድመት ያደረሱ በርካታ ጦርነቶች ተካሂደዋል፤ አብዛኞዎቹ የተቋጩት በንግግር ነው፡፡ እኛስ…ካለፉት ምን እንማር? የትኛው መንገድ ይሻለናል? ስንል፤ያለን ብቸኛው አማራጭ፤ በሀገራዊ የምክክር ኮሚሽን የቀረበውን የሰላም ጥሪ እውን ማድረግ ነው። ይህ ሊያመልጠን የማይገባ ታሪካዊ አጋጣሚ ነው።፡

ሀሳቡ ከማንም ይምጣ ከማን ሕዝባዊ ቅርጽ እንዲኖረው በማድረግ መድኃኒት ማድረጉ የኛ ድርሻ ነው፡፡ በተቋሙ ላይ ሕዝባዊ አጀንዳዎችን በመጫን ሕዝባዊ ማድረጉ በእጃችን ነው፡፡ የምክክር ኮሚሽኑ የተቋቋመበት ሒደትም ሆነ ዓላማ፤እንደ መንግሥታዊ ተቋም አይደለም። ተቋሙም የሚያስረዳው ይህንኑ ነው፡፡ የምንፈልገው ሰላምና ሰላም ብቻ እስከሆነ ድረስ ለጉዳዩ ዕድል ሰጥተን ልንጠቀምበት ይገባል፡፡

ሀገራዊው ምክክሩ በቀጣዩ የጥር ወር ላይ እንደሚጀምር የተነገረ ቢሆንም ቀደም ሲል በነበሩት ጊዜያት ግን በክልሎችና ከተሞች፤የቅድመ ምክክር ሥራዎች ሲካሔዱ መሰንበታቸው የማይዘነጋ ነው። ከምክክሩ አስቀድሞ ሲካሔድ የነበረው የቅድመ ምክክር ሒደቱ፤ከምንም በላይ እጅግ ወሳኙ ምዕራፍ እንደመሆኑ የእያንዳንዱ ግለሰብ አሻራ ሊያርፈበት ይገባል፡፡

ኮሚሽኑ በተቻለው አቅም ሁሉ ይዞ የተነሳው ዓላማ ስኬታማ እንዲሆን ብርቱ ሥራዎችን እየሠራ ቢሆንም፤ ጉዳዩ ሀገራዊ እንደመሆኑ አንድም ዜጋ እንኳን ከዚህ ሊጎድል አይገባም። ሁሉም ዜጋ ከራሱ አልፎ የመጪው ትውልድ ብሩህ ነገዎች በኮሚሽኑ ውጤታማ ሥራ ላይ የተመሰረተ ስለመሆኑ ለአፍታም ቢሆን ሊዘነጋ አይገባም ።

ለዚህም ከሁሉም በላይ ጥያቄ አለኝ የሚለውም ሌላውም ዜጋ ስለሰላም አብዝቶ መሥራት ይጠበቅበታል። የምክክር ኮሚሽኑ የስኬት ሚዛን ከሚለካበት አንዱ መመዘኛ ይሄው እንደሆነ መገመት የሚከብድ አይደለም፡፡

ኮሚሽኑ ለውጥ አይመጣም በሚል አጉል የተዛባ አመለካከት እጃቸውን አጣምረው ከዳር የቆሙ አካላትም፤ ያለ ሙከራ ከሰማይ የሚዘንብ ለውጥ የለምና፤ ተስፋ አድርገው እጃቸውን የሰላም አሸንዳው ላይ መደቀን ይገባቸዋል፡፡ ምንም ሳንሠራ ሰላምን ከሰላም ቅርጫት ውስጥ ብንፈልግ እራሳችንን ማታለል ነው፡፡ ተስፋ አድርገን እንሳተፍ ፤ ድሮም እኮ አይሆንም ብዬ ነበር ለማለት እራሳችንን አናዘጋጅ ፡፡

ይህ ሳይሆን ቀርቶ በድፍን የፖለቲካ ኮብል ሕዝብና ሀገር ቢደማ፤ተጠያቂዎቹ ዛሬ ከሀገራዊ ምክክሩ የሸሸን እኛው እራሳችን መሆናችንን አንርሳ። የመጣንበት የፖለቲካ ድብብቆሽ ከድካም ውጪ ያተረፈልን ነገር እንደሌለ ካለፈው ታሪካችን ተምረናል።

የየትኛውም ሃይማኖት ተከታይ ልንሆን እንችላለን፤ ከየትኛውም ብሔር ልንወጣ እንችላለን፤ የራሳችን የሆነ የፖለቲካ አቋም ሊኖረንም ይችላል፤ እነዚህ ሁሉ ከሀገራዊ ምክክሩ ተሳታፊነት አያግዱንም። ሀገራዊ ምክክሩን ደግፎ ከዓላማው ጎን መቆም ማለት የመንግሥት ደጋፊ መሆን ማለት አይደለም፡፡ ሀገር በመንግሥት ሥር ብትሆንም፤ሀገር ማለት ግን መንግሥት ማለት አይደለም፡፡ ሀገር ከመንግሥት በላይ ነች።

ይህ ታላቅ ሀገራዊ ጉዳይ በስኬት እንዲጠናቀቀ ከኮሚሽኑ ምን ይጠበቃል? የመጀመሪያው ጉዳይ የምክክር ኮሚሽኑ ከሕዝብ ጋር ያለው ግንኙነት ጠንካራና ግልጽ መሆን አለበት፡፡ በምክክር ወቅት ሕዝብን ይወክላሉ ተብሎ የተመረጡ አካላት፤በትክክልም ሕዝብን የሚወክሉና ሕዝቡ እራሱ የመረጣቸው መሆን አለባቸው፡፡ ይህን አሳማኝ በሆነ መንገድ ማሳየት አለበት፡፡

አስቀድሞ ከሕዝቡ አሜንታን ያላገኙ ከሆነ ለማጥራት የሚሞከሩ ነገሮች ይባሱኑ መልሶ ማደፍረሱ የማይቀር ነው፡፡ በእነዚህ ሁሉ መንገዶች አልፎ ኮሚሽኑ በሕዝብ ያለውን አመኔታ ከፍ ማድረግ አለበት፡፡ በጦርነት ላይ ያሉ አካባቢዎችን ለማሳተፍ የሚችልበትን እቅድ መንደፍ የግድ ይለዋል፤አሊያ ለፍቶ መና መቅረት ነው፡፡

በፖለቲካው ትኩሳትና ወላፈን እየተማገደ ያለው ከማንም በላይ ወጣቱ ክፍል እንደመሆኑ በዋናነት ትኩረቱን በእነርሱ ላይ በማድረግ ተሳታፊነታቸውን ማሳደግ አማራጭ የለውም። በአብዛኛው የግጭት መንስኤ እየሆኑ ያሉት የወሰንና የድንበር አስተዳደር ጉዳዮች፤ግንባር ቀደም ራስ ምታቶች ናቸውና ቅድሚያ በመስጠት አስቸኳይ መፍትሔዎችን ማፈላለጉ ነገሩን ቀለል ያደርገዋል፡፡

አሁን አሁን በሀገራችን ውስጥ የሚንጸባረቁ ዝብርቅርቅ ስሜቶች አሉ፤ እያንዳንዳችን ፍላጎታችንና አስተሳሰባችን የተለያየ ነው፡፡ ባለፉት ታሪኮቻችን ላይ ሳይቀር የሀሳብ ግጭት፣ የቋንቋ መደበላለቅ ይታይብናል፡፡ ሀገራዊ ምክክሩ የተራራቁ አስተሳሰቦችን ለማቀራረብ ይጠቅማል፤ የጥላቻ እና የቂም ግድግዳዎችን አፈራርሶ በሕዝቦች መካከል ጤናማ መስተጋብር እንዲፈጠር ያደርጋል፡፡ ታዲያ ለዚህ ሁሉ ስኬት መብቃት የምንችለው ሁላችንም በቅን ልቦና ለሀገራዊ ምክክሩ ውጤታማነት ይበጃል በምንለው መንገድ ጠጠር መወርወር የቻልን እንደሆን ነው፡፡ ለሰላም እጦት ምክንያት የሆኑትን ተነጋግረን ያልፈታናቸው ችግሮች የነገዎቹ ትውልዶች እና የነገዋ ኢትዮጵያ በአዲስ ምዕራፍ እንዲጓዙ ፊታችንን ወደ ሀገራዊ ምክክሩ አዙረን ሰላሟ የተረጋገጠ ኢትዮጵያን ልናስረክብ ግድ ይላል፡፡

# የማዕድን ሀብትን በአግባቡ ጥቅም ላይ ለማዋል ምን ይደረግ ?

**ሄለን ወንድምነው**
**ዜና ትንታኔ**

ኢትዮጵያ በበርካታ የማዕድን ሀብት የታደለች ሀገር ናት። ያለውን ሀብት በሚፈለገው ደረጃ አልምቶ ተጠቃሚ ከመሆን አኳያ ብዙ ይቀራታል። የማዕድን ሀብት በአግባቡ ማወቅና መጠቀም ከተቻለ የሀገሪቱ ኢኮኖሚያዊ እድገት ላይ ተጨባጭ ለውጥ ማምጣት ይቻላል። መንግሥት ተግባራዊ እያደረገው ከሚገኘው ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ ትኩረት ከሰጠባቸው አምስት ዘርፎች አንዱ የማዕድን ዘርፉ ነው።

የማዕድን ዘርፉ ቢለማ ኢኮኖሚያዊ እድገቱ ላይ ምን ለውጥ እንደሚያመጣ እና በሀገሪቱ ያሉ የማዕድን ሀብትን በሚፈለገው ደረጃ አውቀን እንዴት ተጠቃሚ መሆን እንደምንችል የዘርፉ ምሁራን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት አስተያየታቸውን ሰጥተዋል።

በዓመት ወደ ውጭ ከሚላኩት ጠቅላላ ምርቶች በአማካኝ ሶስት ቢሊዮን ዶላር ገቢ ይገኛል። ከዚህ ውስጥ የማዕድን ዘርፉ ድርሻ ከ500 ሚሊዮን ዶላር አይበልጥም። ኢትዮጵያ የበርካታ ማዕድን ሀብት መገኛ ብትሆንም በዓመት ከምታገኘው የወጪ ንግድ ገቢ ውስጥ የማዕድን ዘርፉ 12 በመቶ ብቻ ነው የሚሉት የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ኢኮኖሚክስ መምህር አለማየሁ ገዳ (ፕሮፌሰር) ናቸው።

ኢትዮጵያ ካላት የማዕድን ሀብት ውስጥ ወርቅና የተፈጥሮ ጋዝን ለአብነት ያነሱት ፕሮፌሰር አለማየሁ፤ በሚፈለገው ደረጃ ማልማት ቢቻል ሀገሪቱ አሁን ላይ በዓመት የምታገኘውን የወጪ ንግድ ገቢ በሁለቱ ማዕድናት ብቻ መሸፈን ይቻላል ይላሉ።



አለማየሁ ገዳ (ፕሮፌሰር)



ደረጀ አያሌው (ፕሮፌሰር)

የወጪ ንግድ ገቢን ከማሳደግ ባለፈም ለሥራ ዕድል ፈጠራ፣ ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን በሀገር ውስጥ ለመተካት፣ በኢንዱስትሪ፣ በግብርናው እና በኢኮኖሚያዊ እድገቱም ተጨባጭ ለውጥ ማምጣት እንደሚቻል ጨምረው ያስረዳሉ።

የማዕድን ሀብቱን በሚፈለገው ደረጃ አልምተን ተጠቃሚ ለመሆን፣ ከማዕድን ሀብቱ የሚገኘውን ገቢ ማሳደግ እና የጸጥታ መደፍረስ እንዳያጋጥም የሚቆጣጠር የመልካም አስተዳደር ሥርዓት ቀድሞ መዘርጋት ተገቢ መሆኑን ያስገነዝባሉ።

የማዕድን ሀብቱን በተገቢው ጊዜ መጠቀም ካልቻልን ዋጋ ያጣሉ የሚሉት ፕሮፌሰር አለማየሁ፤ አሁን ላይ ወደ ሥራ እየገቡ ያሉት ኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎች እየበዙ ሲሄዱ ነዳጅ ዋጋ ሊያጣ ይችላል የሚል ስጋት አላቸው። ዓለም በቴክኖሎጂ እየተራቀቀች ያለችበት ዘመን በመሆኑ ሌሎች ማዕድናትንም በአግባቡና በጊዜው መጠቀም ካልቻልን ሊተካቸው የሚችል ሌላ ጥሬ ዕቃ እየተፈጠረ ሳንጠቀምባቸው ዋጋ ሊያጡ እንደሚችሉ ያመላክታሉ።

አሁን ላይ ኢኮኖሚያዊ ዕድገታችን ላይ ለውጥ ለማምጣት ማዕድናትን ወደ ውጭ በመላክ የውጭ ምንዛሬ ገቢን ማሳደግ፣ እሴት ጨምሮ በማምረት የሀገር ውስጥ ገበያን ማስፋፋት እና ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን በሀገር ውስጥ መተካት እንደሚገባ ይመክራሉ።

ማዕድንን አውጥተን እሴት ጨምረን በመሸጥ ተጠቃሚ መሆን እንድንችል ከመውጣቱ በፊት በሰው ኃይል፣ በአደረጃጀት፣ በበጀት እና በቴክኖሎጂ ሰፊ ዝግጅት ማድረግ ይገባል ብለዋል።

ካለፉት ስድስት ዓመታት ጀምሮ በዓመት ከወርቅ የምናገኘው ገቢ እንደሚዋዥቅ አንስተው፤ ከፍተኛው ገቢ 600 ሚሊዮን ዶላር ሲሆን፤ ዝቅተኛው ደግሞ 180 ሚሊዮን ዶላር ነው። ይህ የሆነበትም ሕገወጥነት፣ በአንዳንድ አካባቢዎች የሚፈጠሩ የጸጥታ መደፈረስ እና ሥርዓት አለመዘርጋቱ ነው ይላሉ።

የዘርፉን ችግር ፈትተን ኢኮኖሚያዊ እድገቱ ላይ ለውጥ ለማምጣት መንግሥት ለዘርፉ ትኩረት በመስጠት ሕገ ወጥነትን መቆጣጣር፣ ሰላም ማስከበር እና ሕጋዊ ሥርዓት መዘርጋት ከቻለ በቢሊዮን የሚቆጠር ገቢ ማግኘት ይቻላል ነው ያሉት።

ኢትዮጵያ በርካታ የማዕድን ሀብት መገኛ ብትሆንም እስካሁን ድረስ ምን ያህል ሀብት እንዳላት የዳሰሳ እንጂ ጥልቅ ሆነ ጥናት አልተካሄደም የሚሉት ደግሞ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሥነምድር መመህርና ተመራማሪ ደረጀ አያሌው (ፕሮፌሰር) ናቸው።

በሀገሪቱ ሁሉም አካባቢዎች አስተማማኝ ሰላም፣ በቂ በጀት እና የሰው ኃይል ከለሌ የሥነምድር ጥናት ለማድረግ ያስቸግራል የሚሉት ፕሮፌሰር ደረጀ፤ ለእነዚህ ጉዳዮች መንግሥት ተገቢውን ትኩረት ሰጥቶ ያለንን የማዕድን ሀብት በተገቢው ሁኔታ ማወቅ እና መጠቀም እንደሚያስፈለግ ያስረዳሉ።

ከዳሰሳ ጥናት በመውጣት ዝርዝርና ጥልቅ የካርታ ሥራ መሠራት እንዳለበት አንስተው፤ የት አካባቢ ምን ዓይነት ማዕድን ይገኛል፣ የተገኘው ማዕድን ለምን ዓላማ ይውላል፣ በምን አይነት መንገድ ተጠቃሚ ልንሆንበት እንችላለን የሚሉትን ዝርዝር ጉዳዮች ማወቅ ተገቢ መሆኑን ያመላክታሉ።

## ‹‹የኢትዮጵያ ዲፕሎማሲ...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

ዘመን ዲፕሎማሲን ምን መምሰል እንዳለበት የሚዳሰስበት እንደሚሆን ጠቅሰዋል።

በዚህም ታሪክን፣ አሁናዊ ሁኔታዎችንና መጪውን ጊዜ በማስተሳሰር ጠንካራ ዲፕሎማሲያዊ አቅም ለመገንባት እንደሚያስችል ጠቅሰው፤ ሁሉም ዜጋ በዲፕሎማሲ ሥራዎች እንዲሳተፍና ጉዳዩ የሕዝብ አጀንዳ እንዲሆን ሀገራዊ ንቅናቄ ለመፍጠር የዲፕሎማሲ ሳምንት በየዓመቱ እየታሰበ እንደሚቀጥል ገልጸዋል።

ለውጡን ተከትሎ ብዙ ዘርፎች ላይ የሪፎርም ሥራዎች ተሠርተዋል ያሉት አቶ ደመቀ፤ የኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ ማዕቀፍም ብሔራዊ ጥቅማችንን ማስጠበቅና ሉዓላዊነታችንን ማስከበር በሚያስችል መልኩ ሪፎርም ተደርጓል ነው ያሉት።

በዚህም የውጭ ግንኙነታችን በቀዳሚነት ኢኮኖሚ ዲፕሎማሲ ያተኮረ እንዲሆን ሥራዎች ተሠርተዋል ያሉት ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ባለብዙ ወገንና የሁለትዮሽ ወገን ላይ ያተኮረ፣ የፖለቲካ ማእቀፍ ላይ ማዕከል ያደረገ ዲፕሎማሲ እንዲሁም ዜጋ ተኮር ዲፕሎማሲን እንደ አንድ ትልቅ ማዕቀፍ አድርጎ የያዘ የውጭ ግንኙነት የዲፕማሲው ዋና ዋና የትኩረት መስኮች መሆናቸውን ጠቁመዋል።

የውጭ ጉዳይ የውጭ ግንኙነት ፖሊሲያችን ማጠንጠኛው ከሀገራዊ ፍላጎቶችና ተጨባጭ ሁኔታዎች የሚነሳ ነው ያሉት አቶ ደመቀ፤ ቀዳሚ ዓላማውም በሁሉም መስክ ብሔራዊ ጥቅምን ማረጋገጥና ሉዓላዊነትን ማስከበር መሆኑን ገልጸዋል።

የፖሊሲ ማዕቀፉ ለጎረቤት ሀገራት ቅድሚያ ትኩረት እንደሚሰጥ ጠቅሰው፤ ከዚህ ባለፈ ወደ አፍሪካ ብሎም ወደ ዓለም አደባባይ በባለብዙ ወገንና በሁለትዮሽ ግንኙነት እየሰፋ ይሄዳል ብለዋል።

የፖሊሲ ማእቀፉ ሲዘጋጅ ያለፉትን ዓመታት መልካም ልምዶች መነሻ በማድረግ ነው ያሉት ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ በዓለም አቀፍ ደረጃ የኢትዮጵያን ተደማጭነት፣ ብሔራዊ ጥቅምና የዓለም አቀፍ ውድድርን ሀገራዊ ጥቅማችንን ባስከበረ መልኩ እውን እንዲሆን የሚያደርግ መሆኑን አስገንዝበዋል።

በኢትዮጵያ ዲፕሎማሲ ታሪክ በየዘመኑ ብዙ ፈተናዎች እያጋጠሙ በወቅቱ የነበሩ መሪዎችና ሕዝቡ ባደረጉት ተጋድሎ ፈተናዎችን እየተሻገረች ዛሬ ላይ ደርሳለች ያሉት አቶ ደመቀ፤ በቅኝ ግዛት ዘመንም ብቸኛዋ የጥቁር ሕዝብ ወኪል ሆና በሊግ ኦፍ ኔሽን ተሳትፋለች።

ኢትዮጵያ በየዘመኑ ሲደርስባት የነበረውን ልዩ ልዩ ጫና ተቋቁማ በሠራችው ዲፕሎማሲ ከራሷ አልፎ ለአፍሪካውያንና ሌሎችም ጥቁር ሕዝቦች ትልቅ አስተዋጽኦ ማበርከቷን ተናግረዋል።

ባለፉት ሦስት ዓመታትም በኢትዮጵያ ላይ የከፋና ዘርፈ ብዙ ጫና ሲደረግ እንደነበር አስታውሰው፤ በፀጥታው ምክር ቤት ብቻ ኢትዮጵያ ከ13 ጊዜ በላይ አጀንዳ ተደርጋ ከፍተኛ ጫና እንዲያርፍባት ተደርጓል። በተጨማሪም ኢኮኖሚያዊና ልዩ ልዩ ማእቀቦች እንዲጣልባትና እርዳታንም እንደ አንድ ጫና መፍጠሪያ ለመጠቀም ተሠርቷል ብለዋል።

ይሁን እንጂ ኢትዮጵያውያን፣ መንግሥትና ወዳጅ ሀገራት ባደረጉት ከፍተኛ ርብርብና ተጋድሎ ኢትዮጵያ ሁሉን አቀፍ የሆነውን ጫና ተሻግራ ሉዓላዊነቷን፣ የግዛት አንድነቷንና ብሔራዊ ጥቅሟን አስጠብቃ መቀጠሏን አብራርተዋል።

ችግሩን ለመሻገር የኢትዮጵያን ትክክለኛ አቋም ማሳወቅ፣ በስሜት የሚመጡ ጫናዎችን ማለዘብና ወዳጅ ሀገራት የኢትዮጵያን እውነት ተገንዝበው ከጎናችን እንዲቆሙ የሚያስችሉ ተግባራት መከናወናቸውን አስታውሰው፤ የዓባይ ግድብን ድርድር ከአፍሪካ አውድ ለማውጣት የተደረገውን እንቅስቃሴ በማክሸፍ ወደ አፍሪካ ማእቀፍ እንዲመለስ ማድረግ መቻሉንም አውስተዋል።

በጥቅሉ በተሠራው ጠንካራ ዲፕሎማሲ ከኢትዮጵያ በተቃራኒው ቆመው የነበሩ አንዳንድ ሀገራትም የኢትዮጵያን እውነት ለመረዳት ከጎናችን ለመቆም በቅተዋል ያሉት ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ በዚህ ሂደት ውስጥ ጉልህ ሚና ለነበራቸው ባለድርሻ አካላትም ምስጋና አቅርበዋል።

በቀጣይነትም ኢትዮጵያ በዓለም መድረክ ያላትን ተጽእኖ ፈጣሪነት ለማስቀጠል ሀገራዊ አንድነታችንን አጠናክረን በጋራ መቆም ይጠበቅብናል ብለዋል።

የዲፕሎማሲ ሳምንት "ዲፕሎማሲያችን ለብሔራዊ ጥቅማችን፣ ከአፍሪካ መዲና እስከ ዓለም መድረክ" በሚል መሪ ቃል ከጥር ሁለት እስከ 24 ቀን 2016 ዓ.ም በሳይንስ ሙዚየም ይካሄዳል።

## ባንኮች...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

ለኢንተርፕራይዞች ብድር እያቀረቡ አይደለም።

ባንኮች ከብድር አኳያ በብሔራዊ ባንክ መመሪያ መሠረት ከዓመታዊ የብድር ዕቅዳቸው ውስጥ አምሥት በመቶ የሚሆነውን ለኢንተርፕራይዞች ማበደር እንዳለባቸው የሚያዝ መሆኑን አንስተው፤ ሆኖም ይህ ወደ ትግበራ ያልገባ እና ኢንተርፕራይዞችን የገንዘብ ችግር ሊፈታ ያልቻለ ነው ብለዋል።

በብሔራዊ ባንክ መመሪያ መሠረት ለኢንተርፕራይዞች ብድር ያቀረቡትን ማበረታታት እና ያላቀረቡትን መጠየቅ የተለመደ እንዳልሆነም ጠቁመዋል። ለኢንተርፕራይዞች ብድር ያቀረቡትንና ያላቀረቡትን መከታተል ያስፈልገናልም ሲሉ ተናግረዋል።

ባንኮች ለኢንተርፕራይዞች መስኮት ከፍተው ማገልገል እንዳለባቸው ጭምር የብሔራዊ ባንክ መመሪያ እንደሚያዝ ያነሱት አቶ ንጉሡ፤ ይህ እየተደረገ ባለመሆኑ መሥሪያ ቤቱ ከባንኮች ጋር ጉዳዩን አስመልክቶ ውይይት ቢኖረውም በብዙኃን መገናኛ ተከታታይ ዘገባ ካልተደገፈ በቶሎ ውጤታማ መሆን እንደማይችል አስገንዝበዋል።

ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ከብሔራዊ ባንክ ጋር የተገናዘበ የብድር አሰጣጥ አሠራር አለው ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ ኢንተርፕራይዞችን ተጠቃሚ ለማድረግ ከፋይናንስ ተቋማት ጋር በቅንጅት መሥራት ይገባል ብለዋል።

ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ኢንተርፕራይዞች ብድር ማግኘታቸውን የሚከታተልበት ሥርዓት እንዳለ ጠቅሰው፤ ይህ የአሠራር ክትትል ከክልሎች ጋር እና እስከታችኛው መዋቅር የሚዘልቅ መሆኑን ጠቅሰዋል።

የኢንተርፕራይዞች ብድር አቅርቦት በየሩብ ዓመቱ ሪፖርት የሚደረግ መሆኑንና የቁጥጥር እና ክትትል ሥራ በተከታታይ የሚሠራበት መሆኑንም አያይዘው ተናግረዋል። ይህ ኢንተርፕራይዞች የሚያነሱትን ሃሳብ ለማዳመጥ ዕድል ይፈጥራል ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ መሬት ላይ እየተከናወኑ ያሉ ሥራዎችን በተጨባጭ ለማየት የሚረዳ መሆኑን አስገንዝበዋል።

ይህም ሆኖ በዘርፉ ያሉ ሥራዎች ጤናማ ናቸው ለማለት የሚያስደፍር አይደለም፤ በመሆኑም አሠራሩ አደረጃጀቱ እና ማንዋሎች ምን እንደሚሉ እና መሬት ላይ በተጨባጭ ያለውን ተግባር መመርመር ያስፈልጋል ብለዋል። ይህን ማድረግ ለሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ አንድ ኃይል እና ግብዓት ይሆናል ብለዋል።

## ለድርቅ አደጋ...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

ወደ አራት ሚሊዮን የሚጠጉ ዜጎች መኖራቸውን አንስተው፤ ኮሚሽነሩ፤ ከዚህ ውስጥ 80 በመቶዎቹ የሚገኙት በትግራይ፣ በአማራና በአፋር ክልሎች የሚገኙ መሆናቸውን ተናግረዋል።

በተለይ በአማራ ክልል ስምንት ዞኖች፣ በትግራይ ክልል አራት ዞኖችና በአፋር ክልል ሶስት ዞኖች ላይ የሚገኙ ዜጎች ለድርቅ አደጋ የተጋለጡ በመሆኑ በሚቀጥሉት ሶስት ወራት ተከታታይነት ያለው የሠብዓዊ ርዳታ ድጋፍ ይቀርባል ብለዋል።

የአስቸኳይ ርዳታ ድጋፍ የሚሹ ዜጎች ተገቢውን የሠብዓዊ ርዳታ እንዲያገኙ መንግሥት እየሠራ መሆኑንና በቂ የእህል ክምችት እንዳለውም ጠቁመዋል።

አምባሳደር ሽፈራው እንደገለጹት፤ መንግሥት ከአጋር አካላት ጋር በመተባበር በቀጣይ ሦስት ወራት ለስድስት ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ዜጎች የሠብዓዊ ርዳታ ተደራሽ ያደርጋል።

አብዛኛውን ድጋፍ የሚያቀርበው መንግሥት ቢሆንም ዓለም አቀፍ ተቋማት የድጋፍ ማዕቀፋቸውን አሳድገው እንዲመጡ ጥረት እየተደረገ ይገኛል ሲሉ አስረድተዋል።

መንግሥት በመላ ሀገሪቷ ባሉት ከሶስት ሺህ በላይ የምግብ ማከማቻ ጣቢያዎች አማካኝነት እስካሁንም የሠብዓዊ ድጋፍ እያቀረበ መሆኑን አስታውሰው፤ በአማራ ክልል ሰሜን ጎንደርና ዋግ ኽምራ አካባቢዎች ቀደም ብሎ ከተላከው ድጋፍ ከፊሉ ቢደርስም ከፊሉ በፀጥታ ችግር የተነሳ አለመድረሱንና አልሚ ምግብ ጭነው መንገድ ላይ የቆሙ ተሳቢ ተሽከርካሪዎች መኖራቸውን ገልጸዋል።

የሠብዓዊ ድጋፎች ለታለመላቸው ዓላማ እንዲውሉ ማንኛውም አካል ትብብር ሊያደርግ እንደሚገባና ችግሮቹን በጋራ መፍታት እንደሚያስፈልግ መልዕክት አስተላልፈዋል።

የአየር ንብረት ለውጥ በተለያዩ አካባቢዎች የሚገኙ ዜጎችን ለተረጂነት እያጋለጠ መሆኑን ያነሱት ኮሚሽነሩ፤ ባለፉት ጊዜያት ከድርቅ ባለፈ በደረሱ የተለያዩ የጎርፍ አደጋዎች አንድ ነጥብ አምስት ሚሊዮን ዜጎች ላይ ጉዳት መድረሱን ጠቁመዋል።

መንግሥት ከ2015 ዓ.ም ሐምሌ ወር አንስቶ እስከ ታህሳስ መጀመሪያ ድረስ 11 ቢሊዮን ብር የሚያወጡ ቁሳቁሶችንና የምግብ ድጋፎችን በሶስት ዙሮች በማቅረብ በተለያዩ ሰው ሠራሽና የተፈጥሮ አደጋዎች ለተጎዱ ዜጎች መታደጉን ኮሚሽነሩ ገልጸዋል።

# ወቅታዊ

# "በራሱ የሚኮራና ከድህነት የተላቀቀ፣ ማኅበረሰብና ሕዝብ እንዲኖር መሥራት ያስፈልጋል"

ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር እና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር
አቶ ደመቀ መኮንን



**የዲፕሎማሲ ሳምንትን አስመልክቶ ከምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር እና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን ጋር ያደረግነው ቃለምልልስ ሙሉቃል**

**አዲሰ ዘመን፦ የዲፕሎማሲ ሳምንትን የማክበር ዓላማና አስፈላጊነቱን ቢገልጹልን?**

**ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር እና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን ፦** አሁን የታቀደው የዲፕሎማሲ ሳምንት ዝግጅት ዋናው ዓላማ በሦስት ቁልፍ ጉዳዮች ላይ ያተኮረ ነው። አንደኛ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር እንደተቋም ከተደራጀ ጀምሮ 116 ዓመት ሆኖታል። ስለዚህ ያለፉት ዓመታት የዲፕሎማሲ ጉዟችን በየዘመኑ ያሳረፉት ዐሻራ፤ ያሉት ወረቶች እና የምንማራቸውን ትምህርቶች በማየት ያንን የዲፕሎማሲ ጉዞ የሚዳስስ ይሆናል።

በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ አሁናዊ ሁኔታችን በዲፕሎማሲ መስክ ምን ይመስላል? ምን ዕድሎች አሉ? ምን ፈተናዎችስ አሉ? ብሔራዊ ጥቅማችንን አስከብረን ለመሻገር ምን መደረግ አለበት? የሚለውን ለማየት በእጅጉ ይጠቅማል።

ሦስተኛው ደግሞ የመጭው ዘመን ዲፕሎማሲን ያማተረ የዲፕሎማሲ ሳምንት ዝግጅት ነው። ታሪክንም፣ አሁናዊ ሁኔታንም፣ የመጪው ዘመንም፤ ሦስቱም ጉዳዮች በአንድ ላይ በማስተሳሰር ይህንን የዲፕሎማሲ ሳምንት በኤግዚቢሽን፣ በፓናል እና በልዩ ልዩ ዝግጅቶች ብናከብረው ለመጪው ጊዜ የተሻለ ሀገራዊ ንቅናቄ መፍጠር ይቻላል በሚል ነው ዲፕሎማሲያችን የሚለው ዝግጅት እያደርግን ያለነው፡፡

ሁለተኛ ከዛሬ 116 ዓመት በፊት ጥቅምት 4 ቀን ነው የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር እንደ ተቋም የተደራጀው፤ ከዚያም በፊት በልዩ ልዩ መልክ የዲፕሎማሲ ግንኙነት አልነበረም ማለት አይደለም። ቀደምት የሆኑ ግንኙነቶች ሃይማኖታዊ መልክ ያላቸው፤ ኢኮኖሚያዊ መልክ ያላቸው፤ ባህላዊ እና የፀጥታ ገጽታ ያላቸው፤ ኢኮኖሚያዊ፣ በንግድ፣ በልዩ ልዩ መልክ የሚታዩ የዲፕሎማሲ እንቅስቃሴዎች ነበሩ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ያሉትን ቁም ነገሮች መዳሰስ፤ በደረስንበት ልክ ለዚህ ትውልድ በእጅጉ ይጠቅማል፤ እንደወረትም ይወሰዳል።

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር እንደ አንድ የፌዴራል ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት ሆኖ ከተቋቋመ ጀምሮ ያለው ተቋማዊ እንቅስቃሴ ምን ይመስላል? የሚለው ተያይዞ ሲወሰድ ትልቅ ትርጉም አለው። ልክ ከሁለት ሳምንት በፊት ጥቅምት 4/2016 ዓ/ም የመከላከያ ሚኒስቴር በተመሳሳይ ጊዜ የ116 ዓመት ምሥረታውን አክብሮ ለመጪው ዘመን ተልዕኮ ዝግጅት እንዳደረገ ሁሉ የውጭ ጉዳይ የዲፕሎማሲያችን እቅድ እና መነሻም በዚህ ዙሪያ ያጠነጠነ ነው ማለት ነው።

**አዲስ ዘመን፦ ቀጣይነቱስ ምን ይመስላል?**

**ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር እና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን፦** በእኛ በኩል የምናስበው ይኸ የዲፕሎማሲ ሳምንት ዘንድሮ በእነዚህ በሦስት አውዶች ላይ አተኩሮ የመጀመሪያው ዝግጅት ይሆናል። በየዓመቱ የዲፕሎማሲ ሳምንት እንደዚህ ሰፋ ባለ ዝግጅት ባይሆንም እየታሰበና ዓመታዊ ተልዕኮዎችን ቆጥሮ እያስቀመጠ ሁሉም ዜጋ በዲፕሎማሲ ተሳትፎ ውስጥ እንዲንቀሳቀስ ለማድረግ የሚያስችል አጀንዳ አድርጎ ለመቀጠል እንሠራበታለን። በየዓመቱ በጥቅምት ወር ዓመታዊውና ያለፈው ሥራ ሲገመገም፤ ለመጪው ሥራ ዕቅድ ሲዘጋጅ ይኸንን ያሰበ ቢሆን ሥራውን የበለጠ ያጠናክረዋል፤ የሕዝብ አጀንዳ ያደርገዋል የሚል እምነት ነው ያለን፤ እናም ይቀጥላል።

ባለፉት ጥቂት ዓመታት የለውጡን ማዕቀፍ ተከትሎ በውጭ ጉዳይ፣ በውጭ ግንኙነታችንም እንደዚሁ በግልጽ የተቀመጡ ሀገራዊ ጉዳዮች አሉ። የዲፕሎማሲው አንጓዎች ዋና ዋና የትኩረት መስኮችም፡-አንደኛ፣ የኢኮኖሚ ዲፕሎማሲ ላይ ያተኮረ፤ በሁለተኛ ደረጃ፣ በአጠቃላይ ፖለቲካ የባለብዙ ወገን፣ የሁለትዮሽ ወገን ላይ ያተኮረ የፖለቲካ ማዕቀፍ ላይ ያተኮረ፤ በሦስተኛ ደረጃ ደግሞ የዜጋ ዲፕሎማሲን እንደአንድ ትልቅ ማዕቀፍ አድርጎ የያዘ የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ የትኩረት አቅጣጫዎች ናቸው ያሉት፡፡

ሁለተኛ የውጭ ግንኙነት ፖሊሲያችን ማጠንጠኛው በመጀመሪያ ደረጃ ከሀገራዊ ፍላጎቶች፣ ከሀገራዊ ተጨባጭ ሁኔታዎች ይነሳና ውጭ ጉዳይ ወይም የውጭ ግንኙነት ሲባል ብሔራዊ ጥቅምን ማረጋገጥ ነው፤ ሉኣላዊነትን ማስከበር ነው። በሁሉም መስኮች ጥቅማችንን የማረጋገጥ ጉዳይ ስለሆነ ከሀገራዊና ከውስጣዊ ሁኔታ ይነሳል ማለት ነው። ከዚህ ተነስቶ ቅድሚያ ትኩረት የሚሰጠው ለጎረቤት ሀገራት ይሆናል። ጎረቤት ሀገራት ጋር የሚሰጠው ትኩረት እና ሚዛን እንዳለ ሆኖ ደግሞ ወደ አፍሪካ አህጉር ይሻገራል፤ ከዚያ ወደዓለም አደባባይ፡፡

በባለብዙ ወገን (Multilateral) የሚባለውም፣ በሁለትዮሽ ግንኙነትም እየሰፋ የሚሄድ የዲፕሎማሲ የግንኙነት ማዕቀፍ ነው ያለው ማለት ነው። ቀደም ካሉት ዓመታት ሥርዓቶች የነበሩ አዎንታዊ ልምዶችን መነሻ በማድረግ በለውጡ ማዕቀፍ ልዩ ልዩ የለውጥ ፓኬጆች ሲዘጋጁ የውጭ ግንኙነታችን የቱ ላይ የበለጠ ቢያተኩር? ካለፈው የትኛውን ቢያሻሻል? ለመጭው የትኛውን ቢያጠናክርና ቢያጠብቅ ይሻላል? የሚል መነሻ ተወስዶ ነው የተዘጋጀው፡፡ በእነዚህ ማጠንጠኛዎች ጎረቤት ላይ አተኩሮ፤ ወደአህጉር ዘል እና በዓለም አቀፍ ደረጃ የኢትዮጵያን ተደማጭነት፣ የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅም እና በዓለም ውድድር ጥቅማችንን ባስከበረ ሁኔታ እውን እንዲሆን የሚያደርግ ነው ማለት ነው።

**አዲስ ዘመን ፦ ከተገኙ ውጤቶች፣ ዋና ዋና የሚባሉት ምንድን ናቸው ?**

**ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር እና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን፦** በቅድሚያ በእነዚህ ዓመታት ያለው ጉዞ፣ ያጋጠሙ ተግዳሮቶች፤ የተገኘው ውጤት እና ለመጪው የምንማረው ምንድን ነው? የሚለውን ብናየው የተሻለ ይሆናል ብዬ አስባለሁ።

እንግዲህ በኢትዮጵያ የዲፕሎማሲ ታሪክ በየዘመኑ ብዙ ፈተናዎች እያጋጠሙ ያንን በየዘመኑ መሪዎች፣ በየዘመኑ ባለድርሻ አካላት በሕዝቡ ዋና አቅም ያንን እየተሻገረች አገራችን ብዙ አሻራዎችን አስቀምጣ እዚህ ደርሳለች። ቀደም ብለን በቅኝ ግዛት ዘመን ኢትዮጵያ ብቸኛዋ የጥቁር ሕዝብ ተወካይ ሆና በ"ሊግ ኦፍ ኔሽን" የታደመችበትንና የተጫወተችውን ታሪካዊ ሚና ስንመለከት፤ ከእርሱም ጋር ተያይዞ በጥቁር ሕዝቦች ታሪክ ብዙ ዝርዝር ጉዳዮችን ስናይ የኢትዮጵያ ዲፕሎማሲ በሁለትዮሽ ግንኙነት ለራሷ ለኢትዮጵያ እና ለኢትዮጵያ ሕዝብ ብቻ ሳይሆን ለአፍሪካውያንና ለጥቁር ሕዝቦችም የተጫወተችውን ሚና በደንብ አድርጎ መመልከት ያሻል ማለት ነው።

ያጋጠሙ ፈተናዎች ምን ያህል ፈታኝ እንደነበሩና በየዘመኑ ዐሻራዎች እያሳረፍን የዘለቅንበት የ116 ዓመታት ጉዞ አለ። በእነዚህ የጉዞ ሂደቶች ውስጥ ደግሞ በዚህ በለውጡ ዘመን በተለይ የሦስቱን ዓመታት የዲፕሎማሲ እንቅስቃሴ ስንመለከተው ምናልባት በጣም የከፋና ፈርጀብዙ የሆነ ጫና በኢትዮጵያ ላይ ያረፈበት፤ ያንን ለመሻገር ኢትዮጵያውያን፣ መንግሥት እና ወዳጆቿ ከፍተኛ ርብርብና ተጋድሎ ያደረጉበት ዘመን ነው። በየዘመኑ ለነበሩ ብዙ ፈተናዎች እና ያንን ለመሻገር ለተሠሩ ጥበቦች በየራሳቸው ሚዛን እውቅናና አክብሮት መስጠት በእጅጉ ያስፈልጋል። ያለፉት ጥቂት ዓመታት ሂደትን ስንመለከተው ደግሞ እንዲያው ትውልድ እንዲማርበት ዘርዘር አድርጎ በእንዲህ ዓይነት የጥያቄና መልስ ጊዜ ብቻ ሊዳሰስ የማይችል ጥልቅ የሆኑ ገጠመኞች አሉት።

ለዚህ ውይይት እንዲሆን እንዲያው ለማሳያ አንዳንድ ጉዳዮችን እንናንሳ፣ ለውጡ የተለያዩ የሪፎርም አጀንዳዎችን አውጆ ወደሥራ ሲገባ የውጭ ጉዳይ የግንኙነት ማዕቀፎቹን አሻሽሎ በዜጋ ዲፕሎማሲ፣ በኢኮኖሚ፣ በፖለቲካው እና ተያያዥ በሆኑ ጉዳዮች ሲቀጥል በፊት ከነበረው ተሻጋሪ የሆኑ ጉዳዮች እንደዚሁም ደግሞ ለውጡ ራሱ ያመጣቸው የለውጥ አጀንዳዎች በራሱ የዲፕሎማሲውን ሁኔታ ወደልዩ ልዩ ፈተናዎች እና እድሎች እንዲገባ አድርጎታል። ለምሣሌ፥ የህዳሴ ግድብን ብንመለከተው ከለውጡ በፊት ዓመታትን ያስቆጠረና የኢትዮጵያ ሕዝብ ከዳር እስከዳር እየተረባረበ እያሸጋገረው የነበረ ፕሮጀክት ነው። የለውጡ ዘመንም ይኸንን በመረከብና ያሉበትን ማነቆዎች በመፍታት ወደተሻለ እንቅስቃሴ እንዲገባ ያመቻቸ ነው። ህዳሴ ግድቡ በራሱ በዲፕሎማሲው ላይ ቀደም ብሎ የተጀመረ፤ በለውጡ ዘመን ደግሞ ከፍተኛ ጫና እንዲያርፍብን ያደረገና ብዙ ፈተናዎች ኢትዮጵያ ያለፈችበት ነው።

አንደኛ፣ ከሕዳሴ ግድቡ ጋር ተያይዞ ጫና በኢትዮጵያ ላይ ወርዶባታል። ሁለተኛ ለውጡን ባለመቀበልና በልዩ ልዩ ምክንያት በሀገር ቤት ከፍተኛ የጦርነትና ሀገርን የሚፈታተን ችግር አጋጥሞ ነበር። ከእርሱ ጋር የተያያዙ ፈርጀብዙ ጫናዎች እንደበረዶ ኢትዮጵያ ላይ የሚወርዱበት ሁኔታም ነበር። አንዳንድ ጎረቤት ሀገራት ያንን አጋጣሚ ተጠቅመው ለምሣሌ ሱዳን ጊዜውን ተጠቅማ ወረራ አካሂዳ የተወሰኑ ቦታዎችን የያዘችበት፤ ለአንዳንድ ሽማቂ ኃይሎች ጥግ ሰጥታ በኢትዮጵያ ላይ ጥቃቱ እንዲስፋፋ ያደረገችበት ጊዜ ነበር።

ግብጽና ሱዳን የጋራ ወታደራዊ ስምምነት እያደረጉና ስምምነት ብቻ ሳይሆን በድንበር አካባቢ እንቅስቃሴ እያደረጉ የመጨረሻውን የጦር ቃታ ለመሳብ እያንዥበበቡ ያለበት ሁኔታ ነበር። በዓለም አደባባይ በሴኩሪቲ ካውንስል ብቻ " ከ13 ጊዜ በላይ በአማካይ በወር አንድ ጊዜ ኢትዮጵያ አጀንዳ እየተደረገች ፋታ ያጣንበት ዘመን ነበር። በዚያን ወቅት የተፈጥሮ እና ሰው ሠራሽ ችግሮችም በእጅጉ ኢትዮጵያን ይፈትኑ ነበር። ለምሣሌ፥ የኮቪድ ዘመን፣ የዓለም ችግር ሆኖ ኢትዮጵያም ላይ የነበረው ፈተና በራሱ የዲፕሎማሲውን ሂደት

ወደ ገጽ 8 ዞሯል

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ወቅታዊ

# "በራሱ የሚኮራና ከድህነት የተላቀቀ፣ ማኅበረሰብና ...

ከገጽ 8 የዞረ

ያወሳሰበ እና የራሱ ጫና የነበረው ነው። ሌሎች የተፈጥሮ ችግሮችም በኢትዮጵያ ተከስተው ነበር። ልዩ ልዩ ማዕቀቦች፣ በኢትዮጵያ ላይ የሚደረጉት ከሰብዐዊ መብት ጋር የተያያዙ ክሶችና በጄኔቫ በተከታታይ በኢትዮጵያ ላይ ይደረግ የነበረውን ጫና ማንሳት ይቻላል፡፡

በዩኤስ በኩል ከፍተኛ ጫና ያሳደሩ የኢኮኖሚና የልዩ ልዩ የማዕቀብ ውሳኔዎች የተላለፉበት፤ ኢትዮጵያን ሊፈትኑ የሚችሉ አጀንዳዎች በሙሉ በኢትዮጵያ ላይ የተጫነበት፤ ከአንዳንድ ሀገሮች በመቶ ሺሕ የሚቆጠሩ ዜጎች በአንዴ ከዚያ አገር አስወጥቶ ኢትዮጵያ እንድታስተናግድ ከፍተኛ ጫና እንዲያድርብን የተደረገበትም ነበር፡፡ ሀገር ቤት በሚካሄደው ጦርነት የአፍሪካ መዲና የሆነችው አዲስ አበባ ለዲፕሎማሲ ያልተመቸችና ለደህንነት ስጋት ስለሆነች ብዙ አገሮች "ውጡ፣ እንውጣ" አድማ የገቡበት፤ ኤምባሲያቸውን እየዘጉ ለመውጣትና ሁሉንም ነገር ለማጨለም የተሠራበት ወቅት ነበር። ሌሎች በዚህ በዝርዝር ያላካተትኳቸው ጉዳዮችን ስንጨምር እነዚህ ዓመታት ኢትዮጵያን በእጅጉ የፈተኑና ኢትዮጵያን ከፍተኛ ፈተና ውስጥ የጣሉ ጉዳዮች ነበሩ።

የህዳሴ ግድብ ጉዳይ ከአፍሪካ አጀንዳ ወጥቶ ወደሌሎች አካላት እንዲሄድ፤ የሰላም ድርድር ተብሎ የተያዘው አጀንዳ ከአፍሪካዊ አጀንዳነት ወጥቶ ሌሎች አካላት ሊቆጣጠሩት የፈለጉበት፤ የሰብዓዊ ድጋፍ እንቅስቃሴና ሌሎች የአገልግሎት አጀንዳዎች ከሌሎች የዲፕሎማሲ፣ የኢኮኖሚ ፍላጎቶች ጋር ተያይዘው ኢትዮጵያን ለማንበርከክ እና እጅ ለመጠምዘዝ እንደመሣሪያ የተወሰዱበት ነበር፡፤ በአጠቃላይ ጫናዎቹ ተቆጥረው የሚያልቁ አይደሉም ብሎ ማስቀመጥ ይቻላል።

**አዲስ ዘመን ፦ እነዚህን ጫናዎች እንዴት መሻገር ቻልን ?**

**ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር እና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን ፦**

የመጀመሪያው የድሉ ምንጭ እና ሀብት የኢትዮጵያ ሕዝብ ጽናት፣ የኢትዮጵያ እንደሀገር ብርታት እና የተዋናዮቹ ጥበብና ብልኀት እንዲሁም የወዳጆቻችን አብሮ መቆም ይሆናል ማለት ነው። በእነዚህ አራት ጭብጦች ውህድ ውጤት ኢትዮጵያ ይኸን ፈተና ተሻገራ ዋናውን መስመሯን ሳትለቅቅ በታሪክ በየዘመኑ የተሻገርንባቸውን የአገር ሉአላዊነት፣ የግዛት አንድነት እና የብሔራዊ ጥቅምን በማስከበር ይኸንን በረዶ ለመሻገር ችላለች። ይኸ ድል እንደትልቅ ድል እና ስኬት ሊወሰድ ዋናው ባለቤት ደግሞ የኢትዮጵያ ሕዝብ መሆኑ ሊሰመርበት ይገባል ማለት ነው።

እንደትምህርት ይኸን ለመሻገር ይሠራ የነበረው ሥራ ምንድን ነው? በሰፊው የሕዝብ አቅም ውስጥ ሆኖ ዲፕሎማሲው ሲንቀሳቀስ አንደኛ የኢትዮጵያን ትክክለኛ አጀንዳ፣ ኢትዮጵያ ራሷን መግለጽ አለባት። ራሷን (ዲፋይን) ማድረግ አለባት። ስለዚህ ማስገንዘብ ለተለያዩ አካላት ለተለያዩ ወገኖች የኢትዮጵያን አቋም ማስገንዘብ፤ በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ በስሜት፣ በልዩ ልዩ ጫና የሚመጡ ነገሮችን የማለዘቡ ሥራ ትልቅ ጥበብ ሆኖ ነው የታየው፤ በሦስተኛ ደረጃ ደግሞ በእንዲህ ዓይነት ፈታኝ ጊዜ ወዳጅ ማብዛት ያስፈልጋል።

ወዳጆች በትክክል ተገንዝበው አብረው እንዲቆሙ፤ ኢትዮጵያን ሆነው ለጥቅማችን ድርሻቸውን እንዲወጡ ለማድረግ በሚያስችል ሥራ ታስገነዝባለህ፤ ጫናውን ታለዝባለህ ሁሉንም በማካረርና ክሩ እንዲበጠስ በማድረግ ሳይሆን የሚያሻግርህን ጥበብ በመከተል ወዳጅ ታበዛለህ። በሀገር ቤት ባለው አቅም በእነዚህ የግንኙነት ጥበቦች በየደረጃው በተሠራው ሥራ ይኸንን የማሻገር፣ ዲፕሎማሲው ወደነበረበት እንዲመለስ



(ሪኢንጌጅመንት) የሚል ታክቲክ ተዘርግቶ በዚያ ነው ይሠራ የነበረው፤ ሁኔታው ወደተሻለ ምዕራፍ ሲሸጋገር ደግሞ ከዚያ አለፍ ብሎ የነበረው ግንኙነት የተሟላ የማድረግና እና ወደላቀ ግንኙነት ደግሞ ልንሄድ ይገባል። ክንዳችንን እያበረታን፤ እጃችንን እያስረዘምን በሁለትዮሽ ግንኙነት፣ በጎረቤት ሀገር፣ በሁለትዮሽ፣ በዓለም አቀፍ አውድ ላይ የቆምንበት እና የተሻገርንበት ነው።

የህዳሴ ግድባችንን የሦስትዮሽ ድርድር ከአፍሪካ በማውጣት ቀደም ሲል ዋሽንግተን በዘመነ ፕሬዚዳንት ትራምፕ ጊዜ ከፍተኛ ጫና እየተካሄደ፤ ከዚያ ቅርቃር ውስጥ አውጥቶ አፍሪካዊ እና የኢትዮጵያና አፍሪካዊ በለቤትነት ያለው ድርድር እንዲካሄድ ማድረግ በጣም ትልቅ ስኬታማ ሥራ ነው ማለት ነው። በሌሎች መገለጫዎች ሊጠቀሱ የሚችሉ ሥራዎችም እንደዚሁ ተሠርተዋል ማለት ነው።

ያንን በማጠንከር ራሳችንን የማሳወቅና የማስገንዘብ ሥራ ስንሠራ፤ የማለዘቡ ሥራ ሲከናወንና ወዳጅ ማስፋቱ በስፋት ሲሠራ ቀደም ከነበሩት ታሪካችንና ከሀገራችን የፍትሕ ጥያቄ ጋር እያያያዙ አንዳንድ አገሮች መልሶ የማስተዋልና ኢትዮጵያን ቆም ብለን እናዳምጣት፤ እውነትም የፍትሕ ጥያቄ አላት ብለው በይፋ የገፉበትና ከእኛ ጋር የቆሙበት ነው።

በዚህ ሁሉ ሥራ የሕዝባችን ጥንካሬ ግሩም ነበር። ዲያስፖራው በ#No more እንቅስቃሴ ርብርብና ዘመቻ ሲያካሂድ እያንዳንዱ ዜጋ ያለውን ወርውሯል። አገሩን ለመታደግ ማለት ነው። በእነዚህ ጉዞዎች ነው ይህ ውጤት የተረጋገጠው፤ እዛም ላይ እየቀጠልን፤ እየቀጠልን ለኢትዮጵያ መያዣ ተብለው የተዘየዱት ወይም የተቀመሩት የማነቆ መሣሪያዎች እንዲነሱ በዓለም አደባባይ ላይ ያደረግንበት፤ እንዲያውም ከዚያ አልፈን እንደነ ብሪክስ ዓይነት አዳዲስ የትብብር ማዕቀፎችም ውስጥ ኢትዮጵያ አባል ሆና የገባችበትና በዩኤንም በአውሮፓ ኅብረትም በልዩ ልዩ መስኮች የተሻለ ግንኙነትና የተሻለ እንቅስቃሴ ውስጥ የገባንበት ሁኔታ አለ ማለት ነው፣ በአጭሩ ጉዞው ፈተናዎቹ፣ስኬቶቹም የድሉም ምንጭ ይህ ነው ማለት ነው፡፡

**አዲስ ዘመን ፦ ለመጪው ዘመን የዲፕሎማሲ ሥራችን ሀገራዊ ዝግጅታችን ምን ይመስላል፣ ምንምን ሥራዎችስ እየተሰሩ ነው፣ ኢትዮጵያ ያላት ተስፋና እድል ምንድ ነው?**

**ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር እና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን ፦**

ኢትዮጵያ ያላት ተስፋና ዕድል የሚለውን ጭብጥ ስታነሳ አንዳንድ ነገር መጡብኝ፣ እኔ በዚህ የስራ አጋጣሚ በውጭ ግንኙነት ስራ ጥቂት ዓመታት ስንቀሳቀስ የተገነዘብኩት ብዙ ሀገራት አፍሪካውያን፣ በታሪክ በመጣንባቸው በልዩ ልዩ መልኮች ለኢትዮጵያ ያላቸው ክብርና ግምት በጣም የላቀና ትልቅ ነው፡፡ አንዳንድ ጊዜ እኛ በልዩ ልዩ አጀንዳ ተወጥረን በአለንበት ዓለምን የሚፈትኑ ጉዳዮች ሲመጡ በዩናይትድ ኔሽን ሌላ ቦታ አቋም የሚወሰድባቸው፣ድምጽ የሚሰማባቸው፣ ጊዜያት ሲመጡ ኢትዮጵያ በራሷ ብዙ ችግርና ብዙ ጫና ያለባት ቢሆንም ፣ ኢትዮጵያ ትልቅ አገር ናት፣ ኢትዮጵያ በዩናይትድ ኔሽን፣ በአፍሪካ ህብረት ትልቅ ቦታ ያላት ሀገር ናት፡፡

የኢትዮጵያ ድምጽ፣ የኢትዮጵያ መልዕክትና ተጽዕኖ ተባዥ ነው፡፡ ከዚህ አኳያ ነው ሚናችሁን መወጣት ያለባችሁ፣ይህን አቋም ውሰዱ፣ እንዲህ ዓይነት እርምጃ ውሰዱ፣እንዲህ ዓይነት ድምጽ አሰሙ በሚል ትልቅ ግምት ሰጥተው ነው የሚነግሩን። በነገራችን ላይ ኢትዮጵያ ምናለች ይባላል፡፡ አፍሪካውያን ፣የላቲን አሜሪካ ሀገራት እና ብዙ የዓለም ሀገራት ለኢትዮጵያ ያላቸው አተያይና እይታ በጣም ከፍያለ ነው፡፡ ይህ የሚሆነውም በታሪክና በልዩ ልዩ ገጠመኝ የኢትዮጵያን ቦታ ስለሚያውቁ ነው፡፡

ይህ ትልቅ ዕድልና ሀብት አለ፡፡ ኢትዮጵያውያን ደግሞ በዚህ ፈታኝ ጊዜም፣ በየዘመኑም በነበረውም ምንያህል በጽናት ለነጻነታቸውና ለክብራቸው ተዋድቀው ይህን አገር ለዚህ እንዳበቁ ለሌሎችም የጥቁር ህዝብ ነጻነት መገለጫ ሆነን የመቆም ሌጋሲ አለ፡፡ ይህ የሕዝባችን ውጤት ነው፡፡ ይህ ሁሉ ዕድል እያለ በተለያዩ ስሜቶችና ፍላጎቶች ቅርብ አዳሪ በሚመስል ደረጃ ልዩ ልዩ አጀንዳዎች እያጣቀስን እኛው ራሳችን በሀገር ቤት ውስጥ የምንናቆርበት፣ የምንቋሰልበትና ኢትዮጵያን የምንገዘግዝበት አጋጣሚ ያሳዝነኛል፡፡

ለኢትዮጵያ ጠንካራ ዲፕሎማሲ ይኑር ከተባለና ተጽዕኖ ፈጣሪነቷ ይስፋ ይደግ ከተባለ፣ ማጠንጠኛው መጀመሪያ ሀገር ቤት ውስጥ የሚኖረን አብሮነትና አንድነት ነው። በሀገርቤት ውስጥ የሚኖር ጥንካሬ ተባዥነቱ በየትኛውም የፕላኔቷ ማዕዘናት ውስጥ ያርፋል፡፡ ስለዚህ የትኛውንም ሃሳብ፣ የትኛውንም ልዩነት፣ የትኛውንም ፍላጎት በኢትዮጵያ ማዕቀፍ ውስጥ ጥፋት ሳናስከትል ስልጡንና በሰላማዊ ሁኔታ የመፍታትን ባህል ማዳበር አለብን፡፡ ጠንካራ ሀገር መገንባትና ፣ አብረን መቆም ነው የኢትዮጵያ ትልቁ ተስፋና መሰረቷ፡፡ ይህ ነው ዋናው ማዕዘን። በታሪክም በልዩ ልዩ ስሜትም የምናሳንሳት፣ የማናቆስላትና የምንገዘግዛት፣ ልጆቿ ነን እንጂ በዓለም አደባባይ በብዙ ማዕዘናት ለኢትዮጵያ ያለው ግምትና ክብር ትልቅ ነው፡፡ ለዚያ ክብር እኛው ባለቤቶቹ መሪ ሆነን ጠንክረን መራመድና መቆም አለብን ማለት ነው፡፡

ለመጪው ዘመን ውስጣዊ አብሮነት፣ አንድነት፣ በኢኮኖሚ ከድህነት መውጣት፣ ሀገርን መውደድ ላይ አተኩረን መሥራት ይገባል፡፡ በራሱ የሚኮራ፣ ከድህነትና ጠኔ የተላቀቀ፣ ማኅበረሰብና ሕዝብ እንዲኖርም መስራት ያስፈልጋል፡፡ ይህን

ወደ ገጽ 9 ዞሯል

# “በራሱ የሚኮራና ከድህነት የተላቀቀ፣ ማኅበረሰብና ...

ከገጽ 8 የዞረ

የቤት ሥራ ከሠራን የመጪውን ዘመን ዲፕሎማሲ በስኬትና በማማ ላይ ሆኖ መቀጠል ይቻላል። የመጪው ዘመን ዲፕሎማሲን የምንተነብየውም ከወዲሁ በእይታ ውስጥ ነው፡፡ ዞሮ ዞሮ ሀገርና ሀገራት አስካሉ ድረስ ዲፕሎማሲ ይኖራል። የዲፕሎማሲው አውድና ስልቱ ምን ይሆናል የሚለው ደግሞ እንደየዘመኑ መሰለፍና መታጠቅ ያስፈልጋል፡፡

ለመጪው ዘመን ዲፕሎማሲ ከወዲሁ አስቦ አሁን ያለው ዓለማዊ ሁኔታ፣ ጂኦፖለቲካውና የሀገራት ፍላጎት፣ ምንድነው እያሉና እያነበቡ፣ የዲፕሎማሲውን መንገድ መቃኘት ይገባል፡፡ አሁን ስናይ የጂኦፖለቲካው ሁኔታ በጣም ተገማች ባልሆኑ ሁኔታዎች ይቀያየራል፡፡ አይቀራረቡም በምንላቸው ሀገራት መካከል የበለጠ የመቀራረብ ነገር እናያለን። በትብብር ማዕቀፍ ይታወቁ የነበሩ የትብብር ማዕቀፎች መልካቸውን እየቀየሩ በሌላ አግባብ ይስተዋላሉ፡፡ እና የመጪውን ዘመን ዲፕሎማሲ ፍኖተ ካርታ ለማስቀመጥ አሁን ያለውን ተለዋዋጭ ሁኔታ መነሻ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

ዲፕሎማሲ ስንል በመጪው ዘመን የሚለዋወጠውን ሁኔታ ከራስ ሁኔታ ጋር አጣጥሞና ተወዳዳሪ ሆኖ መቆም ይጠይቃል፡፡ በየዘመኑ አዳዲስ ቴክኖሎጂ ሲመጣ ዲፕሎማሲ አለቀለት፣ በሌላ ተተካና ብዙ የሚባሉ አንዳንድ ሊትሬቸሮች እንደዚያ ይታያል፡፡ የተለያዩ የግንኙነት መስኮች፣ የዓለም ውድድር እና ሀገራት እስካሉ ድረስ፣ ዲፕሎማሲው መልኩን እየቀየረ እንደሚቀጥል ማወቅና ለዚያ የሚበቃ ዝግጅት ማድረግ ይገባል ማለት ነው፡፡

አሁን እንኳ ስናየው ድሮ ከነበረው የመደበኛ ወይም ኮንቬንሽናል የምንለው ዲፕሎማሲ ብቻ ሳይሆን አሁን መታገያው፣ ዲጅታል ዲፕሎማሲ ተጨምሮበታል። የሶሻል ሚዲያው ሁኔታና ላንድ ስኬፑም ተቀይሯል። ዝምብለህ ረጅም ቀጠሮ እየያዝክ እና ፊት ለፊት እየተገናኘህ የከረትሲ ኢንጌጅመንት አሁን ላይ በቂ አይደሉም፡፡ ፈጣን፣ በእጅ ላይ በያዝነው ሞባይል ቴክኖሎጂው ኮንቨርጅ አድርጎ ሁሉም መረጃ በአንድ ጊዜ የሚደርስበት፣ እያንዳንዱ መሪ፣የውጭ ጉዳይ አምባሳደሩ ሁሉም ቲዊት አድርጎ በልዩ ልዩ መሣሪያዎች ግንኙነት የሚያደርግበት ነው ዘመኑ።

ያንን የሚመጥን ዝግጅትና ስራ ካልተሰራ የዲፕሎማሲ ሥራው ከእጃችን ወጥቶ ሌሎች በፈለጉት መልክ ዲፋይን እያደረጉ የሚቀጥሉበት ሁኔታ እየታየ ነው፡፡ ስለሆነም ያነን የሚመጥን የዲጂታል ዲፕሎማሲ ስርዓት አቅም መገንባትና ተወዳዳሪ ሆኖ መገኘት ያስፈልጋል፡፡ አሁን እየመጣ ያለው የጂኦ-ዲጂታል ኢኮኖሚ ሁኔታ የወደፊት የግንኙነቱ አግባብ በኢኮኖሚ ግብይትና ግንኙነት ዲፕሎማሲውን ለመጠቀም የበለጠ ተፈላጊ እየሆነ መጥቷል፡፡ ለምሳሌ የዩኤስ ሲል ካምፓኒ ላይ ያለ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴና እዚያ ላይ ያለ የቴክኖሎጂ ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ አንዳንድ ሀገሮች የራሳቸውን አምባሳደር ለዚያ ተልዕኮ ብቻ መድበው የሚከታተሉበትና ቴክኖሎጂን ለመጠቀም የሚሰሩበት ሁኔታ አሁን ይስተዋላል፡፡

ለአንድ ሀገር አንድ ሚሽን የማቋቋም ብቻ አይደለም፡ በዓለም ላይ ባሉት የሴኩሪቲ፣ የቴክኖሎጂ፣ የሌሎች የግንኙነቶች አውዶች ብሔራዊ ጥቅምን ለማስከበር የምሰማራበት ገበያ የት ቦታ ነው፣ የሀገሬን ፍላጎት በትክክል ለመጠቀም የሚያስችለኝ ስምሪት ምንድነው፣ እያሉ እያሰቡና ተለዋዋጭ የሆኑ ሁኔታዎችን እየቀጠሉ ለዚያ የኢኮኖሚ ሁኔታ ስራዬ ብለው መድበው የሚሰሩበት አለ፡፡ እንደአርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ዓይነት አብዮቶች አሁን እየመጡና እየተስፋፉ ባሉበት ሁኔታ የዲፕሎማሲው ውሎና ተወዳዳሪነት ምን ይሆናል የሚለውን ማሰብና ከወዲሁ መዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡

የድርድር የስምምነት ፣የሌሎች የኢንጌጅመንት ሁኔታዎች በምን አግባብ ነው ሊቀጥሉ የሚችሉት የሚለውን ለመመለስ ቴክኖሎጂው የሚሰጠውን እድል በአግባቡ መጠቀም፣ የሚፈጥረውን አሉታዊ ጫና የሚመክት ሀገራዊ አቅም መገንባትና መሥራት ያስፈልጋል። ከዚህም ባለፈ የዲጂታል ኢኮኖሚ የኢኖቬሽን መሰረተ ልማት አጠቃላይ እንቅስቃሴ ከውጪ ጉዳይ የፖሊሲ ማዕቀፍ ጋር መቃኘትና መተሳሰር አለባቸው፡፡

ዲፕሎማቶቻችን ያንን የሚመጥን ትጥቅ ያስፈልጋቸዋል፡ ፕሮፌሽናሊዝም ያስፈልጋቸዋል፣ የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ብቃት ይጠይቃቸዋል። በቴክኖሎጂው አውድ ውስጥ የሚሰማሩ ኢትዮጵያውያን ወጣቶች ኢትዮጵያን ለብሔራዊ ጥቅሟ የሚያበቃትን አዎንታዊ አስተዋጽኦ ለማድረግ መንቀሳቀስ ይጠበቅባቸቸዋል፡፡ ወደ ፊት እጅግ ተገማች ያልሆነ የዲፕሎማሲ አውድ እየተፈጠረ መሄዱ አይቀርም፡፡ ዲፕሎማሲ ሲባል አንድ ቦታ የሆነ ኤምባሲ ወይም ቆንስላ ጽ/ቤት በመክፈት፣ አምባሳደር በመሾም፣ ዲፕሎማት በመመደብ፣ በአንድ መንገድ ብቻ የሚንቆረቆር የዲፕሎማሲ ጉዞ ብቻ በቂ አይደለም፡፡

በዓለም ላይ ተደራሽ ለመሆን የሚያስችለን ዘመኑ የሚጠይቀውን አሰላለፍ እና ስምሪት ይጠይቃል፡፡ መደበኛ ያልሆነ ዲፕሎማሲ አስፈላጊ እየሆነ መጥቷል። ምናልባት አንዳንድ ጊዜ አንድን ኢትዮጵያን ወክሎ አንድ ቦታ መልዕክተኛ በመሆን ፣የመሪን መልዕክት ለማድረስ፣አንዳንድ ጉዳዮችን ለማስፈጸም፣ለዚያ ሀገር ፣ለዚያ አጀንዳ፣ተጽዕኖ ፈጣሪ የሆነ፣ በዲፕሎማሲው መስክ ያልተሰማራ ግን ሌላ ዜጋ የበለጠ ጠቃሚ ሆኖ ሊገኝ ይችላል፡፡ በአትሌቲክስ መስክ የታወቀ፣በቢዝነስ መስክ የታወቀ፣ በሌሎች አጀንዳዎች ተጽዕኖ የፈጠሩ በሙሉ የኢትዮጵያ አምባሳደሮች ሆነው የሚሰሩበት ሁኔታ እየፈጠሩ መሄድ ያስፈልጋል፡፡

ዘመቻው፣ ከበባው፣ ውሎው፣ በአንድ ጠባብ መንገድ ብቻ የሚፈስ ሳይሆን፣ በሁሉም አቅጣጫ የእኛን ተጠቃሚነት የሚያረጋግጡ ስምሪቶችና እንቅስቃሴዎች ያስፈልጋሉ፡፡ ቴክኖሎጂ አጠቃቀምን ማሳደግ ያስፈልጋል፡፡ ለየዘመኑ የሚጠይቀውን ብቃትና ቴክኖሎጂ መላበስ በእጅጉ ያስፈልጋል፡፡ የዲፕሎማሲያችን ሳምንት አንድ ትልቅ ቦታና ግምት የሰጠው ለመጪው ዘመን ዲፕሎማሲ እንዴት እንዘጋጅ፣ አሁን ያሉት አመልካች ሁኔታዎች ምን ይመስላሉ፣ በዚህ ዙሪያ የአደጉ ሀገራት ቀድመው አርቲፊሻል ኢንተለጀንስንና ሌሎቹን በመጠቀም ምን ምን እየሰሩ ነው የሚለውን በመረዳት ሁልጊዜ እኛ ሌላው ተጠቅሞበት ፣ውሎበት ያንን እየተከተልን የምንኖር መሆን የለብንም የሚለውን ነው። ተከታዮች መሆን የለብንም፣ ሁሉም እኩል ተሰልፎ የሚዋኝበት፣የሚተውንበት፣ጥቅሙን ለማስከበር የሚንቀሳቀስበት፣ዘመን ነው መሆን ያለበት፡፡

በዘመናት ሌሎች ቴክኖሎጂዎች ቀድመው ሀገራቸውን ወደ ሌላ ማማ አሸጋግረዋል፡፡ እኛ ከብዙ ጊዜ በኋላ ተከትለንና መንዝረን ለመከተል ሞክረናል። በዚህ መንገድ ግን መጪው ዘመን መሻከም አይቻልም። ይኸ አገር የሚመጥነው እና ማድረግ ያለብን አዳዲስ የዓለም መዋጊያ፣ መሰማሪያ አውዶችን በሙሉ ፈጥነን የማወቅ፣ አገራዊ አቅም የመገንባት በዚያ ደረጃ ጥቅማችንን የሚያስከብር ስምሪት እና ውሎ ነው። እና አዲሱ ዲፕሎማሲ በዚህ አቅጣጫ የሚገራ፤ ለዚህ የሚያስፈልጉ ፍኖተ ካርታዎች፣ በደንብ ቆጥሮ የሚያስቀምጥና ሁሉንም የሚያሰልፍ መሆን አለበት፡፡ ከዚህም በላይ ኢትዮጵያውያን ከዳር እስከዳር የትኛውም ፍላጎት ቢኖር ለአንድ የጋራ ሀገር አምባሳደር ሆኖ መንቀሳቀስ እና በቅቶ መገኘትን ይጠይቃቸዋል ማለት ነው። መጪው ዘመን በዚህ ነው መቃኘት ያለበት፤

ዲፕሎማሲያችን ቀደምት ታሪኮች አሉት። ቀደም ብዬ እንዳልኩት 116 ተቋማዊ የዲፕሎማሲ እንቅስቃሴዎች አሉት። ስለሆነም ይኸንን በትክክል መዘከር፤ በትክክል መቀመር እና ወረቶቹን ማወቅና መጠቀም ያስፈልጋል። እኛ ሀገር ብዙው ችግር በየዘመኑ የምንመጣ ኃላፊዎች፣ መሪዎች እና የፊት ተዋናዮች የዱሮውን በማፍረስና እንደፍርስራሽ በመጣል ከአዲስ መሠረት ለመነሳት ብዙ እንጥራለን። ነገር ግን ከቀድሞው መማር፣ ወረቶቹን መውሰድ ተገቢ ነው፡፡ ስለሆነም ከቀድሞ አንጋፋ ዲፕሎማቶች፣ አምባሳደሮች እና ተዋናዮች ትምህርት መውሰድ ያስፈልጋል።

በእነከተማ ይፍሩ ዘመን ምን ተሠራ? ምን ጥሩ ነገር አለ? በእነአክሊሉ ሀብተወልድ ዘመን ምን ምን ጥሩ ነገር ተሠራ? በእነኮሎኔል ጎሹ ወልዴ ዘመን ምን ጥሩ ነገር ተሠራ? በውጭ ጉዳይ ቤት ውስጥ በእነስዩም መስፍን ዘመን ምን አዎንታዊ ጥሩ ነገር ተሠራ? በእነብርሃኑ ዲንቃ ዘመን ምን ጥሩ ነገር ተሠራ? በማለት ከፍት ሆኖ፤ በጎ ነገሮቹን ሁሉ መስጥሮ ለሀገር የሚጠቅመውን ማሻገር ያስፈልጋል ማለት ነው።

ውጭ ጉዳይ በዚህ ደረጃ ሁልጊዜ የሚማር፤ ሁልጊዜ የሚበቃ ተቋም እያደረጉ መምራትና ሁሉንም አቅሞች የሚያንቀሳቅስ መሆን ይኖርበታል። እንደ ውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤትነቱ አምባሳደሮቹ ሚሊዮኖች እንደሆኑ ማወቅና ማሰብ ያስፈልጋል።ዲፕሎማሲ፣ የውጭ ግንኙነት ሥራ በሰባቱ ቀናት በ24 ሰዓት ውስጥ በጣም ብዙ ተለዋዋጭአዳዲስ ሁኔታዎች የሚያጋጥሙበት ነው። ሁልጊዜ መማርን ያስፈልጋል። ሁልጊዜ ዝግጁ መሆንን ይጠይቃል። ሁልጊዜ ብሔራዊ ጥቅምን ለማስከበር የሚያስችል ዝግጁነት ይፈልጋል።

እኔ በሕይወት ዘመኔ በብዙ የሥራ መስኮችን ለመሳተፍ ሞክሬአለሁ። ባልሳተፍበትም ደግሞ ሁልጊዜ ትምህርት፣ ሁልጊዜ ሐላፊነት፣ ሁልጊዜ ዝግጅት የሚጠይቁ መስኮችን ለመለየት በትዝብቴ አይቻለሁ። መምህር ለማስተማር ሁልጊዜ ያነብባል፤ ሌሰን ፕላን ያዘጋጃል፤ ከዚያም በሳምንታዊ ሌሰን ፕላኑ የቀናቱን ያስተምራል። ጋዜጠኝነት እንደፕሮፌሽን እንደሥራ ሲወሰድ ሁልጊዜ ለዛ የሚመጥነውን ዝግጅትና ተልዕኮ ማድረግ አለበት።

ዲፕሎማትነት ከዚህ አኳያ ሁልጊዜ ዝግጁ መሆንን ይጠይቃል። ስለኢትዮጵያ ምን ተባለ? ኢትዮጵያ ምንድን ነው የምታጋራው? የራሷን ተፅዕኖ ለማሻገር የሚስችላት ምንድነው የሚለውን ማወቅ ይጠይቃል ማለት ነው። እንዲህ ዓይነት ዝግጁነት በሰፊው አውድ ውስጥ ሆኖ መሥራትን እና ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ ያስፈልጋል። የዲፕሎማሲ ሥራው ከዚህ አኳያ ካለፉት ወረቶች እየተጠቀመ ውስጣዊ አብሮነትንና አንድነትን እያጎለበተ መጓዝን ይጠይቃል፡፡

በዓለም ላይ ኢትዮጵያን ታሪኳን፣ አዎንታዊ ሚናዋን፣ እና ሕዝቧን የሚመጥን የዲፕሎማሲ ሥራ እንዲቀጥል ማድረግ አስፈላጊ ነው። ያ ሲሆን ብሔራዊ ጥቅም ይረጋገጣል። ሉአላዊነት ከፍ ባለ ደረጃ ይከበራል። በየትኛውም ቦታ የኢትዮጵያ ተደማጭነት እና የኢትዮጵያ ጉልህ ሚና ቦታውን ይይዛል። ያንን እውን ለማድረግ ሁሉም ባለድርሻ አካላት ሚናውን እንዲወጣ ማድረግ ያስፈልጋል ነው የምለው፡፡



**አዲስ ዘመን፡-** ስለነበረን ቆይታ እጅግ በጣም እናመሰግናለን ።

# ጎሜ

# ከእናንተ ውስጥ ለሀገሩ አምባሳደር የሆነው ማን ነው?

ምሕረት ሞገስ

እነገብረየስ ገብረማሪያም ዛሬም በማምሻ ግሮሰሪ ጠረጴዛ ከበው ተቀምጠዋል፡፡ ዘውዴ መታፈሪያ ማማረሩን ተያይዞታል፡፡ ተሰማ መንግሥቴ እና ገብረየስ የዘውዴን ምሬት ከመቀላቀል ይልቅ በፅኑ እየተቃወሙት ነው፡፡ እርሱ ደግሞ ‹‹እኔ ኢትዮጵያን ሀገሬ ናት ለማለት እየተቸገርኩ ነው፡፡ ያልተነካ ግልግል ያውቃል፡፡ እናንተ የማትማረሩት ስላልጎደለባችሁ እና በደል ስላልደረሰባችሁ ነው›› ይላቸዋል፡፡ እነርሱ ደግሞ መማረር ልማድ ሆኖብህ እንጂ ተለይቶ ለአንተ ብቻ የጎደለብህ ነገር የለም፡፡ ደግሞም ምንም ቢመርህ ለሀገርህ ክፉ መመኘትም ሆነ ሀገርህን መካድ እና በገዛ ሀገርህ ላይ ማሚረት የለብህም እያሉት ነው፡፡

‹‹በእርግጥ የጠለቀ የማሰብ ችሎታ ከሌለን ሀገራችንን አንወድም፡፡ ለእያንዳንዱ ጉዳይ የማይገባውን ትኩረት እየሠጠን ሀገራችንን የምንጠላበት ምክንያት አድርገን እናስቀምጣለን፡፡›› በማለት ተሰማ ዘውዴን ለመገሰፅ ሞከረ፡፡

ዘውዴ በበኩሉ፤ ‹‹ሀገራችንን እንወዳለን ካልን ከልባችን መሆኑን ማሳየት እና ያንንም መተግበር አለብን። የእኛ ሀገር መውደድ ግን ከቃል ያለፈ፤ ከአንደበታችን የተረፈ አይደለም፡፡ ለእዚህ ማረጋገጫ ካስፈለገ፤ ጥሎ ማለፍ ሳያስፈልግ ለመጣል የምናባክነውን ገንዘብ እና የምናፈሰውን ደም ብቻ መጥቀስ ይቻላል፡፡ ሀገር ለእኔ ጋራ ሸንተረሩ ወይም መሬቱ አይደለም፡፡ ሀገር ለእኔ በዋናነት ሰው ነው፡፡ ሲል ምላሽ ሰጠ፡፡

ገብረየስ ደግሞ፤ ‹‹ምንም ቢሆን ለሀገር ከመሥራት እና በየትኛውም ዓለም የሀገር አምባሳደር ሆኖ ሀገርን ከማስተዋወቅ በተቃራኒው ቆሞ ሀገር ማዋረድ እና አገር መጥላት ትክክል አይደለም፡፡ ነገር ግን በየትኛውም መስክ ዕድል ቀንቶህም ሆነ በትጋትህ ቦታ ስታገኝ በእውነተኛ ስሜት ሕዝብን ማገልገል ይጠበቅብሃል፡፡ ሆኖም አንዳንድ ጊዜ በተቃራኒው ይሆናል ይሔ ደግሞ ሰዎች ሀገራቸውን እንዲጠሉ ያስገድዳቸዋል፡፡

በተናጠል ውጤት ብናመጣ እንኳ በጋራ ከዛ በላይ ውጤት ማምጣት እንደምንችል አምነን ሌላውን ለማስጠጋት ከመሞከር እና በሀገር ደረጃ ውጤታማነትን ከማረጋገጥ ይልቅ ለራሳችን አጥር እንሠራለን፡፡ የቅንጦት እና የምቾት ኑሮን ከሀገር በላይ በማስቀደም ሀገር መካድ፤ ጠመንጃ በያዘ ጠላት ሳንሸነፍ ስኳር በያዘ የውጪ ጠላት ተጠልፈን ሀገራችንን እስከመሸጥ እንደርሳለን፡፡ በስኳር እየተታለሉ ሀገር እወዳለሁ ማለትም ውሸት ነው። እንደአንተም በአደባባይ ሀገር ለመጥላት መዳዳትም ፍፁም ነውር ነው፡፡›› ብሎ ብርጭቆውን አንስቶ የሚጠጣውን ተጎነጨ፡፡

ዘውዴ ገብረየስን ከተል ብሎ ‹‹ሰዎች ለጊዜው ባለሥልጣን፣ ገንዘብ ያላቸው ወይም ቀልጣፋ እና ጉልበት ያላቸው ሆነው ሁሉን ማድረግ ይችሉ ይሆናል። ገንዘብ እና ጉልበት የሌለውን ዕድሜው የገፋ ሰውን ዝቅ አድርገው ሊያዩ ይችላሉ፡፡ ይህ ደግሞ እጅግ ያስቀይማል፡፡ እኔ እንዲህ የሚያደርጉ ሰዎች ተበራክተው፤ አቅመ ደካማ ሆኜ እየተገፋሁ ስኖር፤ ሰዎችን ያሰቃየ ዋጋ መክፈል ያለበት ሰው ዋጋ ሳይከፍል እንዲሁ ዘመናት ሲቆጠሩ ሀገሬን ላለመውደድ እና ኢትዮጵያን እንደሀገሬ ላለመቀበል ባናንገራግር እንደጥፋተኛ መቆጠር አለብኝ ብዬ አላምንም፡፡›› ብሎ ሀገርን አለመውደድ ወይም ሀገርን አለመቀበል እንደጥፋት መታየት የለበትም ሲል ለመሞገት ሞከረ፡፡

ገብረየስ፤ ‹‹ ድፍረትን ማብዛት በምንም መልኩ ስኬታማ ለመሆን ምቹ ሁኔታን አይፈጥርም፡፡ ምንም እንኳ ሀገርን እንደሚወዱ እና እንደሚያከብሩ ቢናገሩም ራሳቸውን ቅድሚያ ሀገራቸውን ሁለተኛ የሚያደርጉ፤ ደፍረው ብዙኃንን እየገፉ የሚያሰቃዩ ሊኖሩ ይችላሉ። ይህም በማኅበረሰብ ደረጃ በሁሉም ነገር የመቀዝቀዝ እና የመሰላቸት ስሜት ሊፈጥር ይችላል፡፡ እኔም በተመሳሳይ መልኩ የመሰላቸት አዝማሚያ ውስጥ ያለሁ ይመስለኛል፡፡ ይህ ቢሆንም ግን የትም ብሔድ ‹የሀገሬ አምባሳደር ነኝ፡፡› ብዬ ስለማምን ሀገሬን በተመለከተ የምናገረውም ሆነ የምሠራው ሀገሬን በሚጠቅም

**አንገትን ደፍቶ በድህነት መኖር እንዲቀጥል፤ ኢትዮጵያ ዘላለሟን በልመና እና በርዳታ ላይ ተንጠልጥላ እንድትዋኝ የሚፈልጉ ስለመኖራቸው መካድ አይቻልም፡፡ ለእኔ እነዚህ ፍፁም ኢትዮጵያዊ አይደሉም**

መልኩ እንደሚሆን አልጠራጠርም፡፡›› አለ፡፡

ተሰማ በበኩሉ፤ ‹‹ በጣም የሚገርመው ልማዳችን መጥፎው መጥፎው ላይ የተንጠለጠለ ነው፡፡ ከማሞገስ ይልቅ ማንኳሰስን እንመርጣለን፡፡ መርምሮ መድኃኒት ሰጥቶ አክሞ ከሚያድነው ይልቅ፤ ተኩሶ የሚገድለውን እናሞካሻለን፡፡ ራሳችንን ስናይ እንኳ ውበታችንን ሳይሆን የጎደለብንን እያየን እንሸማቀቃለን።›› ብሎ ፊቱን ወደ ዘውዴ በማዞር፤ ‹‹በቅርብ ዓመታት ውስጥ የጎደለብህ ቢኖርም ያገኘኸውም በጣም ብዙ ነገር አለ። አንተ ግን ከምሬት አርፈኸ አታውቅም፡፡ ከመማረር ይልቅ መልካም መልካሙን እያየህ ያንንም እያሰብክ እና እየተናገርክ መቆየት ይሻልኃል፡፡ የዛን ጊዜ በሒደት ብዙ መልካም ነገር ሊመጣ ይችላል፡፡ ውጪ ሀገር እየኖሩ ኢትዮጵያን ከማገዝ እና ሀገራቸውን ከማስተዋወቅ ይልቅ፤ በተቃራኒው ሀገር የሚያጠፉ ተግባር እንደሚፈፅሙ ሰዎች መሆን የለብህም፡፡›› አለው፡፡

ዘውዴ ተሰማን በትዝብት አስተያየት እየተመለከተው፤ ‹‹የምፈልገውን ያህል እንኳ ባገኝ ኢትዮጵያ ውስጥ እነዚህ ሁሉ መከራ እና ችግሮች ተከማችተው እንዴት አልማረርም?›› ሲል ተሰማን ጠየቀው፡፡ ተሰማ በበኩሉ፤ ‹‹አሁን ላይ ኢትዮጵያ ውስጥ ብዙ ችግር መኖሩ የሚካድ አይደለም፡፡ የኑሮ ውድነት፤ ግጭት፤ ሥራ አጥነት የመሳሰሉት ችግሮች ብዙ ናቸው፡፡ ነገር ግን እያራገቡ እና እያቀጣጠሉ ችግሩ እንዲሰፋ ከመሞከር ይልቅ፤ ስለሰላም መመካከር እና ችግሮች የሚፈቱበትን ሁኔታ መነጋገር ይሻላል፡፡ ያለበለዚያ ከውጪም ከውስጥም ያለነው ስለሀገራችን መጥፎ መጥፎውን ብቻ እያየን የምናዝን፤ ካየነው በላይ እያጋነንን የምናወራ ከሆነ ዞሮ ዞሮ ተጎጂዎቹ ሁላችንም ነን፡፡

ምሬትን የሚያመጡ ነገሮችም እየተቀጣጠሉ የበለጠ እየሰፉ ይሔዳሉ፡፡ አንዳንዴ እንደውም ሀገራችንን የባሰ ችግር ውስጥ የምንከታት እራሳችን እንሆናለን። ስለሀገራችን በጎ ነገር ከማሰብ እና ከመናገር ይልቅ፤ መልካም ገፅታዋን እያዩ እየተደሰቱ ከማስተዋወቅ ይልቅ በተቃራኒው ሀገራችን ውስጥ የሌለውን ችግር እየጨማመርን መከራውን ቆልለን ካወራነው ሀገር ወዳድ ሳንሆን ሀገር የምንጠላ ግብዞች ነን ማለት ይቻላል፡፡›› ሲል ሁሌም ቢሆን መጥፎ መጥፎውን ማየት እና ያዩትንም አጋንኖ ማስተጋባት ሀገር ወዳድነት ሳይሆን አገር ጠልነት መሆኑን አስረዳ፡፡

ዘውዴ ተቆጣ፤ ‹‹እንዴት እንዲህ ትላለህ? አይንህ እያየ የተፈጠረውን እንዳልተፈጠረ አላየሁም ስለጉዳዩም አልናገርም ብለህ ራስህን ታታልላለህ? ይሔ መቼም ቢሆን ተቀባይነት የሌለው አስተሳሰብ ነው።›› አለና የቀዳውን ቢራ ተጎነጨ፡፡ ተሰማ በበኩሉ፤ ‹‹ያለውን ችግር መካድ አስፈላጊ አይደለም፡፡ ነገር ግን መጥፎውን ብቻ ሳይሆን ጥሩውንም እዩ፤ ሁልጊዜ መጥፎውን እያያችሁ ከምታንቋሽሹ ደጉንም እያያችሁ አሞካሹ። እያልን ነው፡፡ አንተ እና አንዳንዶች ግን ሁልጊዜም ከመጥፎ ወይም ከተሠራ ስሕተት ውጭ ጥሩ እና የተሠራ መልካም ተግባር አይታያችሁም፡፡ ይሄ ደግሞ እናንተን ብቻ ሳይሆን አጠቃላይ ሀገርንም ይጎዳል፡፡›› ሲል ሃሳቡን ገለፀ፡፡

ዘውዴ ከመብረድ ይልቅ ይበልጥ ቁጣው አየለ። ‹‹እናንተ ስትል እነማንን አካተህ ነው? አልገባኝም›› ሲል ተሰማ ላይ አይኑን እያፈጠጠ፡፡ ተሰማ ፈገግ ብሎ፤ ‹‹እናንተማ ኢትዮጵያ ውስጥም ሆነ ከኢትዮጵያ ውጪ እየኖራችሁ ከእኛ በላይ ኢትዮጵያዊ የለም ብላችሁ የምትፎክሩ የተለየን ኢትዮጵያዊ ነን ባዮቹ፤ በተግባር ግን ኢትዮጵያን የማትወዱ፤ አንድ ሰው ሲሞት እልፍ አለቀ እያላችሁ የሞት ዜናንን የምታራግቡ እናንተ ናችሁ። ኢትዮጵያ ግድብ ስትገነባ የምትቃወሙ፤ የባሕር በር ስታገኝ አይናችሁ ደም የሚለብሰውን ማለቴ ነው፡፡

አንዳንዴ ለሀገራችሁ አምባሳደር መሆን ሲገባችሁ በሰው ሀገር ሆናችሁ ሳይቀር የሀገራችሁን ስም በውሸት የምታጠፉ፤ ሠላም እያለ ሠላም የለም እያላችሁ ቱሪስት የኢትዮጵያን ምድር እንዳይረግጥ የምታስፈራሩ...›› ብሎ ሊቀጥል ሲል ሃሳቡን ሳይጨርስ ዘውዴ ከመቀመጫው ተነሳ፡፡

ተሰማ የዘውዴን ከመቀመጫው መነሳት ተከትሎ ወደ ላይ አየው፡፡ ዘውዴ ሰውነቱ እየተንቀጠቀጠ‹‹ እንከባበር እንደእዚህ የማለት መብት የለህም፡፡›› ሲል ገብረየስ የዘውዴን ትከሻውን ይዞ አስቀመጠው። አንገቱን አስረዝሞ ወደ ላይ ሲያየው የነበረው ተሰማም አይኑን እና አንገቱን ወደ ታች ሰበር አድርጎ፤ የተቀመጠውን ዘውዴን ማየት ጀመረ፡፡ ዘውዴ፤

‹‹አምባሳደር የሚሆነው የሀገሩ ዲፕሎማሲያዊ ተወካይ እንጂ ሀገር ውስጥ ቁጭ ብዬ የመንግሥት ተቀጣሪ ሆኜ በማይረባ ደሞዝ የማገለግለው እኔ ዘውዱ አምባሳደር አይደለሁም፡፡ መሆንም አልችልም፡፡›› አለ።

ተሰማ በበኩሉ ለዘውዴ፤ ‹‹ተረጋጋ እንዲህ በትንሹም በትልቁም መበሳጨት እድሜ ከማሳጠር ውጪ ትርፍ የለውም፡፡ ለነገሩ አንተም ሆንክ የትኛውም ኢትዮጵያዊ በሀገራቸው እና በተላኩበት ሀገር መካከል መልካም ግንኙነት እንዲኖር ከሚላኩት አምባሳደሮች በተጨማሪ ሁላችንም አምባሳደር መሆን እንዳለብን አይካድም፡፡›› ሲለው ዘውዴ ንዴቱ ተቶት መሳቅ ጀመረ።

‹‹በእርግጥ አምባሳደሮች በኢትዮጵያ እና በተላኩበት ሀገር መካከል መልካም ግንኙነት እንዲኖር ከመሥራት በተጨማሪ በአካባቢያቸው ስላለው ማንኛውም የፖለቲካ ወይም የኢኮኖሚ እድገት የሀገራቸውን መንግሥት አዘውትረው ማሳወቅ ይጠበቅባቸዋል። ይህንን እየሠሩ ነው? መልሱን ራሳቸው ይመልሱት። እኔ ግን እዚህም ኖርኩ እዛ ያልተሾምኩበትን እኔን አምባሳደር ነህ ብለህ እንደአምባሳደር ሥራ ማለት ለእኔ ከማሾፍ የተለየ አይደለም፡፡›› ሲል አምባሳደር ስላልሆነ የሀገሩ አምባሳደር ሆኖ የመሥራት ግዴታ እንደሌለበት እና ፍላጎት እንደሌለው አስረዳ፡፡

ተሰማ በበኩሉ፤ ‹‹አየህ ከእኛ በላይ ኢትዮጵያዊ የለም ትላላችሁ፡፡ በተቃራኒው ስለሀገራችሁ መናገር እና መሥራት አትፈልጉም፡፡ ሀገር ውስጥ እንደ አምባሳደር ላትታሰብ ትችላለህ፡፡ ወይም አምባሳደር ሆነህ እንድትሠራ ብዙ ግድ ላይሠጥህ ይችላል፡፡ ነገር ግን ሀገር የሚያዋርዱትን ልትገስፅ ይገባል፡፡ በውጭ ስትኖር ደግሞ የበለጠ ‹ስንቅህን በአህያ አመልህን በጉያ› እንደሚባለው ኢትዮጵያዊነት እንዳይዋረድ ገበናችንን መደበቅ ሲኖርብህ በተቃራኒው ገበናችንን በማውጣት ራስን ለውርደት መዳረግ ትክክል አይደለም፡፡ ነገር ግን በተደጋጋሚ ብዙዎች ይህን ሲያደርጉ ይስተዋላል፡፡ አንተም ከሀገር ብትወጣ ያው ነህ፡፡

ሀገር መውደድ ሌላ፤ መንግሥት መጥላት ሌላ ሁለቱም የተለያዩ ናቸው፡፡ ነገር ግን የወቅቱን መንግሥት የጠሉ ሰዎች ለሀገራቸው አምባሳደር ከመሆን ይልቅ በተቃራኒው መንግሥት ይወርዳል ብለው ሕዝብ እንዲተላለቅ የሚሠሩት ሥራ እና የሚያስተላልፉት መልዕክት እጅግ ያሳፍራል፡፡ አንዳንዶች በማኅበራዊ የትስስር ገፅ የሀገር ምስጢርን አሳልፈው እስከመግለፅ ይደርሳሉ፡፡ አሁን አሁንማ አንድ የመንግሥት አካል ለሀገር የሚጠቅም ዜና ሲያበስር ማጥላላትን እንደመልካም ሥራ ወስደውታል፡፡

ቻይናዊ በፍፁም ቻይናን የሚያዋርድ ንግግር አይናገርም፡፡ ሀገር ለማዋረድ አይዳዳውም፡፡ ቢገፋም፤ ቢጨቆንም ችግሩን ዋጥ አድርጎ ችግር የሚፈታበትን መላ ይመታል፡፡ ሲሆን ሲሆን ሀገሩን የሚጠቅም ቴክኖሎጂም ሆነ መረጃ ሰርቆ ለሀገሩ ሕዝብ ኑሮ መሻሻል እና ዕድገት ሚናውን ይወጣል፡፡ አንድ አሜሪካዊ አሜሪካንን ያስቀድማል እንጂ ሌላውን ሀገር አስቀድሞ አሜሪካንን አዋርዶ አይናገርም፡፡

ለአገር መስዋዕት መሆን ቢያቅተን እንኳ እንዴት የሀገራችን ጠላት እንሆናለን? ይህንን በብዙ መልኩ አየዋለሁ፡፡ የትም ብንሔድ መጨረሻችን ሀገራችን ናት። ሀገራችን ብትከበር ለእኛም ክብራችን ነው። ለቱሪዝም የሚመች ሥራ ሲሠራ የቱሪዝሙን ዘርፍ ዕድገት ከማስተጋባት ይልቅ፤ በቱሪዝም ዘርፍ ላይ የተሠራውን ሰበብ እየፈለጉ ማጥላላትን ሙያ አድርገው የወሰዱ ብዙ ናቸው፡፡›› ብሎ አንዳንዶች የሚፈፅሙት ተግባር ፍፁም አንድ ሀገሩን ከሚወድ ሰው የሚጠበቅ አለመሆኑን አስረዳ፡፡

ገብረየስም በበኩሉ፤ ‹‹ አዎ! እኛ ኢትዮጵያውያኖች ሀገራችንን የምንወደው በምላስ እንጂ በተግባር አይመስለኝም፡፡ ምክንያቱም በየማኅበራዊ የትስስር ገፅ የምናሳየው ስለሀገራችን ሕዝብ መልካም ባሕል እና እሴት ሳይሆን ሀገር ውስጥ ስላለው ግጭት አባብሰን ጎብኚ ደፍሮ ሀገር ውስጥ እንዳይመጣ የሚያደርግ ነው። ሐቁን ከመግለፅ ይልቅ ውሸት ላይ እንጠመዳለን።

በአጠቃላይ ጊዜ ወስደው የውሸት ሃሳብ ቀርፀው ኢትዮጵያን ለማጥላላት የሚደክሙ እና ኢትዮጵያዊ ነን ብለው የሚናገሩ ሰዎች መኖራቸውን ማሰብ እጅግ አድካሚ ነው፡፡ አንገትን ደፍቶ በድህነት መኖር እንዲቀጥል፤ ኢትዮጵያ ዘላለሟን በልመና እና በርዳታ ላይ ተንጠልጥላ እንድትዋኝ የሚፈልጉ ስለመኖራቸው መካድ አይቻልም፡፡ ለእኔ እነዚህ ፍፁም ኢትዮጵያዊ አይደሉም፡፡ ስለዚህ እውነተኛ ኢትዮጵያዊ ስለሀገሩ መልካም መልካሙን ያውራ፤ መልካም መልካሙን ያስተዋውቅ ይህ ሲሆን ሀገር ያድጋል፤ ሀገራችንን የፈለግንበት ደረጃ ላይ ማድረስ እንችላለን፡፡ ከድህነት ተላቀን የበለፀገች ሀገር እናደርጋታለን፡፡ ምሬት እና ውሸት ተሸክመን ያንንም ለሌሎች እያሻገርን ከቀጠልን ሀገራችንን እንቀብራታለን፡፡ ሀገር ተቀብራ የሚተርፍ ኢትዮጵያዊ አይኖርም፡፡ ሁሉም ይቀበራል፡፡›› ሲል ኢትዮጵያዊ ነኝ የሚል ከመማረር ይልቅ ለኢትዮጵያ የሚበጀውን ይሥራ ሲል ሃሳቡን ገልፆ የጠጡበትን ለመክፈል እጁን ወደ ኪሱ ከተተ፡፡

# የዘመን ጥበብ

## ዝማኔ እንጂ ቅንጦት አይደለም

**ሙሉጌታ ብርሃኑ**

ኪነ ጥበብ ከጊዜው ጋር እየገሰገሰ መሔዱን ቀጥሏል። የዘመን ጥበብ ከቴክኖሎጂው ጋር እጅና ጓንት ሆነው ቅልጥ ያለ ፍቅር ውስጥ ናቸው ቢባል ስህተት አይደለም። ጥበብ በቴክኖሎጂ ባትወለድም ከጥበብ ውስጥ ያለ ኪነ ጥበብ ግን ከቴክኖሎጂ ጋር ከመተቃቀፍ አልቦዘነም። ድሮ ድሮማ ሁሉም ብርቅ፣ ድንቅ ነበር። ድሮ ድሮማ ሙዚቃ ለማድመጥ መቻል ለግማሽ ምዕተ ዓመት ያህል የራቁትን ወዳጅ ዘመድ ድምፅ እንደመስማት የሚናፍቅ ነበር፡፡ ፊልሞችን ከቴሌቪዥን መስኮት ለማየት መቻል ደግሞ ከህዋ ላይ በአካል ተገኝቶ ቬነስን እንደመመልከት ያለ መታደል ነበር፡፡ "ነው" አላልንም፤ ነው ያልናቸው እልፍ ጉዳዮች "ነበር" እየሆኑ መጥተው በነበር ቀርተዋል። ምስጋና ለቴክኖሎጂው ይግባውና ዛሬ ላይ የማይቻል የለም የምንልበት ጊዜ ላይ ደርሰናል፡፡ ዛሬ ላይ ሙዚቃ ለማድመጥ የፈለገ እንደ ድሮው ዘመን ዝሆንና የዝሆን ልጅ የመሰሉትን ግዙፍ ራዲዮንና የካሴት ክር ፍለጋ መውጣት/መውረድ የለም። ፊልምን ለመመልከት ሽቶ የሰማይ ስባሪ የሚያህለውን ቴሌቪዥንና እንደ ድንጋይ አለት የገዘፈ ማጫወቻ አያስፈልገውም፡፡ በዘመኑ እነዚህ ሁሉ እንደ ብርቅና ድንቅ ቴክኖሎጂ ከታዩ በኋላ ቀጣዩ ጥያቄ የነበረውን የድምፅ እንዲሁም ጥቁርና ነጭ ምስልን አልፎ ዛሬ የደረስንበትን ለመድረስ በሀገራችን ረዥም ጊዜን የፈጀ ነበር፡፡

አብዛኛውን ጊዜ ስለ ኪነጥበብ መውደቅና መነሳት፤ መሔድና መምጣት፤ ስለ ማደግና መቀጨጭ፤ እንዲሁም፣ ምንስ በልቶ ምን ይጠጣ በማለት፤ እያነሳን የማናፈርጣቸው ሀሳቦች የሉም። ስለ ሀገራችን ሙዚቃና ፊልሞች እድገት ካደጉ ሀገራት አኳያ እያነጻጸርን ስናወራ፤ ፊት ለፊት ለዓይን ቅርብ ስለሆኑ ጉዳዮች እንጂ ለእድገቱ ከጎደሉን ነገሮች አንዱ ዓለማት የደረሱበት ቴክኖሎጂ እንደሆነ ግን እምብዛም አናነሳውም፡፡ ስለ እንጀራው እንጂ እንጀራውን ስለምንጋግርበት ምጣድ ግድ ካለን ነገ ላይ እንጀራ ስለመብላታችን እንጃለቱ። የትኛዎቹም ሚዲያዎች (ከግዙፍ የቴሌቪዥን መስኮት እስከ ትስስር ገጾች) በቴክኖሎጂ የተወለዱ የቴክኖሎጂ የአብራክ ክፋይ ናቸው። ቴክኖሎጂ ስንል በኪነ ጥበብ ውስጥ ሦስት አንደምታዎች አሉት። የመጀመሪያው የትኛውም የኪነ ጥበብ ሥራዎች ኢንተርኔትን በመጠቀም ተደራሽነታቸውን ለማስፋት የሚያገለግሉ እንደ ማኅበራዊ ሚዲያና መተግበሪያዎች ያሉ ናቸው። ሁለተኛውና ግዙፉ ደግሞ የሳተላይት ስርጭት የማስተላለፊያ መንገድ ነው። ሦስተኛው ቴክኖሎጂ ከሁለቱ የሚለይ ሲሆን የድምፅና የምስል ጥራታቸው ዘመኑን የዋጀ እንዲሆን የምንጠቀምባቸው ቴክኖሎጂዎች መሆናቸው ነው።

ኪነ ጥበብ ያለ ቴክኖሎጂ፤ ዓሣ ያለ ውሃ እንደ ማለት አይደለም፡፡ ያለ ቴክኖሎጂ መሥራት ይቻላል፤ ያለ ቴክኖሎጂ ማደግ ግን የማይወጡት ዳገት ነው። ስለ ቴክኖሎጂው ስናነሳ ከእጅ ወደ አፍ ለመሰሉ እዚሁ በዚሁ ለሆኑ ኪነ ጥበባዊ ሥራዎቻችን ሳይሆን ኪነ ጥበብን በመጠቀም በራሱ በኪነ ጥበብ፤ እንዲሁም በማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮቻችን የተጫኑብንን ቀንበሮች ሰባብረን ወደ ዓለም አቀፉ አደባባይ መውጣት እንድንችል ነው፡፡ የነገሩ ወሳኝነት የገባቸው ሀገራት የኪነ ጥበብ ዘርፎቻቸውን ለዓለም ገበያ በማቅረብ ጥፍጥናውን በማጣጣም ላይ ናቸው። ትምህርት ቤቶችን በመክፈትና ዘመኑን የዋጁ የቴክኖሎጂ ግብዓቶችንም በተመቻቸ ሁኔታ በማስገባት ባገኙባቸው ቀዳዳዎች ሁሉ ወደ ዓለም ገበያ ይተማሉ። ወደ እኛ ስንመጣ ግን መልኩ የቅንጦት ነው የሚመስለው። ለዚህ ወሳኝ የሆኑ እንደ ካሜራና መሰል ያሉ ለምስልና ድምጽ ቅጂ የሚያገለግሉ ቁሳቁሶች እንኳን ከውጭ ወደ ሀገር ውስጥ ሲገቡ የሚጣልባቸው ቀረጥ የዱላ ያህል የሚፈነክት ነው። ኪነ ጥበብ የሀገርን ገጽታ ከመገንባትም ባሻገር ኢኮኖሚውን ተሸክሞ የመሮጥ አቅም እንዳለው ዘንግተን ይሁን ችላ ብለን፤ ከመንግሥት ጀምሮ ትኩረትን በመነፈጉ፤ "አላደገም" ከሚል ትችት በስተቀር ምን ይሆን የሚያስፈልገው የሚለውን መጋረጃ ገልጠን ጓዳውን አንመለከትም። አሁን አሁን በኪነ ጥበቡ ምን ልሥራ ከማለት ይልቅ በምን ልሥራ ሆኗል ትልቁ ጉዳይ። እንደ ግለሰቦች ብቻም ሳይሆን እንደ ሀገርም የቴክኖሎጂውን ጉያ የሚኮረኩር ነው። ገና ለገና ኪነ ጥበብ "መዝናኛ ነው" ብለን እንደ ቅንጦት ከተመለከትነው ቅንጦት ብቻ ሆኖ ይቀራል፡፡ ካወቅንበትስ ቅንጦት አይደለም። ከቴክኖሎጂው ረገድ ብቻም ሳይሆን በሁሉም ነገር ኪነ ጥበብ በሀገራችን፤ የጀርባ አጥንት ተደርገው ከሚቆጠሩት እንደ አንዱ ዘርፍ ቢታይ፤ ካሉን የታሪክ የብሶች አንጻር የኢትዮጵያን ምሰሶ የምናቆምበትን ኃይል ለማመንጨት እንችል ነበር፡፡ ሆሊውድና ቦሊውድን እንኳን ብንመለከት በጊዜው በብዙዎች ጥረት በሁለት እግራቸው እንዲቆሙ ተደርገው ዛሬ ላይ የሀገራቸው ዋልታና ማገር ለመሆን የበቁ ናቸው፡፡

ኪነ ጥበብ ጓዙን ጠቅልሎ ወደ ቴክኖሎጂው ገብቷል፤ እንደኛም በመግባት ላይ ነው፡፡ ታዲያ ጥበብ እያበበች ወይንስ እየረገፈች ነው? አንዳንድ ፍካት፤ አንዳንድ ድርቀት፤ በድምሩ ሞትና ሕይወትን ታቅፋለች። የቴክኖሎጂው ፍሬ በሀገራችን በጥቂቱ እየተበተነ ብዙ መልካም ነገሮችን መፍጠሩ እንዳለ ሆኖ በሌላ በኩል ግን ቲያትር ቤቱን አስቦዝኖታል፡፡ ዓለም በቴክኖሎጂ ሰተት ብላ ወደ ቤታችን ገባችና ከውጭ ያሉ ጉዳዮችን ፍለጋ ለመውጣት አስንፋናለች፡፡ በአንድ የእጅ ስልክ ዓለምን ከጫፍ እስከጫፍ እናዳርሳለን። ገዝተን ከቤታችን ባስገባነው ቴሌቪዥን በሀገርና በውጭ የተሠሩ ልዩ ልዩ የመዝናኛ ዘርፎችን በአንዲት ሪሞት ብቻ ምርጫና ፍላጎታችንን እንዘውራለን፡፡ እናም የቲያትር ተመልካቹም ከዚሁ ተሟሙቆ ወደ ቲያትር ቤት መሔዱን ዘንግቶታል፡፡ ዛሬ ቴክኖሎጂው በበዛበት ዘመን ጥበብ ፊቷ ገርጥቶ፤ አጥንቷ ገጦ መለመሏን ቀርታለች በማለት የድሮው ዘመን የተሻለ ስለመሆኑ የሚናገሩ ብዙ ናቸው። በርግጥ "ውሸት ነው" ለማለት ባያስደፍርም፣ ቴክኖሎጂው ያደበዘዘው ኪነ ጥበብን ሳይሆን ኪናዊ ማንነትን ነው። ከቴክኖሎጂ በፊት ኪነ ጥበብ በጥበብ መሬት ላይ ነበረች፤ ማለትም አፍቃሪዎቿን የምታገኘው በገጽ ለገጽ ነበር። በጥቂት ነገር ለጥቂቶች ብቻ ተመጥኖ ይቀርባል። ከብዛቱ ጥራቱ እንልም የለ?፤ የሚቀርቡትም እኛኑ የመሰሉ ጉዳዮች ናቸው። አሁን ግን በሁለት ነገሮች አሉታዊ መልክ ተጎናጽፏል፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ፣ በቴክኖሎጂው አማካኝነት ተደራሽ እየሆኑ ያሉት የኪነ ጥበብ ሥራዎች ተደራሲያኑን ያማከለ አይደለም፡፡ በዚህም ምክንያት አስፈላጊ የሆኑ የእድሜም ሆነ ሌሎች ገደቦችን ተግባራዊ ለማድረግ አይቻልም፡፡ በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ አድማጭ ተመልካቹ፤ እንዲሁም፣ አንባቢያኑ ዓለማቀፋዊ እየሆኑ ሲመጡ፤ ለሁሉም የሚመጥንና አካታች የሆኑ ይዘቶችን ለመፈለግ ስንዳክር ከታች ያሉ ብዙ ነገሮችን አንመለከታቸውም፤ ወይንም፣ ጥቃቅን እየመሰሉን እናልፋቸዋለን፡፡ በሁሉም ዓይንና ጆሮ ለመግባት ስንል ከዚህም ከዚያም ስንቃርም ደግሞ ቀደም ሲል የነበረውን እንበርዘውና አጠገባችን ላለው ማኅበረሰብ ወይኑን ሆምጣጤ እናደርግበታለን፡፡ ለአብነት ያህል የሀገራችንን ሙዚቃ ድሮና ዘንድሮ ብንል፤ ሙዚቃና ሙዚቀኛ በየአይነቱ እየፈላ በተራቀቀ የቴክኖሎጂ ቅንብሮች የተንበሸበሸበትን ዘመን፤ አብዛኛዎቻችን ግን አጣጥለን ሙዚቃማ ድሮ ቀረ በማለት፤ ከአድማጩ ሙዚቀኛው በበዛበት በዚህ ጊዜም፤ ሙዚቃ ሞልቶ ሙዚቃ ጠፋ እንላለን፡፡ የምንለውም እንደ ድሮው በእኛ የማንነት ልክ ተሰፍሮ ባለመሠራቱ ነው። ከማኅበራዊ ሚዲያዎች አንስቶ እስከ ግዙፍ ኢንዱስትሪዎች ያሉት ከየዓለም ዳርቻው በገፍ ከሚለቁብን የራሳቸው ማንነት አንጻር፤ ከማየትም አልፎ የኛም ጭምር አድርገን ስለተቀበልናቸው ነው፡፡ በቴክኖሎጂው ወደ አንድ መንደርነት እየተቀየረች ባለችው ዓለም ውስጥ ጥያቄው "የማን መዝሙር ይዘመር?" የሚል ሆኗል። ብዙ የያዝን እኛ በሁሉ ጠንክረን መቆም ካልቻልን፤ ጥቂት ይዘው በቴክኖሎጂው ኃይል በየጆሮዎቻችን በሚጮሁት መዋጣችን አይቀርም። ዓለም አንድ ሆና ለቡና ለመጠራራት በደረሰችበት በዚህ ዘመን፤ የኛ የሆኑት የጥበብ አፍቃሪያን እንኳን በቴክኖሎጂ የበለጸጉ የኪነ ጥበብ ሥራዎችን በሚፈልጉት ልክ ከኛ ማግኘት ካልቻሉ፤ ፊታቸውን ወደ ውጭ በማዞር ሌላኛው ፈተና ይጋረጥበታል።

መሰላሉን ከረገጥን አይቀር በዚሁ ተንደርድረን ወደ ሌላኛው ደረጃ እንሻገር። ሀገራችን ኢትዮጵያ ከቴክኖሎጂ አንጻር ገና በአፍላነት እድሜ ላይ እንደመሆኗ በዚያ

> **አንባቢያኑ ዓለማቀፋዊ እየሆኑ ሲመጡ፤ ለሁሉም የሚመጥንና አካታች የሆኑ ይዘቶችን ለመፈለግ ስንዳክር ከታች ያሉ ብዙ ነገሮችን አንመለከታቸውም፤ ወይንም፣ ጥቃቅን እየመሰሉን እናልፋቸዋለን**

ዘመን ከማንም በላይ የነበራት እምቅ የኪነ ጥበብ ሀብት በዓለም ተወዳዳሪ እንዳይሆን አግዶታል። እየሞተ ያለ የመሰለንም ብዙዎች ጥቂት ይዘው ወደ ፊት ሲገሰግሱ፤ ብዙ የያዝን እኛ የቅንጦት እየመሰለን ባለንበት በመቆማችን ነው። ኪነ ጥበብን በቴክኖሎጂ ስንቃኘው ሀሳቡ ለሁሉም የኪነ ጥበብ ዘርፎች የሚሆን ቢሆንም በዋናነት ግን በፊልምና ሙዚቃዎቻችን ዙሪያ የሚያንዣብብ ነው የሚሆነው፡፡

ያሉንን እምቅ የኪነ ጥበብ ሀብቶቻችንን በቴክኖሎጂው ደግፈን ወደ ዓለም መድረክ ካወጣናቸው ባሕል፣ ኢኮኖሚ፣ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ እሴቶቻችን ከፍ በማድረግ ዓለም ፊቷን ወደኛ እንድታዞር ብቻም ሳይሆን ዓለምን መዘወር እንችላለን፡፡ ከመሳጭነቱ የተነሳ የሰው ልጆችን አዕምሮና ሥነልቦና በቀላሉ የመግዛትና የመቆጣጠር ኃይል አለው፡፡ ከኪነ ጥበብ አንዲቷን ሰበዝ መዘን በፊልሙ ዘርፍ ብንመለከት፤ ለዚህ ማሳያ የሚሆን እንደም እንኳን በአሜሪካ የለም፡፡

የአሜሪካ ኃያልነት የመጣው መች በሥራዋ ብቻ ሆነና፤ ለዚህ መብቃቷ ባላት ኢኮኖሚና ደረቅ ፖለቲካም ብቻ አይደለም፡፡ ይልቅስ የፊልም ኢንዱስትሪው የጀርባ አጥንቷ ነው፡፡ እሷም ብትሆን "እድሜ ለፊልሞቼ" ትበል እንጂ። ልታደርጋቸው የምትሻቸውን ነገሮች አስቀድማ ለዓለም የምትናገረው በፊልሞቿ ነው፡፡ ፊልሞቿ ሁሉ ያላትን የቴክኖሎጂ ጥበብ፣ ዘመናዊ የጦር መሣሪያ፣ የኢኮኖሚና የፖለቲካ አቅሟን በፊልሞቿ በኩል በማሳየት ዓለምን ጸጥ እረጭ ለማድረግ የምትጠቀምበት ማስፈራሪያዋም ጭምር ነው፡፡ ብዙ ጉዳዮቿም ምናባዊ ናቸው፤ ገና ለዛሬ ሀምሳና ስድሳ ዓመት ያላትን ምኞት ልክ ዛሬ ላይ የደረሰችበት ያህል አድርጎ ገጽታዋን በመገንባት እንደ ቆንጆ ኮረዳ ዓለምን ሁሉ ታማልልበታለች። አንዳንዴም፤ እሷ ሚያው! ብትል ፊልሞቿ ግን እንደ አንበሳ ስታጓራ ያለውን የሚያንቀጠቅጥ ድምፅ ከተቆጣ ፊቷ ጋር አድርገው እያሳዩ ብራቅ መስላ እንድትፈራ በማድረግ፤ የጌቶቹ ጌታ ስለመሆኗ እየነገሩ ያሳምኑናል። ዓለም በማየት የተሞላች ናትና ገጽታ ግንባታ ለሀገር ወሳኙ ነገር ነው፡፡ ኪናዊ የሆነ ፕሮፖጋንዳ ምን ያህል ወሳኝ እንደሆነ እንገነዘብበታለን፡፡

የፊልሙ ዘርፍ ብዙ ነገሮችን የተነፈገ ቢሆንም ባለቤት አልባ ሆኖ መሰንበቱ ደግሞ ሌላ እራስ ምታት ነው። ሌላው ቀርቶ የእይታ ጊዜያቸውን ጨርሰው ከሲኒማ ሲወርዱም ቀጣይ መዳረሻቸው ከፊልም ቤቶች የዘለለ አልነበረም፡፡ ከእኛ ለእኛ ብቻ ሆኖ በቂ ገንዘብና እውቅና የሚያስገኙም አልነበሩም። በዓለም ላይ የተለያዩ የፊልምና መሰል ኢንዱስትሪዎች ገቢያቸው ከሲኒማዎቻቸው ብቻ ሳይሆን በዋናነት ለዓለም አቀፉ ተመልካቾቻቸው ከሚያደርሱባቸው ከእነዚሁ የቴክኖሎጂ መንደሮቻቸው ነው። አሁን አሁን ዘግየት ብሎም ቢሆን ከወደ እኛም የተሻሉ ነገሮችን ለማየት እየቻልን ነው፡፡ በጥቂቱም ቢሆን የሀገራችንን ኪነ ጥበብ ለማስተዋወቅ የእድል በር ከከፈቱልን የሚዲያው ቴክኖሎጂዎች መሐከል የዩቱብን ውለታ አንዘነጋውም። ቅሉ የጥበብ ሥራው ባለቤቶች የሚንቀሳቀሱበት በተናጠል ቢሆንም፡፡

በፊልሙ ዘርፍ በተናጠል እየተደረጉ የነበሩ እንቅስቃሴዎች ውጤት በድምሩ አሁን ደግሞ ሌላ የተሻለና የዓለም አቀፉን በር ለኢትዮጵያ ፊልሞች የሚከፍተውን እድል አስገኝቷል፡፡ ከሁለት ዓመታት ወዲህ በተለይ በአሁኑ ሰዓት በውጭ ሀገራት የሚገኙ፤ በፊልም ኢንዱስትሪው የሚሠሩ ድርጅቶች ፊታቸውን ወደ ኢትዮጵያ በማዞር ላይ ናቸው፡፡ ሸሚዛቸውን እየጠቀለሉ እጃቸውን ለማስገባት መዳዳታቸውም፤ የኢትዮጵያ ፊልሞች ተወዳጅ እየሆኑ ከመምጣታቸውም ባሻገር ያለንን ሀብት መገንዘባቸውን የሚያሳይ ነው። ከእነዚህም አንዱ ከሁለት ዓመታት በፊት ድርጅቱን ከፍቶ መሥራት የጀመረው የፈረንሳዩ ካናል ፐላስ አንዱ ነው፡፡ ከሀገራችን የተመራረጡትን፣ የኛ ብቻ የሆኑ ፊልሞችን የዓለም አቀፍና ሰፊ የስርጭት ሽፋን ባለቤት በሆነው በዲኤስቲቪ ያሳያል፡፡ በአሁኑ ሰዓት ፈቃድ አግኝቶ በዋናነት እየሠራ ያለው የፊልም ተቋም ካናል ፐላስ ይሁን እንጂ፤ በኢትዮጵያ ፊልሞች ፍላጎት ያደረባቸው በርካታ የውጭ ድርጅቶች ወደ ኢትዮጵያ ፊልም ፕሮዲዩሰሮች ማኅበር ጎራ ማለታቸው አልቀረም።

በሙዚቃው ስንመለከት ደግሞ ከአድማጭ ተመልካቹ ይልቅ ለሙዚቀኞቹ ገዘፍ ያለ ተጠቃሚነትን የሚያረጋግጡ ልዩ ልዩ መተግበሪያዎች ተፈጥረዋል። ሀገር በቀል ሆነው ዛሬ ላይ ሙዚቃውን በባለቤትነት ከመምራትም፤ ነገ ላይ ከፍ ወዳለ ኢንዱስትሪ የማደግ ተስፋንም የሰነቁ ናቸው፡፡ በአሁን ሰዓት በሀገራችን እየሠሩ ካሉና የዚህ ዓይነቱ መተግበሪያ ባለቤት ከሆኑት፤ የሰዋሰው መልቲሚዲያ በዋናነት ተጠቃሽ ነው። በእነዚህ ሁለት ዓመታት በተለይም ከአንድ ዓመት ወዲህ ከበርካታ ሙዚቀኞች ጋር የስምምነት ውል በመፈጸም አጋሩ አድርጓቸዋል። ስምምነት የፈጸሙ እነዚህ ሙዚቀኞችም አዳዲስ የሙዚቃ ሥራዎቻቸውን የሚያስረክቡት መተግበሪያውን ለሚያስተዳድረው ተቋም ብቻ ይሆናል። ተቋሙ ለሙዚቀኞቹ ክፍያውን የሚፈጽመው፤ አስቀድሞ ሥራውን በመግዛት፣ አሊያም በሥራው ተወዳጅነትና በሚያስገኘው የገቢ መጠን ተሰልቶ እንደስምምነታቸው ሊሆን ይችላል። ዓለምን ለመድረስ የሚችሉ እንዲህ አይነቶቹም ቴክኖሎጂዎች ግሩም ናቸው፡፡ በብዙ የድኅነት ችንካር ተቸንክረን በቴክኖሎጂ መበልጸግ ስላለበት የኪነ ጥበብ ዘርፍ ማውራት ቅንጦት አይደለም፤ ረሃባችንን የምናስታግስበት መድኃኒት እንጂ። ያውም ብዙዎች ለመሻማት የሚሯሯጡለት የታሪክ ሀብት ይዘንማ እንዴትስ ስለቅንጦት መስሎ ይሰማን . . . ቅንጦት አይደለም፤ የዘመን ጥበብን አዘምኖ ከዘመኑ ዓለም ጋር ስለመሔድ ነው፡፡

ማህበራዊ

# ልዩ ልዩ

## ‹‹ነገን አብረን እንሳል›› ሠዓሊ ዓለም ጌታቸው

**እየሩስ ተስፋዬ**

አካል ጉዳተኛ እንደ መሆኗ የሌሎች አካል ጉዳተኞችን ሕይወት ጠንቅቃ ታውቀዋለች። የእርሷ ሕይወት በብዙ ፈተና ያለፈ ቢሆንም ስለፈተናዎቹ ከመናገር ይልቅ ሰርቶ ማሳየትን ትመርጣለች፡፡ ለሌሎች ለመትረፍ እና የአስተሳሰብ ለውጥ መምጣት አለበት በሚል ቅን ሃሳብ ብርቱ ጥረቷን ቀጥላበታለች - ሠዓሊ እና መምህርቷ ዓለም ጌታቸው፡፡ ሠዓሊዋ፣ ‹‹ዓለም ጋለሪ እና ቡና›› ብላ በከፈተችው የሥነ ጥበብ ማዕከል ታዳጊ ልጆችን እና ፍላጎቱ ላላቸው ሰዎች ሥዕል ታስተምርበታለች። ቡና፣ ሻይ ... ለሚፈልጉትም ማዕከሉ ክፍት ነው፡፡

ማዕከሉ ከተመሰረተ 14 ዓመታትን አስቆጥሯል። እስካሁን ድረስ ከአራት ሺህ በላይ፣ ዕድሜያቸው አራት ዓመት የሞላቸውን ጨምሮ፣ በርካታ ታዳጊዎችን ሥዕል ማስተማር ችሏል፡፡ ወደ ጋለሪው ሲገባ የተሰቀሉ የተለያዩ መልዕክት ያላቸውን ሥዕሎች ቡና እና ሻይ እያሉ እንደልብ መመልከት ይቻላል፡፡ ወደ ጋላሪው ለሚመጡ ወጣቶችም ይሁን ተገልጋዮች ‹‹ምን ይምጣላችሁ? ሻይ ወይስ ቡና?›› የሚለውን ትዕዛዝ ከተቀበሉ በኋላ የማይቀር ጥያቄም አለ፡፡ እርሱም ‹‹መጽሐፍ ማንበብ? ወይስ ሥዕል መሳል?›› የሚል ነው፡፡ ሥዕል (ባይችሉ እንኳን መሞኮር) አልያም እያነበቡ ሻይ ቡና ከማለት ውጭ ተሰብስቦ ያለ ሥራ መቀመጥ በፍጹም የተከለከለ ነው፡፡ ለዚህም በየጠረጴዛዎቹ ላይ ሥዕል ለመሳል የሚያግዙ ቀሳቀሶች ተቀምጠዋል፡፡ ማንበብ ፍላጎታቸው ለሆኑት ደግሞ አዲስ ዘመን ጋዜጣ፣ የተለያዩ ይዘት ያላቸው መጻሕፍትም ዝግጁ ናቸው።

ትውልድን ለመቅጽ እና ለማፍራት እንዲሁም ለየትኛውም ነገር ራሳቸውን ተጠያቂ እንዲያደርጉ ኃላፊነትን የሚሰማው መልካም ትውልድ እንዲመጣ እርሷ እና ሌሎች መምህራኖች በሥራ ላይ ናቸው፡፡ ሀገር ያለችው ልጆች ላይ ነውና በሥነ ምግባር ተኮትኩተው እንዲያድጉ እና ስለ ሀገራቸው ገጽታ በሚገባ እንዲረዱ ለማድረግም የልጆች መጻሕፍትንት ትጽፋለች፡፡

አንዳንዶቹ ወደ ጋለሪው ሥዕል ለመግዛት ፈልገውም ይሁን ልጆቻውን ሥዕል ለማስተማር ሲመጡ ድንገት እርሷ ብቻ ሆና በዊልቸር ስትንቀሳቀስ ያዩት ‹‹ሰው የለም እንዴ?›› ብለው መጠየቃቸውን ያስታወሰችው ሠዓሊዋ እና መህርቷ ዓለም፤ ከቅያሜ ይልቅ ይህ አንዱ የአስተሳሰብ ችግር መሆኑን በማስገንዘብ አጋጣሚውን ተጠቅማ ታስተምርበታለች፡፡



እንደ ሠዓሊዋ ማብራሪያ፤ ዓለም ጋለሪ ከሥነ ጥበብ ጋር በተያያዘ በርካታ ሥራዎችን ይሠራል። ወጣቶች ጊዜያቸውን አልባሌ ቦታ ከማሳለፍ ይልቅ መጥተው ሥዕል እንዲስሉ ያበረታታል፡፡ ያላቸውን ሰዓት አብቃቅተው መጻሕፍት ያነባሉ። ማዕከሉ የእውቀት መገኛ ቦታ በመሆኑ፣ ሰዎች መጥተው የአእምሮ ምግብ የሚያገኙበት ሥፍራ ለመሆን በቅቷል፡፡

ሌላው ነገር አካል ጉዳተኞች ጥሩ አስተሳሰብ ያለው ማሕበረሰብ ካልገጠማቸው ከአካላቸው ይልቅ አእምሯቸው እጅጉን ይጎዳል፡፡ ከባዱ ችግርም ሆነ ጉዳት ይህ ነውና።

ሠዓሊዋ ‹‹አብረን›› የተባለ ምግባረ ሠናይ ድርጅት መሥርታለች፡፡ ድርጅቱ አካል ጉዳተኞችን ለማሰልጠን፣ ተምረው የአንድ ሞያ ባለቤት ሆነው ራሳቸውን እንዲችሉ የማድረግ ዓላማ ያለው ነው። እስካሁን ድረስም ከ40 በላይ አካል ጉዳተኞችን አሰልጥሎ በማእከሉ እና በሌሎች ቦታዎች ለሥራ ማብቃቱን ታስረዳለች፡፡

በተደጋጋሚ አፅንኦት ሰጥታ እንደምትናገረው፣ ማዕከሉ በተለይ በተለይ አስተሳሰብ ላይ ይሠራል። የአስተሳሰብ ሕክምናም ያደርጋል፡፡ አካል ጉዳተኞች ላይ ያለውን የአስተሳሰብ ችግር ለመቅረፍ ወደ ተለያዩ ተቋማት በማቅናት፤ እንዲሁም የሻይ ሰዓትን ብቻ በመጠቀም አስተሳሰብ ላይ የበለጠ ለመሥራት እቅዷ እና ፍላጎቷ እንደሆነ ትናገራለች።

ዓለም የምትሠራቸው ሥራዎች አብዛኞቹ ከሥነ ጥበቡ ጋር የተያያዙ ናቸው፡፡ በቅርቡ ደግሞ በሀገራችን ለመጀመሪያ ጊዜ 50 ተፅዕኖ ፈጣሪ አካል ጉዳተኞች የሚያቀርቡት ‹‹ነገን አብረን እንሳል›› የተሰኘ የሥዕል ዓውደ ርዕይ ለማዘጋጀት እርሷና ጓደኞቿ ሽር ጉድ እያሉ ይገኛሉ፡፡ ከእነዚህ ተፅእኖ ፈጣሪ አካል ጉዳተኞች መካከል አንጋፋ መምህራን፣ ጋዜጠኞች፣ የሕግ ባለሙዎች፣ ሠዓሊያን፣ የህክምና ባለሞያዎች፣ በመንግሥት ሥራ በኃላፊነት ደረጃ ላይ ያሉ ኃላፊዎች እና ሌሎችም ተሳትፈውበታል። እነዚህ የራሳቸውን ድርሻ እየተወጡ ያሉ አካል ጉዳተኞች ስራዎቻቸውንም ያቀርባሉ፡፡

50ዎቹ የሀገር ባለውለታዎች ብዙ ችግሮችን ተጋፍጠው ለዛሬ በቅተዋል፡፡ ‹‹አሁን በትንሹም ቢሆን ይሻላል፡፡›› በማለት ከአካል ጉዳተኞች ጋር ተያይዘው የሚነሱ ችግሮች በትንሹም ቢሆን ከትናንት ዛሬ እንደሚሻል ያመላከተችው ሠዓሊዋ፤ አገራቸውን ለረዥም ዓመታት ያለገሉ መሆናቸውን ከግንዛቤ በማስገባት ለእነርሱ እውቅና መስጠት እና ማበረታታት እንደሚገባ በማመን ዓውደ ርዕዩን ለማዘጋጀት አስፈልጓል፡፡

ሀገራችንን ጨምሮ ሕይወታችን በእጃችን ነው ያለው፡፡ ከችግራችን ይልቅ ያለን ነገር ብዙ ነው። ስለዚህ እነርሱን ነገሮች እናጉላቸው በሚል ሃስብ ሰዓሊ ከሆኑት ውጭ ያሉ አካል ጉዳተኞች ሃሳባቸው ተጠይቆ በሸራ እና በቀለም እንዲያሰፍሩ በማድረግ ከሠዓሊያኑ ውስን ድጋፍ ተደርጎላቸዋል፡፡ በዕለቱም ማስተላለፍ የፈለጉት ሃሳብ ላይ ገለፃ እንዲሰጡ ይደረጋል፡፡

ከዓውደ ርዕዩ በተጨማሪም የእነዚህ 50 ተፅዕኖ ፈጣሪ አካል ጉዳተኞች ግለ ታሪካቸው ተሰንዶ በመፅሐፍ መልክ በማዘጋጀት በችግር ውስጥ አልፈው ሀገራቸውን እንዴት እያገለገሉ እንደሆነ ለማሳየት እየተሠራ ነው፡፡ አሁን ላይ በተለያዩ ሁኔታዎች ውስጥ ላለው ትውልድ ከማስተማር በሻገር፣ ብቁ አካል ጉዳተኞች መኖራቸውን ግንዛቤ ለመስጠት ያስችላል፡፡ ለውጥ ማምጣት የሚቻለው ከራስ ጀምሮ ሲሠራ እና ራስን በማነሳሳት እንደሆነ የምትናገረው ሠዓሊዋ፣ እጅን ወደ ሌላ አካል መጠቆም እንደማይገባ ለማስተማር ያግዛል ባይ ናት።

ማዕከሉ የትውልድ ማዕከል ነው፡፡ በውስጡ ትምህርተ ቤት፣ ጋለሪ፣ የሀሳብ መድረክ የሚካሄድበት ዓለም ዓውደ ሃሳብ፣ የቤተ መጽሐፍት እና የበጎ አድራጎት አገልግሎት የሚሰጥ ማዕከል ነው፡፡ ይህንን ታሳቢ በማድረግ ወደ አንድ ማዕከል በማምጣት እና ሁሉም ሰው ተሰባስቦ የሚገለገልበት ቦታ እንዲሆን ለማድረግ ግን የመንግሥት ድጋፍን ትሻለች፡፡

# ዓለም አቀፍ

## ኢኳዶር ከአደንዛዥ ዕጽ አዘዋዋሪዎች ጋር ለምታደርገው ትግል የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ አወጀች

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

በኢኳዶር አንድ ሞገደኛ የአደገኛ ዕጽ ሰንሰለት መሪ ከፍተኛ ጥበቃ ከሚደረግለት እስር ቤት ካመለጠ በኋላ በሀገሪቱ ከፍተኛ ውጥረት ሰፍኗል። ችግሩን ተከትሎ የሀገሪቱ ፕሬዚዳንት ዳንኤል ኖቦዋ አስቸኳይ ጊዜ አውጀዋል።

አዋጁ የሚቆየው ለ60 ቀናት ነው። የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ በየቀኑ ከሰዓት እላፊ ገደብ ጋር እንደሚተገበር ፕሬዚዳንቱ ተናግረዋል።

የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁን በተመለከተ ፕሬዚዳንት ኖቦ በኢንስታግራም ገጻቸው ላይ በለቀቁት ቪዲዮ አሸባሪዎች ካሏቸው የአደንዛዥ ዕጽ አዘዋዋሪዎች ጋር በሚደረገው ውጊያ ተግባራቸውን ለመወጣት “ሁሉንም የፖለቲካ እና የህግ ድጋፍ” ለወታደራዊው ኃይል እንደሚሰጣቸው ተናግረዋል።




እስከ አሁን በሀገሪቱ እስር ቤቶች በተነሳ ነውጥ 10 ሰዎች ተገድለዋል። የኢኳዶር ጎረቤት የሆነቻው ፔሩ የፖሊስ ኃይል ወደ ድንበር አስጠግታለች። ይህም የሆነው ነውጡ ወደ ሀገሯ እንዳይሸጋገር በመስጋት ነው።

አሜሪካ በኢኳዶር የተነሳውን አመጽ ያወገዘች ሲሆን ለኢኳዶር ፕሬዚዳንት ማንኛውም እርዳታ እንደምታደርግ ይፋ አድርጋለች።

ኢኳዶር የዓለማችን ከፍተኛ ሙዝ ላኪ ሀገር ናት። ከሙዝ ሌላ ነዳጅ፣ ቡና፣ ኮኮዋ፣ ሽሪምፕ እና የዓሣ ምርቶችን ወደ ውጭ ትልካለች።

በኢኳዶር የአደገኛ ዕጽ ነጋዴዎችና አዘዋዋሪዎች በሀገሪቱ አለመረጋጋትን በተደጋጋሚ ይፈጥራሉ። ወደ አውሮፓና አሜሪካ የሚላኩ የኮኬይን ዕጽ ለመቆጣጠር በሚደረገው ሽኩቻ ሀገሪቱ ሰላም ስታጣ ይህ የመጀመሪያው አይደለም።

ሰሞኑን በቴሌቪዥን ስቱዲዮ በነበረው እገታና ጥቃት አንድ ጭምብል የለበሰ ታጣቂ ሽጉጥ በጋዜጠኛ ላይ ደግኖ ይታይ ነበር። ሌላ ታጣቂ ደግሞ ፕሬዚዳንቱ ጣልቃ እንዳይገቡ ለማሳሰብ እፈልጋለሁ ቅረጹኝ እያለ ሲጠይቅ ነበር።

አንዲት ሴት ደግሞ “እባካችሁ አትተኩሱ’ እያለች ስትማጸን በቀጥታ ተላልፏል። አንድ ሌላ የቴሌቪዥን ሠራተኛ ለኤኤፍፒ በዋትስአፕ ባሾለከው መረጃ “ሊገደሉን መጥተዋል። እዚህ ስቱዲዮ ነው ያሉት። ፈጣሪ ሆይ አድነን። ወንጀለኞቹ በቀጥታ ሥርጭት ላይ ናቸው” ሲል መልእክት ልኮ ነበር።

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ የሀገሪቱ እስር ቤቶች ውስጥ የአደገኛ ዕጽ አዘዋዋሪ አደገኛ ቦዘኔዎች አስነሱት በተባለ ነውጥ በርካቶች ተገድለዋል። ነውጦቹ ብዙውን ጊዜ በአደገኛ ዕጽ ቡድኖች መካከል የሚነሱ ናቸው።

ኮኔሮስ የሚባለውና የኢኳዶር አደገኛ የዕጽ አዘዋዋሪ ቡድን እንደሆነ የሚነገርለት ኃይል በሀገሪቱ ለሚነሱ አመጾች ዋንኛው ተጠያቂ ይደረጋል።

ፊቶ በሚል ስም የሚታወቀው የቡድኑ አደገኛና ሞገደኛ መሪ ጥብቅ ጥበቃ ከሚደረግለት እስር ቤት ማምለጡን ተከትሎ ሁለት የከርቸሌው ጠባቂዎች ምናልባት እንዲያመልጥ ሳይረዱት አይቀሩም በሚል በቁጥጥር ሥር ውለዋል።

ፊቶ ከ2011 ጀምሮ በተደራጀ ወንጀል፣ በአደንዛዥ ዕፅ አዘዋዋሪነት እና በግድያ ወንጀል የ34 አመት እስራት ተፈርዶበት ነበር።

ከማረሚያ ቤት ሲያመልጥ የአሁኑ ለሁለተኛ ጊዜ ሲሆን እ.ኤ.አ. በ 2013 ከማረሚያ ቤት አምልጦ ከሶስት ወራት በኋላ እንደገና ተይዟል፡፡

በሺዎች የሚቆጠሩ የጸጥታ ኃይሎችን ባሳተፈ ኦፕሬሽን ፊቶ ባለፈው ነሃሴ የፕሬዚዳንት እጩ ፌርናንዶ ቪላቪሴንሲዮ መገደሉን ተከትሎ ከፍተኛ ጥበቃ ወደሚገኝ እስር ቤት ተዘዋውሮ ነበር፤ ይሁንና ዳግም አመለጠ።

የፊቶ ማምለጥ ለወጣቱና አዲሱ ፕሬዚዳንት መጥፎ ዜና ሆኗል። ፕሬዚዳንቱ በኢኳዶር የአደገኛ ዕጽ ሰንሰለትን እበጣጥሳለሁ ብለው ቃል ገብተው ነበር በቅርብ ጊዜ ወደ ሥልጣን የመጡት።

በዚህ የፕሬዚዳንቱ ምርጫ እጩ የነበሩትና ከፍተኛ የማሸነፍ ግምት የተሰጣቸው ፈርናንዶ ቪላቪሴንሲዮ በታጣቂ መገደላቸው አይዘነጋም።

ፈርናንዶ ቪላቪሴንሲዮ ከዚህ ፊቶ ከሚባለው ሞገደኛ አደገኛ ቦዘኔ የሞት ዛቻ በደረሳቸው በማግስቱ ነበር የተገደሉት።

በተያያዘ ጭንብል ያጠለቁ ታጣቂዎች በኢኳዶር ስቱዲዮ ሰብረው ሲገቡ በቀጥታ ስርጭት ላይ የነበሩ ጋዜጠኞችና የቴክኒክ ባለሙያዎችን ማገታቸውን ቢቢሲ ዘግቧል።

በቀጥታ ሥርጭት ላይ የነበሩ ጋዜጠኞችና ሌሎች የቴክኒክ ባለሙያዎች በታጣቂዎቹ የታገቱት ለአጭር ሰዓት ነው። ፖሊስ የታገቱትን የስቱዲዮ ባለሙያዎችንና ጋዜጠኞችን በሙሉ አስፈትቻለሁ፤ 13 ተጠርጣሪዎችንም በቁጥጥር ሥር አውያለሁ ብሏል።

ኢኳዶር በደቡብ አሜሪካ የምትገኝና ፔሩና ኮሎምቢያን የምትጎራበት ሀገር ስትሆን የሕዝቧ ቁጥር17 ሚሊዮን ይጠጋል።

# ነፃ ሃሳብ

# የኢትዮጵያ የዲፕሎማሲ ጉዞ ከድሮ እስከ ዘንድሮ

**እስማኤል አረቦ**

ዲፕሎማሲ በሀገራትና መንግሥታት እንዲሁም በዓለም አቀፍ ተቋማት መካከል የሚካሄድ ዘርፈ ብዙ የውጭ ግንኙነቶች የሚከወኑበት ሁነኛ ጥበብ ነው። የዲፕሎማሲ ዋና ተግባር በአገራት መካከል ዓለም አቀፍ ግንኙነቶችን ማስተዳደር እና ሰላማዊ ግንኙነትን ማረጋገጥ ፤ የንግድ ስምምነት ድርድሮችን፣ በጋራ ችግሮች ዙሪያ ውይይትን፣ አዳዲስ ፖሊሲዎች መተግበርን እና አለመግባባቶችን በሰላማዊ መንገድ መፍታትን ያካትታል፡፡

ዲፕሎማሲ ወይንም የኹለትዮሽ ግንኙነት ማለት ሀገራት በሰላማዊ መንገድ እርስ በእርሳቸው አገራዊ ጉዳዮቻቸውን የሚፈጽሙበት እና ሰጥተው በመቀበል መርህ የየአገራቸውን ብሔራዊ ጥቅም የሚያስከብሩበት መንገድ ነው። ኢትዮጵያም ጥንታዊ የዲፕሎማሲ ታሪክ ካላቸው ሀገራት አንዷ ነች፡፡

ሀገሪቱ ከጥንት ጀምሮ በሃይማኖት በባህልና በንግድ እንቅስቃሴ ከበርካታ ሀገራት ጋር የጠነከረ ግንኙነት መሰረት የጣለችና በዲፕሎማሲው መስክም ተጠቃሽ ተሞክሮ ማዳበር የቻለች ሀገር ነች፡፡ ከዋሻ ዲፕሎማሲ ዛሬ እስከ ደረስንበት እስከ ዘመነኛው የዲጂታል ዲፕሎማሲ ድረስ ዕምቅ ታሪክና ተሞክሮ ያላት ነች፡፡

በእነዚህ የዲፕሎማሲ ሂደቶች ኢትዮጵያ በውጭው ዓለም ገናና ሆና እንድትታይና ሉላዊነቷና አንድነቷ ተጠብቆ እንዲቆይ ያስቻሉ ስራዎች ተከናውነዋል። በየዘመናቱ የነበሩ የኢትዮጵያ መሪዎችም ሀገሪቱን ከውጭውም አለም ጋር የሰመረ ግንኙነት እንዲኖራትና አልፎ ተርፎም ተጽዕኖ ፈጣሪ ሀገር እንድትሆን ዘርፈ ብዙ ግንኙነቶችን ሲመሰርቱ ቆይተዋል፡፡

በዘመነ አክሱም የዲፕሎማሲ ዘመን የሁለትዮሽና የባለብዙ ወገን ዲፕሎማሲያዊ መሰረቶች ተጥለዋል።ከእነዚህ መካከል በንጉስ ኢዛና ዘመን ንግድና ኃይማኖትን መሰረት ያደረጉ ግንኙነቶች ተፈጥረዋል፡፡ ወደ መካከለኛው ዘመን ስንመጣ የዲፕሎማሲው ዋነኛ አቅጣጫ የሀገርን ሉአላዊነትና አንድነትን ማጽናት ነበር፡፡

ኢትዮጵያ ከውስጥም ከውጭም የሚመጡባትን የሉአላዊነት አደጋዎች በመጋፈጥና አንድነቷን አስጠብቆ መሄድ የዲፕሎማሲው ቁልፍ አቅጣጫ ነበር፡፡በተለይም በኃይማኖትና በባህል ታጥሮ የቆው የዲፕሎማሲ ግንኙነት ወደ ንግድና ወታደራዊ ግንኙነት ያደገበት ጊዜ ነበር፡፡

19ኛው ክፍለ ዘመን የአውሮፓና የኢትዮጵያ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ያንሰራራበት ፤ አውሮፓውያን የአፍሪካ አህጉርን በተጠናከረ ሁኔታ ማሰስ የጀመሩበት ጊዜ ነበር፡፡ አውሮፓውያን በሳይንስ ምርምር እና በሚሽነሪዎች አማካኝነት የክርስትና ሃይማኖትን ለማስፋፋት ከፍተኛ ጥረት ያደርጉ ነበር፡፡ በተጨማሪም ንግድን ማስፋፋት ሌላው ዓለማቸው ነበር፡፡

በወቅቱ የነበሩት የኢትዮጵያ መሪ አጼ ቴዎድሮስ ሀገራችውን ከዘመነ መሣፍንት ትርምስ በመታደግ አንድነቷን ለማረጋገጥና ለማዘመን ራዕይ ሰንቀው መታገል ቢጀምሩም በአገር ውስጥ የተጠናከረ አመጽ ስለተነሳባቸው ይህንኑ ለማስታገስ ላይ ታች የሚሉበት ጊዜ ነበር፡፡ በተጨማሪም ከአውሮፓ የመጡ የሃይማኖት ሰባኪዎች ጋር ግብግብ በመግጠም ለአገራቸው የሚያስፈልጋት የቴክኖሎጂ ፈጠራ ስራዎችን ማስፋፋት እንጂ የሃይማኖት ትምህርትማ እዚህ ያሉት የኔ ሰዎች ምን ይሰራሉ በማለት ይሞግቱ ነበር፡፡

የአጼ ቴዎድሮስ አገራዊ የተማከለ አስተዳደር የመፍጠርና የማፅናት ትግል ጠንካራ በሆነ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ታጅቦ እ.ኤ.አ በ1861 ዓ.ም ተጀመረ። በዚህም በ1862 ዓ.ም ለታላቋ ብሪታኒያ ንግስት ቪክቶሪያ በወቅቱ ለኢትዮጵያ ሉዐላዊነትና የግዛት አንድነት ስጋት ነው ባሉት ጉዳይ ላይ ካሜሩን በተባለ የእንግሊዝ ቆንሲል አማካይነት የትብብር ጥያቄና መልዕክት ፣መላካቸውን የታሪክ መዛግብ ያትታሉ ፡፡

የብሪታኒያ መንግሥት ይህን የትብብር ጥያቄ ሳይቀበለው በመቅረቱና መልስ በማጣታቸው ንጉሱ ተቆጥተው የብሪታኒያ መልክተኞችን እና ሌሎች አውሮፓዊያንን አማሰራቸው፤ይህ ርምጃቸው በሁለቱ መንግሥታት መካከል ዲፕሎማሲያዊ መቃቃር በመፍጠሩ ብሪታኒያ ጦር ወደማዝመት አድርሷታል።

በ1868 ዓ.ም በታላቋ ብሪታንያ ወራሪ ኃይልና በአፄ ቴዎድሮስ መካከል በመቅደላ ጦርነት ተካሄዷል ፤በወቅቱ አጼ ቴዎድሮስ የውስጥ ድጋፍ በማጣታቸውም በመቅደላ ለመሸነፍ የተገደዱበት እውነታ ተፈጥሯል ፡፡

በተመሳሳይም ከአጼ ሚኒሊክ አሁን እስከ ያሉ መሪዎች በሙሉ በየዘመናቸው የውጭ ወራሪዎችን በመመከትና የኢትዮጵያን አንድነትና ሉአላዊነት በማስከበር ረገድ የበኩላቸውን ተጋድሎ ሲያደርጉ ቆይተዋል፡፡ በተለይም አጼ ሚኒሊክም እና አጼ ኃይለ ስላለሴ ጣሊያንን የሚረቱበትን ዲፕሎማሲ ሲያማትሩና በተቻላቸው አቅም ሁሉ መሲዮኖቻቸውን በማሰማራት የሀገር ሉላዊነትና አንድነትን በሚያጠናክሩ ጉዳዮች ላይ ትኩረት ሰጥተው ተንቀሳቅሰዋል ፡፡

በተለይ ኢትዮጵያ ከአጼ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት (ከ1950ቹ) ጀምሮ የአፍሪካ አንድነት አስጠባቂ መሠረት፣ የፓን አፍሪካኒዝም መከታ ሆኖ ዘልቃለች፡፡ በዚህም ኢትዮጵያ በየዘመናቱ የሚያጋጥማትን የሉአላዊነት ፈተናዎች በማለፍ ከራሷ አልፋ ሌሎች ጥቁር ህዝቦች መከታ በመሆን ዛሬ ላይ ደርሳለች፡፡የአፍሪካ አንድነትን በመመስረትና ለአፍሪካ ህብረት መመስረት ጉልህ አስተዋጽኦ በማበርከት የአፍሪካ ዲፕሎማሲ አንድርምጃ እንዲጓዝ የበኩሏን ድርሻ ተወጥታለች።፡

እንደሀገር ለዲፕሎማሲና ለውጭ ግንኙነት ትኩረት ከተሰጠ 116 ዓመታት የተቆጠሩ ሲሆን በእነዚህ አመታት በርካታ ፈተናዎችንና ስኬቶችን በማስመዝገብ ኢትዮጵያን ከነሙሉ ክብሯ ለዛሬው ትውልድ ለማስረከብ ተችሏል፡፡ 116 አመታትን ያስቆጠርው የኢትዮጵያ ዘመናዊ ዲፕሎማሲ በተለይ ባለፉት አምስት አመታት አዳዲስ ገጽታዎችን በመላበስ አድማሱን አስፍቶ ቀጥሏል፡፡

በተለይም ለቀጠናዊ ግንኙነት የመጀመሪያውን ትኩረት በመስጠት ኢትዮጵያ ከጎረቤት ሀገራት ጋር የጠበቀ ዲፕሎማሲያ ግንኙነት እንዲኖራት ተደርጓል፡፡ የኢትዮጵያ ልማት በአስተማማኝ መሠረት የሚቆመው የኢትዮጵያ የውስጥ ሰላምና መረጋጋት ሲረጋገጥ እንደሆነ እና ይኸው ሰላምና መረጋጋት የሚጸናው ደግሞ ከጎረቤት አገራት ጋር ሰላማዊ ግንኙነትን በማዳበርና የአገራቱ ሰላምና መረጋጋት ሲረጋገጥ ነው።

ለዚህም ከጎረቤት አገራት ጋር በወዳጅነት፣ በትብብርና ኢኮኖሚያዊ ትስስርን በሚያመጣ መልኩ የተቃኘ ዲፕሎማሲ በመስራት መሆኑን ያስቀምጣል። ይህንኑ መሰረት በማድረግ ጠቅላይ ሚኒስትር አብይ አህመድ(ዶክተር) ወደ ስልጣን በመጡ በጥቂት ቀናት ውስጥ የመጀመሪያ የውጭ ጉዟቸውን ያደረጉት ወደ ጎረቤት ሀገር ጂቡቲ ነው፡ ፡

ጂቡቲ ለኢትዮጵያ 95 በመቶ የወደብ አገልግሎት የምትሰጥ በመሆና እና ሁለቱ ሀገራት በኢኮኖሚው መስክ ከፍተኛ ትስስር ያላቸው ከመሆናቸው አንጻር ከጎረቤት ሀገራት ጂቡቲን ማስቀደማቸው ተገቢ ነበር ማለት ይቻላል፡ ፡ ከዚያም ጠቅላይ ሚኒስትሩ ያቀኑት ወደ ሱዳን ሲሆን በቀውስ ውስጥ የነበረችውን ሀገር ወደ ተሻለ መረጋጋት የሚወስድ የአስታራቂነት ሚና ተጫውታለች፡፡

በመቀጠልም ለ20 ዓመታት ያህል በጦርነት ስጋት ውስጥ የቆዩትን ኢትዮጵያንና ኤርትራን በማስታረቅና ግንነታቸውንም ወደ ተሻለ ደረጃ በማድረስ ቀጠናዊ ዲፕሎማሲው ወደ ከፍታ እንዲሸጋገር ኢትዮጵያ የመሪነቱን ሚና ተወጥታለች ፡፡ኢትዮጵያ በአፍሪካ ቀንድ ቀጠና ብሎም በአፍሪካ ደረጃ ሰላም አስጠባቂ ኃይል ሆና መውጣት ችላለች።

> **በዚህም ኢትዮጵያ በየዘመናቱ የሚያጋጥማትን የሉአላዊነት ፈተናዎች በማለፍ ከራሷ አልፋ ለሌሎች ጥቁር ህዝቦች መከታ በመሆን ዛሬ ላይ ደርሳለች።የአፍሪካ አንድነትን በመመስረትና ለአፍሪካ ህብረት መመስረት ጉልህ አስተዋጽኦ በማበርከት የአፍሪካ ዲፕሎማሲ አንድ ርምጃ እንዲጓዝ የበኩሏን ድርሻ ተወጥታለች**

የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ የጎረቤት አገራትን ሰላምና መረጋጋት የራስ ሰላምና መረጋጋትን ማስጠበቂያ መንገድ ነው ብሎ ስለሚነሳ፣ ኢትዮጵያ በተመድ እና በአፍሪካ ሕብረት ማዕቀፍ በአፍሪካ ቀንድ ብሎም በመላ አፍሪካ በሚከሰቱ ግጭቶች በወታደራዊ መስክ ሰላም አስከባሪ፣ በፖለቲካ መስክም የሰላም ሂደቶች (peacemaking) ዋና ተዋናይ በመሆን በአለም አቀፉ ማኀበረሰብ ዘንድ በጎ ገጽታ መገንባት እና በቀጠናውም ዋና የሰላም አስጠባቂ ኃይል ሆና እንድትወጣ ያስቻለ ዲፕሎማሲ ተሰርቷል።

ሌላው ባለፉት አምስት ዓመታት በዲፕሎማሲው መስክል ላይ የታየው እምርታ ኢትዮጵያ ኢትዮጵያ ዜጋ ተኮር ዲፕሎማሲ መከተሏ ነው፡፡አዲስ በሆነው በዚህ ዜጋ ተኮር ዲፕሎማሲ በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ የበሩ በርካታ ኢትዮጵያውያን ወደ ሀገራቸው በክብር ለመመለስ ችለዋል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ(ዶክተር) በሱዳን በነበሩበት ወቅት በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ በእስር ቤት ይኖሩ የነበሩትን በማስፈታት በታሪክ ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ ለመጀመሪያ ጊዜ ራሳቸው በተሳፈሩበት አውሮፕላን ከልዑካቸው ጋር ወደ ሀገር ቤት እንዲጓዙ ማድረጋቸው መንግሥታቸው ለዜጋ ተኮር ዲፕሎማሲ ያለውን ቁርጠኝነት ያሳየ ነበር፡፡

ለበርካታ ሀገራት በምሳሌነት የሚጠቀስና የዘመናዊ ዲፕሎማሲ አዲስ ማሳያ ተደርጎ የሚወሰድ አንዱ ክስተት ኢትዮጵያ የተከተለችው አረንጓዴ ዲፕሎማሲ ነው፡፡ኢትዮጵያ ባለፉት አምስት አመታት ከ32ነጥብ 5 ቢሊዮን በላይ ችግኞችን በመትከል አለም አስደንቃለች።በእነዚሁ አመታት አረንጓዴ አሻራ የአካባው መድህን መሆኑን በመረዳት ከራሷ አልፎ የጎረቤት ሀገራትም ተጠቃሚ እንዲሆኑ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ችግኞች ወደ ጎረቤት ሀገራት በመላክና አብሮ በመትከልም የጋራ አካባቢን በጋራ የመጠበቅ መርህ እውን እንዲሆን መሰረት ጥላለች፡፡

ከዚሁ ጎን ለጎንም የጎረቤት ሀገራት በኃይል አቅርቦት እንዲተሳሰሩ ኢትዮጵያ እያከናወነችው ያለችውም ተግባር አንዱ የኃይል አቅርቦት ዲፕሎማሲ ነው፡፡ኢትዮጵያ ከአባይ ግድብ እና ከግልገል ግቤ ሶስት የኃይል ማመንጫዎች የምታገኘውን ኃይል ከራሷ አልፋ የጎረቤት ሀገራትን ልማት እንዲያቀላጥፍ ለኬንያ፤ለጅቡቲ፤ለሱዳን፤ለደቡን ሱዳን ኃይል በማቅረብ ላይ ትገኛለች፡፡

ዘመናትን የዋጀው የኢትዮጵያ የዲፕሎማሲ ጉዞ ሀገርን አጽንቶ ህዝብን ማዕከል አድርጎ ዛሬ ላይ ደርሷል፡፡ዛሬም ግስጋሴውን ቀጥሎ ከሀገር አፍሎ ቀጠናዊ ትስስርን ማዕከል አደርጎ ዕይታውን አስፍቷል።ከመንግሥት ለመንግሥት ግንኙነት አልፎ ወደ ኢኮኖሚያዊና ቀጠናዊ ትስስር የሰፋው ዲፕሎማሲዊ ግንኙኘትም አዲስ ገጽታ የተላበሰ ከመሆኑም ባሻገር ኢትዮጵያን በዲፕሎማሲው መስክ ያላትን ተጽዕኖ ፈጣሪነት የሚያጎላ ነው፡፡

ከጥንት እስከ ዛሬ የኢትዮጵያ ዲፕሎማሲ አንዱ መለያ ስደተኞችን የመቀበል ዲፕሎማሲ ነው፡፡ ኢትዮጵያ በቀደመ ታሪኳ የፍልሰት መነሻ ሳትሆን መዳረሻ ነበረች። ከተለያዩ ሀገሮችም ፈልሰው የመጡ የሌላ ሀገር ዜጎችን ማለትም አይሁዶንች፣ አርመኖችን፣ ዓረቦችን፣ ግሪኮችን፣ ቱርኮችንና ሌሎችን ተቀብላ በማስተናገድ ትታወቃለች፡፡የነብዩ ሞሃመድ ተከታዮችን ከተቀበለችበት ጊዜ ጀምሮ ኢትዮጵያ የበርካታ ሀገራትን ስደተኞች በመቀበል ስሟ በታሪክ ድርሳናት ጭምር የሚወሳ ነው፡፡

ኢትዮጵያ ስደተኞችን የመቀበልና የማስጠለል የረዥም ጊዜ ታሪክ አላት፡፡ አሁንም የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋዎችን በመሸሽ ሀገራቸውን ጥለው የሚሰደዱ የጎረቤት ሀገር ዜጎችን አስጠልላለች። በዚህም ወደ አንድ ሚሊዮን ለሚጠጉ ስደተኞች ኢትዮጵያ ቤታቸው ሆናለች፡፡ ይሄም ሰብዓዊነት ብቻ ሳይሆን ዓለም አቀፋዊ ግዴታዋን ለመወጣት ያላትን ቁርጠኝነት ያሳያል።

የቡና ዲፕሎማሲ ሌላኛው የኢትዮጵያ ዲፕሎማሲ መገላጫ ነው፡፡ኢትዮጵያ የቡና መገኛ ሀገር እንደመሆኗ መጠን ቡናን በማስቀደም በየትኛውም ሀገር በሚዘጋጁ ባዛሮችና ኤግዚቢሽኖች ላይ በመሳተፍ ዲፕሎማሲያዋን በማጠናከር ላይ ትገኛለች፡፡ኢትዮጵያን የሚጎበኙ የሀገር መሪዎችም የኢትዮጵያን ጥዑም ቡና እንዲቀምሱ በማድረግ አይረሴ ጊዜ እንዲያሳልፉና ኢትዮጵያን ከልባቸው እንዲያኖሩ የማድረግ ስራ ሲሰራ ቆይቷል፡፡ 44ኛው የአሜሪካው ፕሬዚዳንት ባራክ አባማ የዚሁ ዕድል ተቋዳሽ ነበሩ፡፡

ዓለም በፈጣን የቴክኖሎጂ ለውጥ ውስጥ ትገኛለች፡፡ ዲፕሎማሲውም እንደጥንቱ በሰው አቅም ብቻ ሳሆን በቴክኖሎጂ የሚታገዝበት ደረጃ ላይም ደርሷል፡፡ ይህን መነሻ በማድረግም ዲጂታል ዲፕሎማሲን ሁነኛ የዲፕሎማሲ ማሳለጫ መንገድ ማድረግ ጀምራለች፡፡ የዲጂታል ዲፕሎማሲ አውዶችን የንግድና ኢንቨስትመንት አማራጮችን በማስተዋወቅ፣ የኢኮኖሚ አቅሟን ለማሳየት እንዲሁም የውጭ ኢንቨስተሮችን ለመሳብ ትኩረት ሰጥታ እየሰራች ትገኛለች፡፡

ኢኮኖሚ

# ኢንቨስትመንት

## አበረታች አፈጻጸም የተመዘገበበት የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት

አንተነህ ቸሬ

የደቡብ ምእራብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ክልል በግብርና፣ በማእድን፣ በቱሪዝም፣ በኢንዱስትሪና በመሳሰሉት ዘርፎች ለሚካሄዱ የኢንቨስትመንት ስራዎች ሊውሉ የሚችሉ እምቅ ሀብቶች ያሉት ክልል ነው፡፡ ክልሉ አስደናቂ የሆነ መልከዓምድራዊ አቀማመጥ፣ ልምላሜና የተፈጥሮ ሀብት ያለው በመሆኑም የባለሀብቶችን ትኩረት የሚስብ መሆኑ አያጠያይቅም፡፡

ለኢንቨስትመንት ሊውሉ የሚችሉ የክልሉን ሀብቶች ለመለየት የተደረጉ ጥናቶች እንዳመለከቱትም፤ ክልሉ ለዓመታዊ ሰብሎች፣ ለቡናና ቅመማ ቅመም እና ለአትክልትና ፍራፍሬ ልማት የሚውል ሰፊና ምቹ መሬት አለው፡፡ ክልሉ ከፍተኛ መጠን ያለው የቡና ምርት ለማእከላዊ ገበያ በማቅረብም ይታወቃል፡፡

በአገልግሎትና በኢንዱስትሪ ዘርፎችም እንዲሁ ክልሉ የኢንቨስትመንት መዳረሻና አማራጭ ሊሆን የሚችል ነው፡፡ ለኢንዱስትሪ ግብዓት የሚውል የድንጋይ ከሰል በክልሉ በዳውሮ እና በኮንታ አካባቢዎች በስፋት ይገኛል። በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች በባለሀብቶች እየተገነቡ ከሚገኙ የድንጋይ ከሰል ማጠቢያ ፋብሪካዎች አንዱ እየተገነባ የሚገኘውም በእዚሁ ክልል ስለመሆኑ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ በእዚህም ክልሉ የሀገሪቱን የድንጋይ ከሰል ፍላጎት ለማሟላት እየሰሩ ከሚገኙ ክልሎች አንዴ መሆን ችሏል፡፡

ክልሉ በወርቅ ማእድን ሀብቱና ምርቱም ይታወቃል፡፡ በአሁኑ ወቅት ከፍተኛ መጠን ያለው ማዕድን ምርት ለማዕከላዊ የገበያ ከሚያቀርቡ የሀገሪቱ አካባቢዎች መካከል አንዱ ሆኗል፡፡ ኦፓልና ሌሎች ማዕድናትም በክልሉ ይገኛሉ ተብሎ ይገመታል። በክልሉ ገና በጥናት ያልተለዩ ብዙ ሀብቶች ስለመኖራቸው መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

በአሁኑ ወቅት በክልሉ በርካታ ባለሀብቶች በተለያዩ የኢንቨስትመንት ሰራዎች ተሰማርተው እየሰሩ ይገኛሉ። የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶቹም ለበርካታ ዜጎች የስራ እድል መፍጠር ችለዋል፡፡ አሁንም በርካታ ባለሀብቶች በክልሉ በተለያዩ የኢንቨስትመንት ዘርፎች ለመሰማራት ፍላጎት ማሳየታቸውን ነው ከክልሉ የተገኘ መረጃ ያመለከተው፡፡

የክልሉ መንግሥት ኢንቨስትመንትን ለመሳብ ያከናወናቸውና እያከናወናቸው የሚገኙ ተግባሮችም እንዲሁ ክልሉን ሌላው የኢንቨስትመንት መደረሻ ካደረጉት ምክንያቶች መካከል ሊጠቀስ ይችላል፡፡ እንደ ክልል ከተዋቀረ አጭር እድሜ ያለው ቢሆንም፣ በክልሉ ኢንቨስትመንቱ ያለበትን ነባራዊ ሁኔታ የሚያሳይ ሰፊ ጥናትና ውይይት ተደርጓል፡፡

ባለሀብቶች ወደ ክልሉ ገብተው በኢንቨስትመንት ስራዎች ላይ እንዲሰማሩ ለማበረታታት የክልሉን ርዕሰ መስተዳድርና የካቢኔ አባላትን ጭምር ያሳተፈ የንቅናቄና የፕሮሞሽን ስራ በስፋት ተሰርቷል፡፡ ክልሉ ከተቋቋመ ጊዜ ጀምሮ የተሰሩት የኢንቨስትመንት ፕሮሞሽን ስራዎች በክልሉ የኢንቨስትመንት ፍሰት እንዲጨምር አስተዋፅዖ አበርክተዋል፡፡

የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል በ2015 የበጀት ዓመት አበረታች የኢንቨስትመንት አፈፃፀም ማስመዝገቡንና በ2016 የበጀት ዓመትም ይህን አፈፃፀሙን ለማሳደግ እየሰራ እንደሚገኝ የክልሉ ንግድና ኢንቨስትመንት ቢሮ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡

የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል በኢንቨስትመንት ዘርፍ በ2015 የበጀት ዓመት ያስመዘገባቸውን ስኬቶች በ2016 የበጀት ዓመትም አጠናክሮ ለማስቀጠል እቅድ አዘጋጅቶ በትግበራ ላይ እንደሚገኝ የክልሉ ንግድና ኢንቨስትመንት ቢሮ ምክትል ኃላፊና የኢንቨስትመንት ዘርፍ ኃላፊ አቶ ከበደ ተስፋዬ ያስረዳሉ፡፡

**በክልሉ ባለፉት ስድስት ወራት በግብርናው ዘርፍ ሁለት ነጥብ አንድ ቢሊዮን ብር ካፒታል ለሚያስመዘግቡ ባለሀብቶች ፈቃድ ለመስጠት ታቅዶ፣ አራት ነጥብ አራት ቢሊዮን ብር ላስመዘገቡ ባለሀብቶች የኢንቨስትመንት ፈቃድ ተሰጥቷል**

እርሳቸው እንደሚሉት፣ በበጀት ዓመቱ በግብርና 84፣ በአገልግሎት 64 እንዲሁም በኢንዱስትሪ 58፣ በአጠቃላይ ለ206 ፕሮጀክቶች ፈቃድ በመስጠት ወደ ስራ ለማስገባት ታቅዷል፡፡ እነዚህ ፕሮጀክቶች ከ11 ነጥብ አንድ ቢሊዮን ብር በላይ ካፒታል እንደሚያስመዘግቡና ከ109ሺ በላይ ለሚሆኑ ዜጎች (ሦስት ሺ 181 ቋሚ እና 105ሺ 951) የስራ እድሎችን እንደሚፈጥሩ ይጠበቃል፡፡ በክልሉ በርካታ ባለሃብቶች የተሰማሩት በግብርና ዘርፍ ነው፡፡ በርካታ ባለሀብቶች ከግብርናው ዘርፍ በተጨማሪ በማምረቻና በአገልግሎት ዘርፎች እንዲሰማሩ ማድረግ ከ2016 የበጀት ዓመት እቅዶች መካከል አንዱ ነው፡፡ ክልሉ ከግብርናው ዘርፍ ባሻገር ባለሀብቶች በማምረቻና በአገልግሎት ዘርፎች በስፋት እንዲሰማሩ የሚያስችል የመሬት ዝግጅት ተግባር አከናውኗል፡፡

በክልሉ ባለፉት ስድስት ወራት ከአራት ነጥብ አምስት ቢሊዮን ብር በላይ ካፒታል ያስመዘገቡ 38 ባለሀብቶች የኢንቨስትመንት ፈቃድ ወስደዋል። በግብርና ሁለት ነጥብ አንድ ቢሊዮን ብር ካፒታል ለሚያስመዘግቡ ባለሀብቶች ፈቃድ ለመስጠት ታቅዶ፣ አራት ነጥብ አራት ቢሊዮን ብር ላስመዘገቡ እንዲሁም በኢንዱስትሪ ዘርፍ ደግሞ 427 ሚሊዮን ብር ለሚያስመዘግቡ ባለሀብቶች ፈቃድ ለመስጠት ታቅዶ፣ 340 ሚሊዮን ብር ላስመዘገቡ ባለሃብቶች የኢንቨስትመንት ፈቃድ ተሰጥቷል፡፡

የኢንቨስትመንት አቅም (Potential) በመለየት ረገድ፣ በስድስት ወራት ውስጥ 4ሺ744 ሄክታር ለኢንቨስትመንት የሚውል መሬት ለማጥናትና ለመለየት ታቅዶ፣ 17ሺ 137 ሄክታር መሬት ተለይቷል፡፡ ከዚህ መሬት ውስጥ 6ሺ323 ሄክታር መሬት ለባለሃብቶች ለማስተላለፍ ታቅዶ፣ 8ሺ296 ሄክታር መሬት ማስተላለፍ ተችሏል፤በመሆኑም በአቅም ልየታና መሬት ማስተላለፍ ዘርፎች ከእቅዱ በእጅጉ የበለጠ አፈፃፀም ማስመዝገብ ተችሏል፡፡

ለኢንቨስትመንት የሚሆን አቅም ያለውን መሬት በማጥናት ረገድ የበጀት ዓመቱ ጠቅላላ እቅድ 12ሺ650 ሄክታር መሬት ነው ለማጥናት ታቅዶ የነበረው፡፡ መሬት የተላለፈላቸው ባለሀብቶች ለአንድ ሺ 591 ዜጎች የስራ እድል ይፈጥራሉ ተብሎ የተጠበቀ ሲሆን፣ ለ621 ዜጎች ቋሚ የስራ እድል ፈጥረዋል፡፡

አቶ ከበደ እንደሚያስረዱት፣ ቀደም ሲል መሬት ወስደው ያላለሙ ባለሀብቶችን በተመለከተ፣ የመሬት ኦዲቲንግ ተግባር በከፍተኛ ትኩረት እየተሰራ ነው፡ በስድስት ወራት 28 ፕሮጀክቶችን ኦዲት ለማድረግ ታቅዶ፣ 16 ፕሮጀክቶች ኦዲት ተደርገዋል፡፡ ከዚህም ውስጥ 14 ፕሮጀክቶች መሬት እንዲቀነስባቸውና ስምንት ፕሮጀክቶች ደግሞ ሙሉ በሙሉ መሬት እንዲነጠቁ ተደርጓል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም፣ ለ387 ፕሮጀክቶች ድጋፍና ክትትል ማድረግ ተችሏል፡፡

‹‹እንዲህ ዓይነት እርምጃዎች ካልተወሰዱ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች በታለመላቸው የጊዜ ገደብ ላይጠናቀቁ ይችላሉ፡፡ ይህ የኦዲቲንግ ሥራ መሬት ተረክበው የማያለሙ ባለሃብቶች በፍጥነት ወደ ስራ እንዲገቡ ለማድረግ ወይም መሬቱን ለሌሎች አልሚዎች ለማስተላለፍ ያግዛል፡፡ የኢንቨስትመንት አዋጁ (1180/2010) ለባለሃብቶች የተሰጡ መሬቶች ሊነጠቁ የሚችሉባቸውን ቅድመ ሁኔታዎች በግልፅ አስቀምጧል፡፡ የባለሃብቶች የስራ እንቅስቃሴዎች በእነዚህ መስፈርቶች መሰረት ተገምግመው ቅድመ ሁኔታዎቹ ካልተሟሉ መሬት እንዲነጠቁ ይደረጋል›› ሲሉ አስገንዝበዋል፡፡

የአገልግሎት አሰጣጥን ለማሻሻል በየደረጃው የሚገኙ የክልሉ ተቋማት ለባለሀብቶች መረጃ ከመስጠት ጀምሮ የተሻለ የአገልግሎት አሰጣጥ ሥርዓትን ለማስፈን ጥረት እያደረጉ ይገኛሉ፡፡ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክት ፕሮፖዛሎች በጥልቀት እንዲታዩ እንዲሁም የኢንቨስትመንት ፈቃድና መሬት በፍጥነት እንዲሰጡ እየተደረገ ይገኛል፡፡

በመሰረተ ልማት ዝርጋታ ረገድ ነባሮቹን የማጠናከር እና የተጀመሩትን የመጨረስ እንጂ አዳዲስ፣ በተለይ መንገዶችን፣ ለመገንባት የሚያስችሉ ምቹ ሁኔታዎች እንደሌሉ አቶ ከበደ ይገልፃሉ፡፡ እርሳቸው እንዳሉት፤ የበጀት እጥረት በክልሉ የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ ላይ መሰናክል ሊፈጥር የሚችለው ዋናው ችግር ነው። የክልሉ ዞኖች የሚመደብላቸው በጀት ቀደም ሲል በደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ስር በነበሩበት ጊዜ የነበራቸው በጀት ነው፡ አገሪቱ ያለችበት ነባራዊ ሁኔታም ተጨማሪ በጀት ለማግኘት የሚያስችል አይደለም፡፡

አቶ ከበደ እንደሚናገሩት፤ በበጀት ዓመቱ ስድስት ወራት ባለሃብቶችን የማነቃቃት ስራዎች ተከናውነዋል፡ በክልሉ በግብርና ኢንቨስትመንት ላይ የተሰማሩና በስድስቱም ዞኖች የሚገኙ ባለሀብቶች በፌዴራል ደረጃ በተቋቋመው የግብርና አልሚ ባለሀብቶች ማኅበር ውስጥ አባል ሆነው በንቃት እንዲሳተፉ ተደርጓል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በሁሉም ዞኖች ላይ በግብርና ኢንቨስትመንት ላይ የተሰማሩ ባለሃብቶችን በማስተባበር የሰብል አምራቾች ማኅበራት እየተቋቋሙ ይገኛሉ፡ ለአብነት ያህል በከፋ፣ ቤንች ሸኮ እና ሸካ ዞኖች ማኅበራቱ ተቋቁመዋል፤ በቀሪዎቹ ዞኖችም ማኅበራቱን ለማቋቋም እንቅስቃሴዎች እየተደረጉ ይገኛሉ፡፡

ባለፈው የበጀት ዓመት በተዘጋጀው የመሬት መጠቀሚያ ደንብ መሰረት የመሬት ክፍያ ያልከፈሉ ባለሃብቶች ክፍያ መክፈል መጀመራቸውም ትልቅ ስኬት እንደሆነ አቶ ከበደ ይናገራሉ፡፡ ‹‹በመሬት ክፍያ ረገድ በተለይ ነባሮቹ ባለሃብቶች ክፍያ መክፈል እንዳለባቸው ታምኖበት፣ ለዞን ባለሙያዎች ስልጠና በመስጠት ክፍያውን እንዲያስፈፅሙ ማድረግ ተችሏል፡፡ ይህ በበጀት አመቱ የመጀመሪያ ስድስት ወራት ከተከናወኑ በጎ አፈፃፀሞች መካከል አንዱ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል›› ይላሉ፡፡

የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ካሏቸው ፋይዳዎች መካከል አንዱ ፕሮጀክቶቹ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ በሚከናወኑባቸው አካባቢዎች የሚገኙ የማኅበረሰብ ክፍሎችን ተጠቃሚ ማድረጋቸው ነው፡፡ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል መንግሥት ባለሀብቶችን ወደ ክልሉ ሲያስገባ ባለሀብቶች በተለያዩ መንገዶች የአካባቢውን ማኅበረሰብ ተጠቃሚ እንዲያደርጉ በማሰብ ነው፡፡

ማኅበረሰቡ ከኢንቨስትመንት ስራዎች በስራ እድል ፈጠራ፣ በምርትና አገልግሎት አቅርቦት፣ በቴክኖሎጂ ሽግግርና በገበያ እድል ተጠቃሚ እንዲሆን ይጠበቃል፡ በዚህ ረገድ በክልሉ የሚከናወኑ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ለክልሉ ህብረተሰብ ዘርፈ ብዙ ፋይዳዎች እንዳሏቸው ይገልፃሉ፡፡ ‹‹በኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ ‹አንድ ባለሃብት ወደ አንድ አካባቢ ሲመጣ ለማኅበረሰቡ የሚሰጠው አገልግሎት ምንድን ነው?› የሚለው ጥያቄ ትኩረት የሚሻ ዐቢይ ጉዳይ ነው›› የሚሉት አቶ ከበደ፣ ይኸው ጉዳይ የክልሉ የኢንቨስትመንት ዘርፍ ተግባር አካል እንደሆነ ይናገራሉ፡፡

እሳቸው እንደሚያብራሩት፣ በክልሉ የሚገኙ ባለሀብቶች በሚያከናውኗቸው የኢንቨስትመንት ተግባራት አማካኝነት የስራ እድል ከመፍጠር በተጨማሪ፣ ልዩ ልዩ ድጋፎችን በማድረግ ማኅበራዊ ኃላፊነታቸውን እየተወጡ ይገኛሉ፡፡ ባለሀብቶች የኢንቨስትመንት ስራዎቻቸውን በሚሰሩባቸው አካባቢዎች የመሰረተ ልማት ዝርጋታ ተግባራትን ስለሚያከናውኑ የአካባቢው ኅብረተሰብ በዚህ ተግባር በኩል ተጠቃሚ ይሆናል፡፡ ይህ የማኅበረሰቡ ተጠቃሚነት ማኅበረሰቡ ለኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች አዎንታዊ አመለካከት እንዲኖረው አድርጓል፡፡

ባለሀብቶችን በማስተባበር ባለፉት ስድስት ወራት 39 ኪሎ ሜትር መንገድ ለመስራት ታቅዶ፣ 54 ኪሎ ሜትር መንገድ መስራት ተችሏል፡፡ ለሁለት አረጋውያን ቤተሰቦችም የመኖሪያ ቤቶች እንዲገነቡ ተደርጓል። ከዚህ በተጨማሪም የክልሉ የኢንቨስትመንት ቢሮ ባለሀብቶችን በማስተባበር ለሦስት ተማሪዎች ቋሚ የትምህርት ቁሳቁስ ድጋፍ እያደረገ ይገኛል፡፡

በቴክኖሎጂ ሽግግር ረገድ፣ ባለሀብቶች ለአርሶ አደሩ 300 ኪሎ ግራም የቡና ምርጥ ዘር አቅርበዋል፤አጠቃላይ የምርት ስልጠናዎችን ሰጥተዋል፡፡ ባለፉት ስድስት ወራት ጊዜም 425 አርሶ አደሮች የቴክኖሎጂ ሽግግር ተጠቃሚዎች እንዲሆኑ ማድረግ ተችሏል፡፡

# ስፖርት





## ቡድኑ የመጨረሻ ምዕራፍ የመጀመሪያ ጨዋታውን ሞሮኮ ላይ ያደርጋል

ብርሃን ፈይሳ

ኮሎምቢያ አስተናጋጅ የሆነችበት 11ኛው የሴቶች ከ20 ዓመት በታች ዓለም ዋንጫ ከወራት በኋላ ይጀመራል፡፡ ለዚህ ውድድር አፍሪካን የሚወክሉ አራቱ ቡድኖች ሊለዩ ከጫፍ የደረሱ ሲሆን፤ የኢትዮጵያ ከ20 ዓመት በታች ብሄራዊ ቡድንም የዓለም ዋንጫ ተሳታፊነቱን ለማረጋገጥ 180 ደቂቃዎች ብቻ ቀርተውታል፡፡ ቡድኑ ላለበት ለዚህ ወሳኝ ጨዋታም ወደ ካዛብላንካ ያቀና ሲሆን፤ ከነገ በስቲያ ከሞሮኮ አቻው ጋር የሚገናኝ ይሆናል፡፡

አራት ዙሮች ያሉትን የማጣሪያ ጨዋታ አልፎ የመጨረሻው ምዕራፍ ላይ የደረሰው የኢትዮጵያ ብሄራዊ ቡድን ተሰባስቦ ለዚህ ጨዋታ የሚሆነውን ዝግጅት ከታህሳስ 7/2016 ዓ.ም አንስቶ ሲያከናውን ቆይቷል፡፡ በ35 ሜዳ እና በእድሳት ላይ በሚገኘው አንጋፋው አዲስ አበባ ስታዲየም ሲያደርግ የቆየውን ዝግጅት አጠናቆም ከትናንት በስቲያ ምሽት ወደ ስፍራው አቅንቷል። ለቡድኑም የኢፌዴሪ ባህልና ስፖርት ሚኒስትር የስፖርት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ አምባሳደር መስፍን ቸርነት፣ የፌዴሬሽኑ ፕሬዚዳንት ኢሳያስ ጅራ፤ እንዲሁም የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት በተገኙበትም ሽኝት ተደርጎለታል፡፡ ከሽኝቱ አስቀድሞም የብሄራዊ ቡድኑ ዋና አሠልጣኝ ፍሬው ኃይለገብርኤል ዝግጅቱን በሚመለከት መግለጫ የሰጡ ሲሆን፤ ቡድናቸው በዓለም ዋንጫው ተሳታፊ እንድትሆን የሚያስችላትን ዝግጅት ሲያደርጉ መቆየታቸውን ጠቁመዋል፡፡

ቡድኑ ከሳምንታት በፊት ጥሪ የተደረገለት ከፕሪምየር ሊጉ ለተውጣጡ 31 ተጫዋቾች መሆኑን ያወሱት አሠልጣኙ፤ በሂደት ወደ 23 ዝቅ ቢደረግም የአንዲት ተጫዋች ፓስፖርት በመበላሸቱ 22 ተጫዋቾችን ይዘው ለመጓዋዝ መገደዳቸውን ጠቁሟል፡፡ ሞሮኮን ለመግጠም ዝግጅት ሲደረግ ቢቆይም በሚፈለገው ልክ ግን ሊሆን አልቻለም፤ ይኸውም የዝግጅቱ አንድ አካል እንዲሆን የጠየቁት የወዳጅነት ጨዋታ ባለመሳካቱ ነው፡፡ አሠልጣኙ ሁለት የወዳጅነት ጨዋታ ዕድሎች እንዲመቻችላቸው ፌዴሬሽኑን ቢጠይቁም ምላሽ አለመሰጠቱ ጫና ይኖረዋል፡፡ በአንጻሩ ተጋጣሚያቸው የሞሮኮ ብሄራዊ ቡድን ከአልጄሪያ እና ቦትስዋና ቡድኖች ጋር የወዳጅነት ጨዋታዎችን ያደረገ ሲሆን፤ ከዚህም የጥቂት ደቂቃ ተንቀሳቃሽ ምስል በመመልከት አጨዋወታቸውን ለመገንዘብ ተሞክሯል፡፡

በዚህም፣ በርካታ ፕሮፌሽናል ተጫዋቾች ያሏት ሞሮኮ ፈጣን አጨዋወት ያለው ቡድን ያላት ሲሆን፤ የተሻለ ሆኖ ለመገኘት ጥረት እንደሚደረግም አሠልጣኙ አብራርተዋል። ከዚህ ባለፈ በሞሮኮ ያለው የአየር ሁኔታ ተለዋዋጭ እንደመሆኑ ከጨዋታው 7 ቀናትን አስቀድሞ በመጓዝ የአየር ሁኔታውን ለመላመድ እንዲቻል ጥያቄ ያቀረቡ ቢሆንም ይሁንታን አላገኙም፡፡ ሆኖም ባሉት ቀናት አስፈላጊውን ዝግጅት በማድረግ፣ እንዲሁም ከ17 ዓመት በታች እና ከ20 ዓመት በታች ከነበሩት ብሄራዊ ቡድኖች የተሰባጠረው ቡድናቸው ካለፉት ጨዋታዎች ልምድ እያገኘ መምጣቱን ተከትሎ ዓላማውን ለማሳካት ከፍተኛ ጥረት የሚደረግም ይሆናል። በተጨማሪም የቀድሞ ብሄራዊ ቡድን ተጫዋች የነበሩ የአሠልጣኞች ቡድን አባላትን ጨምሮ በባለሙያዎች የሥነልቦና ጫና ውስጥ እንዳይገቡ የተሰራው የማነቃቂያ ሥራ ተጫዋቾቻቸውን እንደሚያግዝም አሠልጣኙ አንስተዋል፡፡

በየሁለት ዓመቱ የሚደረገው ይህ ውድድር ቀድሞ 16 ቡድኖችን የሚያሳትፍ ቢሆንም ከዚህ ዓመት ጀምሮ ግን ቁጥሩን ወደ 24 በማሳደግ ይካሄዳል፡፡ የአፍሪካ እግር ኳስ ኮንፌዴሬሽን (ካፍ) በአራት ቡድኖች የሚወከል ሲሆን፤ በማጣሪያውም 35 ቡድኖችን ሲያጫውት ቆይቷል፡፡ እስከ አራተኛው ዙር የደረሱ ስምንት ቡድኖች (እነዚህም ኢትዮጵያ እና ሞሮኮን ጨምሮ፤ ሴኔጋል፣ ጋና፣ ግብጽ እና ካሜሮን ናቸው) ከነገ ጀምሮ ጨዋታቸውን በማከናወን በደርሶ መልስ አሸናፊ የሚሆኑት ወደ ኮሎምቢያ የሚጓዙ ይሆናል። ኢኳቶሪያል ጊኒን እና ማሊን በመርታት ለመጨረሻው ዙር የደረሰው የኢትዮጵያ ብሄራዊ ቡድንም በመጪው ቅዳሜ ከሜዳው ውጪ ጨዋታውን ካደረገ በኋላ እጣ ፋንታውን የሚወስንበትን የመጨረሻ 90 ደቂቃ ከቀናት በኋላ በሜዳው (አበበ ቢቂላ ስታዲየም) ያካሂዳል፡፡



ከ20 ዓመት በታች የኢትዮጵያ ብሄራዊ ቡድን የመጨረሻው ዙር የማጣሪያ ጨዋታውን ከነገ በስቲያ ሞሮኮ ላይ ያከናውናል


### ትግራይ ክልል

የባለንብረት ስም፣ ጌታቸው ሃይሉ ካሕሳይ የሰሴዳ ቁጥር፣ 03-55308 ኢት የተሽከርካሪው አይነት የጭነት የሻሲ ቁጥር፣ LZZ5ELSD0CD723062 ሞዴል፣ ZZ3257N3447A የሞተር ቁጥር፣WD615.47*120707015337 የሊብሬ ቁጥር፣ 0120502 ከላይ የተጠቀሰው ተሽከርካሪ ባለንብረት በ17/04/2016 ዓ/ም የኋላ ሰሌዳ ስለጠፋብኝ ምትክ ይሰጠኝ ብለው በማመልከቻ ጠይቀዋል። ስለዚህ ሰሴዳውን ወድቆ ያገኘ ወይም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካላቀረቡ ለአመካቹ ተለዋጭ ሰሌዳ የምንሰጣቸው መሆኑን እናሳውቃለን።

**በትግራይ ክልል ጊዜያዊ አስተዳደር የመቐለ ከተማ ትራንስፖርት ጽ/ቤት**

### ኦሮሚያ ክልል

የባለንበረቱ ስም ወ/ሮ ማማዬ ተሾመ የሆነ ተሽከርካሪ ሰሌዳ የኋላ ሰሌዳ ቁጥር 01-50775 ኦሮ ጠፍቶብኛል ብለው ለመስሪያ ቤታችን አመልክተዋል። በዚህ መሠረት ይህን ሰሌዳ ወድቆ፣ ተሰርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ይህ ባይሆን ግን ለአመልካቹ ተለዋጭ ሰሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልጻለን።

**በኦሮሚያ ክ/መ የሻሸመኔ ከተማ ትራንስፖርት ኤጀንሲ**

### ማስታወቂያ

ለሀዛል ሪል እስቴት አ.ማ አባላት በሙሉ የሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ጽ/ቤት ተወካይ በተገኙበት ሐምሌ 9 ቀን 2015ዓ/ም በተደረገው የማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ላይ ካፒታል ለማሳደግ የመነጨውን 403,000(አራት መቶ ሶስት ሺ)አክሲዮን ለአባላቱ ለመደልደል በተደረገው ውይይት እያንዳንዱ አባላት በስሙ የሚደለደለውን የአክሲዮን ድርሻ ክፍያ ከሐምሌ 9 ቀን 2015ዓ/ም ጀምሮ እስከ ጥር 8 ቀን 2016ዓ/ም ድረስ ባለው 6ወር ውስጥ ክፍሎ እንዲያጠናቅቅ በዚህ በተሰጠው ጊዜ ውስጥ የሚጠበቅበትን ሙሉ ክፍያ ያላጠናቀቀ አባል የከፈለበትን የአክሲዮን ድርሻ ብቻ ይዞ በአባልነት እንዲቀጥልና ያልተከፈለባቸው አክሲዮኖች በሙሉ ማህበሩ መዝግቦ ለአባላት ሽያጭ እንዲያቀርብ ተብሎ በተወሰነው መሰረት የሚጠበቅባችሁን 2,500,000(ሁለት ሚሊዮን አምስት መቶ ሺብር ) በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ እንድትከፍሉ እያሳሰብን ከ 2,100,000 (ሁለት ሚሊዮን አንድ መቶ ሺ ብር ) በታች መዋጮ የከፈላችሁ ቅጣት የተወሰነባችሁ በመሆኑ የምትከፍሉትን የቅጣት መጠን በማህበሩ ጽ/ቤት በመገኘት በሚነገራችሁ የቅጣት መጠን መሰረት ከዋናው መዋጮ ጋር አካታችሁ እንድትከፍሉ እናስታውቃለን ።

**ሀዛል ሪል እስቴት አ.ማ**

### አዲስ አበባ አስተዳደር

የባለንብረት ስም ወ/ሮ ሰምሀር እቁባይ ክ/ማርያም የሰሌዳ ቁጥር ኢት 03-01-27255 የተሽከርካሪው አይነት ልዩ ጎታች የሻሲ ቁጥር WJMS3TPSOOC113602 ሞዴል MP720E37HT የሞተር ቁጥር 8210.42K3420.587748 የሊብሬ ቁጥር 0032685 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው 24/4/2016 አመልክተዋል፡፡ ሠሌዳውን ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የአራዳ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም የማነ ገ/ሀዋርያት ገ/ፃድቅ የሰሌዳ ቁጥር አአ 02-01-B61889 የተሽከርካሪው አይነት የመስክ ተሽከርካሪ የሻሲ ቁጥር 1J4FJ28BPL609526 ሞዴል JEEP(CHOROKEE) የሞተር ቁጥር F073134 የሊብሬ ቁጥር 180604 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው 3/3/2016 አመልክተዋል፡፡ ሠሌዳውን ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የን/ስ/ላ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

### የንግድ ምልክት ዕድሳት ማስታወቂያ

| | | |
|---|---|---|
| 1. | የባለቤቱ ስምና አድራሻ | ታታ ሰንስ ፕራይቬት ሊሚትድ (Tata Sons Private Limited) |
| | | Bombay House, 24 Homi Mody Street, Mumbai – 400 001, India |
| 2. | የማመልከቻ ቁጥር | FTM/6850/2015 |
| 3. | የዕድሳት ጊዜ | ከ09/11/2022 እስከ 09/11/2029 |
| 4. | የንግድ ምልክቱ | TATA |
| 5. | ባለቤቱ ይህንን የንግድ ምልክት የሚጠቀመው በዓለም-አቀፍ ምድብ 12 በ03/08/2008 ዓ.ም. በአዲስ ዘመን ጋዜጣ Vol.LXXVI No.213 በወጣው ማስታወቂያ ከተዘረዘሩት ምርቶች ጋር በተያያዘ ነው፡፡ | |
| 6. | ማንኛውም ግለሰብ ወይም ሕጋዊ ሰውነት ያለው ተቋም - ከባለቤቱ ሳያስፈቅድ በዚህ የንግድ ምልክት በሚገለገል ወይም አስመስሎ በሚሠራ ላይ በሕግ ክስ ይመሠረትበታል። የኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ባለስልጣን ADDIS ZEMEN VOl-LXXXIII No-122 2/5/2016 (11/1/2024) | |